ነገሬ-ኢትዮጵያ

ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን እንናገራለን!

ቅፅ 1 ቁጥር 7 | አርብ መጋቢት 26 2006 ዓ.ም. | ዋጋ 8.00

የሚሊዮኖች ድምጽ ለነጻና ፍትሃዊ ምርጫ 13

የ2007 ምርጫ ከወዲሁ ትኩረት ይሻል! 2

የማዕድኑ ሙስና በኢትዮጵያ 7



የመምህራን ፍዳ 3

ከሙስሊሞች እንቅስቃሴ በስተጀርባ 5

የሂውማን ራይትስ ዎች የቴሌኮም እና ኢንተርኔት ቁጥጥር በኢትዮጵያ ሪፖርት

HUMAN RIGHTS WATCH

የሰማያዊ ፓርቲ አባላት ደም ሊለግሱ ነው

አዲስ አበባ፡- የሰማያዊ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች እሁድ መጋቢት 28 ቀን 2006 ዓ.ም የበጎ ፈቃድ ደም ልገሳ ሊያደርጉ ነው፡፡ በሰማያዊ ፓርቲ የሴቶች ጉዳይ አስተባባሪነት የተዘጋጀው ይህ ፕሮግራም ቀጣይ እሁድ ከቀኑ 7 ሰዓት ጀምሮ ‹‹በጎ ፍቃደኝነት ለነጻነት›› በሚል መርህ በፓርቲው ጽህፈት ቤት እንደሚደረግ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ዋና ዓላማውን በወሊድ ጊዜ በሚፈጠር

ወደ ገፅ 6 ይዞራል

አንድነት ዕሁድ የተቃውሞ ሰልፍ ያደርጋል

አዲስ አበባ፡- አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ (አንድነት) በአዲስ አበባ ከተማ የሚታዩትን የማህበራዊ አገልግሎት ችግሮች ለመቃወም ዕሁድ መጋቢት 28 ቀን 2006 ዓ.ም በከተማዋ ሰልፍ እንደሚያካሂድ አስታውቋል፡፡

ፓርቲው እንዳስታወቀው በከተማዋ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ እያጋጠመ ያለውን የመብራት፣ የውሃ እና የስልክ መቆራረጥ ችግሮች እንዲሁም በርካታ የህዝብ ገንዘብ የወጣባቸው መንገዶች ለምረቃ በበቁ በጥቂት ቀናት ልዩነት መፍረሳቸው፣ ነዋሪውን ማንገላታቱን ለመቃወም ሰልፉን ያደርጋል፡፡ ትራንስፖርት ማግኘት በሁሉም አካባቢዎች አስቸጋሪ በመሆኑ የከተማይቱ የሥራ እንቃስቃሴ መዳከሙንና፣ መንግሥት ‹‹የምትታለብ ላም›› በማለት የሚጠራው

ወደ ገፅ 6 ይዞራል

ርዕሰ አንቀጽ

የ2007 ምርጫ ከወዲሁ ትኩረት ይሻል!

ምርጫ ህጋዊ፣ ታማኒነት ያለውና ለህዝብ ይሁንታ የሚሰራ መንግስት የሚመረጥበት ዋነኛው ማዕቀፍ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ባለፉት አስርና አስራ አምስት አመታት ምርጫ ብታካሂድም በዚህ ሂደት በህዝብ አመኔታን ያተረፈ መንግስት ልትመሰርት አልቻለችም፡፡ ይህን ተከትሎም ምርጫ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር የማያመጣ ተደርጎ እንዲወሰድ አድርጎታል፡፡ ለዚህ ውድቀት ትክክለኛ ምርጫ እንዳይኖር ሌት ተቀን ከሚሰራው ገዥው ፓርቲ ባሻገር ተቀናቃኝ ፓርቲዎችም የራሳቸውን አሉታዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

ተቀናቃኝ (ተቃዋሚ) ፓርቲዎች ገዥው ፓርቲ ከሚፈጥርባቸው መሰናክል ባሻገር እራሳቸው ለሰላማዊ የስልጣን ሽግግር የሚያበቃ ምርጫ ለማድረግ ሲጥሩ አይስተዋሉም፡፡ በአብዛኛዎቹ ምርጫዎች ተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ የሚጀምሩት ምርጫ ቦርድ የጊዜ ሰሌዳ ካወጣ በኋላ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ተስፋ ጥሎባቸው የነበረውን ህዝብ ከምርጫ በኋላ ተስፋ እንዲቆርጥ ያደርጉታል፡፡ ፓርቲዎቹ ጠንካራ፣ በእውቀትና ጥናት ላይ የተመሰረተ ዝግጅት ስለማያደርጉ ትክክለኛ ምርጫ እንዲደረግ የማይፈልገውን ገዥው ፓርቲ ላይ ተገቢውን ግፊት ማድረግ አልቻሉም፡፡ ገዥውን ፓርቲ አሸንፈው ህዝብን ለመምራት በምርጫ ቦርድ የተመዘገቡት የተቃዋሚ ፓርቲዎች አንድ ምርጫ ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ አልፎ ሌላ ምርጫ እስኪመጣ ድረስ ስለ ምርጫ የሚያከናውኑት ስራ አይታይም፡፡ ወደ ታች ወርደው ለማደራጀትና ለመቀስቀስ የሚጥሩት ምርጫ ሊደርስ ወራት ብቻ ሲቀሩት ነው፡፡ በመሆኑም በገዥው ፓርቲ ፖሊሲና እርምጃዎች ደስተኛ ያልሆነውን ጨምሮ ህዝብ ውስጥ እንደ አዲስ ለመግባት ይገደዳሉ፡፡ ይህም ከወጭ፣ ከሰው ኃይልና ከሌሎች ወጭዎች ባሻገር አመኔታ እንዳያገኙ እያደረገ ነው፡፡ ምርጫ ኖረም አልኖረም አርሶ አደሩን ጨምሮ ህዝብን አባሉ ማድረግ የሚጥረው ገዥው ፓርቲ ሰፊ እድል እንዲፈጠርለት አድርጓል፡፡

ምርጫ ከስልጣን ሽግግር በተጨማሪ ፓርቲዎች ህዝብን የሚያስተምሩበት መድረክ ነው፡፡ በዚህ መድረክ አንድ ግለሰብ በድምጹ መሪውን እንደሚመርጥና እንደሚያወርድ የሚማርበትና የሚያሳይበት መድረክ ነው፡፡ ይህ ሰላማዊ መድረክ አዋጭ መሆኑን በማስተማርም ተቃዋሚዎች ቀዳሚ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ ይሁንና ከምርጫው አስቀድሞ ለምርጫው የሚሆን አቅም በመገንባት፣ ህዝብን በማስተማርና ገዥው ፓርቲ ላይ ጫና ለማሳረት የሚያስችል ስራ ሲሰሩ አይታይም፡፡

በአገራችን ምርጫ ታሪክ በጉልህ የሚነሳው ምርጫ 97 ተቃዋሚዎች አብዛኛውን እንቅስቃሴ ያደረጉት ምርጫው በተቃረበበት ወቅት ነው፡፡ በወቅቱ ተቃዋሚዎች ህዝብን በአጭር ጊዜ ማንቀሳቀስም ሆነ በስርዓቱ ላይ ጫና መፍጠር ቢችሉም ከምርጫው በኋላ የተከተለውን እሰጣ ገባ በሚገባ ሳይወጡት ቀርተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በምርጫ ሊመጣ ይችል የነበረውን ሰላማዊ የስልጣን ሽግግርም ብቻ ሳይሆን ምርጫ እንደ ምርጫ ተስፋ እንዳይጣልበት ጠባሳ ጥሎ አልፏል፡፡ የ2002 ምርጫ ክስተት ደግሞ ምርጫ የአምባገነኖች መጠቀሚያ እንጅ ለውጥ ሊያመጣ እንደማይችል እንዲታሰብ አድርጎታል፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርጫ አሸንፈው ስልጣን ከመያዝ በፊት ፍትሃዊ ምርጫ የሚካሄድበትን መደላድል እንዲፈጠርም በገዥው ፓርቲ ላይ ጫና ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ምርጫ ሲደርስ ከሚያደርጉት በተቃራኒ በእቅድና በስልት የሚመሩ ከሆኑ ብቻ ነው፡፡ ተቃዋሚዎች የራሳቸውን የቤት ስራ ሰርተው ገዥው ፓርቲ ፍትሃዊ ምርጫ እንዳይኖር የሚያደናቅድ ከሆነ ወደ ምርጫው ባለመግባትም ሆነ ሌሎች አማራጭ የሰላማዊ ትግል ስልቶችን በመጠቀም ጫና ማሳደር የሚችሉት ከአሁኑ ለምርጫ የሚያበቃ ስራ መስራት ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ የምርጫ ሰሞን ግርግ ብቻ ኢህአዴግን ከማጀብና ህዝብ ምርጫ ለውጥ እንደማያመጣ እንዲያምንና ተስፋ እንዲያጣ ከማድረግ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ በመሆኑም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ካለፉት ስህተቶች ተምረው ከአሁኑ ለምርጫው ትኩረት በመስጠት ለምርጫ የሚያበቃ ከምርጫ በኋላ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ቁመና ሊገነቡ እንደሚገባ ነገረ ኢትዮጵያ ማሳሰብ ትፈልጋለች፡፡

እንዲህም ተብሏል

«ብዕር የህዝብ ዕጽዋት አትክልተኛ ነው፡፡ ጠመንጃ ደግሞ የዕጽዋት አራጅ ነው፡፡ አንዱ በትጋት የተከለውን ታዳጊ ተክል ሌላው በፋሽስታዊ ድንፋታ ይጨፈጭፋል፡፡»

ጸጋዬ ገ/መድህን፣ ደራሲ

«የጦርነትን ታሪክ የሚያነብ ሰው በጦርነት ላይ እንዳረጀ የጦር ሰው የጦርነትን ባህል ባሳቡ ያውቃል፡፡»

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ የታሪክ ጸሐፊ

«ሽብርተኝነትን ለማቀጨጭና ሰላምን ለማስፈን መሰረቱ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን ማረጋገጥ ነው፡፡»

ቤናዝር ቡቶ፣ ፓኪስታናዊት ፖለቲከኛ

አንደኛ ዓመት ቅጽ 1. ቁጥር 6

ነገረ-ኢትዮጵያ ጋዜጣ ጥር 2006 ዓ.ም ተመሰረተች፡፡ ነገረ-ኢትዮጵያ በሰማያዊ ፓርቲ አሳታሚነት የምትታተም ፖለቲካዊ፣ ወቅታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የምትዳስስ በየሳምንቱ አርብ የምትወጣ ጋዜጣ ናት፡፡

ጋዜጣዋ ሚዛናዊና ነጻ ሆና የማገልገል መርህ አላት፤ ማንኛውም ሀሳብ በነጻነት የሚስተናገድባትና የሚንሸራሸርባት እንድትሆን እንፈልጋለን፡፡ ገዥው ፓርቲም ቢሆን አቋሙንና ፖሊሲውን ለመግለጽ ቢፈልግ የሰፊ ሚዲያ ባለቤት ነው ብለን ዕድሉን አንነፍገውም፤ በራችን ለሁሉም ክፍት ነው፡፡

የአሳታሚ አድራሻ:- የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 09/10
ቤት ቁ.460
E-mail:- info@semayawiparty.org
P.O.Box: 180298

ዋና አዘጋጅ
ጌታቸው ሺፈራው
የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02
ቤት ቁ. 07/859/14
E-mail:-getcholink@gmail.com
ስልክ ቁጥር:- 09-10-45-99-32

ምክትል ዋና አዘጋጅ
በላይ ማናዬ
የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02
ቤት ቁ.099
E-mail:- belaymb@gmail.com
ስልክ ቁጥር:-09-20-19-09-72

አምደኞች
ፕ/ር አለማየሁ ገ/ማርያም
ታዴዎስ ታንቱ
ታምራት ታረቀኝ
አፈወርቅ በደዊ
እያስፔድ ተስፋዬ

ሕትመትና ክትትል
ሳሙኤል አበበ
0913 98 46 40

አታሚ፡ ኪሃራኢ ህትመትና ማስታወቂያ
0921881755

በዚህ ጋዜጣ ላይ የሚወጡ ማንኛውም ዕሁፎች ማተሚያ ቤቱን አይመለከቱም

የመምህራን ፍዳ

በላይ ማናዬ

‹‹እኔ ጆርጅ ቡሽን (ፕሬዚዳንት) አላደንቅም፤ ጠፈር ላይ የወጡትንም አላደንቅም፡፡ የማደንቀው እነዚህን ሰዎች ለትልቅ ደረጃ ያደረሷቸው መምህራንን ነው፡፡››

መምህራን የሀገር ምሰሶዎች... መምህርነት የሙያዎች አባት... መምህር የእውቀት ብርሃን...ይህ እውነት ነው፡፡ እውነቱ ግን ዛሬ ላይ ተጋርዷል፡፡ መምህርነትም ሆነ መምህራን የነበራቸው ክብር ዛሬ ላይ በኢትዮጵያ መሬት በአስደንጋጭ ፍጥነት እየወረደ ይገኛል፡፡ መምህራን በሙያቸው እያፈሩ ነው፡፡ እውቀታቸውን እየሰሱ ነው፡፡ አዎ፣ መምህራን ጫንቃቸው ጎብጦ ነገን በደበዘዘ ተስፋ የሚጠባበቁ ‹ምስኪኖች› እየሆኑ ነው፡፡ ግን እንዴት?

ካድሬነት Vs መምህርነት

ወጣት ነው፤ ገና ለስራው ዓለም ብዙ አበርክቶት የሚጠበቅበት፡፡ ወጣቱ በአዲስ አበባ አብዮት ቅርስ መሰናዶ ት/ቤ የኬሚስትሪ መምህር ነው፡፡ በስራው ዓለም ለአራት ዓመታት ያህል ቆይቷል፡፡ በእነዚህ ዓመታት ግን የሚሸተው ሙያዊ ተግባሩን ለመወጣት ከብዶታል፡ ፡ መምህርነቱን የሚፈታተኑ በርካታ ጉዳዮች እየተፈራረቁበት ተቸግሯል፡ ፡ ወጣቱ ትዳር መሥርቶ፣ ወልዶና ከብዶ መኖር ቀርቶ ጥሩ ጫማና ልብስ ገዝቶና ጥሩ ምግብ ተመግቦ ለመኖር እንኳ እንዳቃተው ይናገራል፡ ፡ ከተማሪዎቹ በታች እየሆነ የሚታይበትን የኑሮ ጫና መቋቋም እንደተሳነውም ይገልጻል፡፡ በዚህ ሁኔታም ሆኖ ማስተማር ይፈልግ ነበር፡፡ ዳሩ ግን መምህርነቱ ከዚህም በላይ ፈተና አሳይቶታል፡፡ ነጻነቱን ነፍጎታል፡፡

የፖለቲካ ሰዎች (ካድሬዎች) የሚያስተምርበት ድረስ እየሄዱ ተጽዕኖ ያደርጉበታል፡፡ ት/ቤቶች የእውቀት ማበልፀጊያና መጋሪያ ደጆች ቢሆኑም አሁን አሁን ስልጣን ፈላጊዎች መናሃሪያ አድርገዋቸዋል፤ የፖለቲካ ማዕከላት ሆነዋል፡፡

ወጣቱ መምህር ይናገራል፤ ‹‹...የኢህአዴግ ካድሬ ካልሆንክ ችግር ነው፡፡ ካድሬነት ወደህ የምትገባበት ሳይሆን ካድሬ ባለመሆንህ ከሚደርስብህ አድሎአዊ አሰራር ለማምለጥ ብለህ የምትገባበት ሲኦል ሆኗል፡፡ መምህርነት መሰረቱ እውቀት ነው፡፡ አሁን ግን ያ አይደለም መሰረቱ፤ ካድሬነት ነው፡፡ በእውቀት ላይ ብቻ ተመስርቼ አስተምራለሁ ካልክ በድህነት እያክክ ትኖራታለህ፡፡ አንድ ተራ ካድሬ ከአንተ በላይ ገንዘብ ይከፈለዋል፡፡ እናም ብታምንበትም ባታምንበትም ካድሬ ሆነህ ወደ ቀበሌ ከተሾምክ ደመወዝህ 4000 ብር ይደርሳል፡፡ መምህርነት ላይ ከቆየህ ግን ይህን ደመወዝ በ20 ዓመት እንኳ አትደርስበትም፡፡››

እንደ ወጣቱ ገለጻ መምህራን ሙያቸውን አሻሽለው ነገን በተስፋ ለማለም አልታደሉም፡፡ በሙያቸው ክብርን አያገኙም፡፡ ወርን ጠብቃ ከምትመጣ መናኛ ደመወዝ በቀር ሌላ ማበረታቻ ጥቅማጥቅሞች የላቸውም፡ ፡ በእርንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ደግሞ መምህራን ከተማሪዎቻቸው ሳይቀር የሚደርስባቸው ንቀትና ማንንጠጥ እየጨመረ ይገኛል፡ ፡ ‹‹የሚገርምህ አንዳንድ ተማሪዎች ከመምህራን በላይ ስልጣን አላቸው፡፡ ያገዘሁላል ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ካድሬ ተማሪዎች በዝተዋል፤ የተማሪ ደህንነቶችም አሉ፡፡ ስለምታስተምረው ነገር ነጻነት የለህም፡፡ ይህ መምህራንና ተማሪዎች እርስ በእርስ እንዳይግባቡ እየተገነባ ያለ የበርሊን ግንብ ነው፡፡

‹‹ተማሪ መምህሩን እየደበደበ እንዴት ማስተማር ትችላለህ...ለምሳሌ በቅርብ ጊዜ በተማሪ ድብደባ የደረሰበት አንድ መምህር ኮማ ውስጥ ይገኛል፡ ፡ የተማሪ ወላጆችም እኛ መምህራንን እንደ ተላላኪ ነው የሚያዩን፡፡ ምን ታደርጋለህ...አንዱ ልጅ አንዱ የእንጀራ ልጅ የሆነበት ስርዓት ለዚህ አበቃን፡፡ እንደ ባለሙያ ሳይሆን እንደ ሎሌ ነው እየታየን ያለነው፡፡››

ሌላው ያነጋገርኩት መምህር በእንጦጦ አንባ ት/ቤት ታሪክ ያስተምራል፡፡ መምህሩ ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን የባልደረባውን አባባል ይጋራል፡፡ ት/ቤቶች የፖለቲካ ማዕከላት እየሆኑ መምጣታቸውንም ይጠቅሳል፡፡ ‹‹...የኢህአዴግ መሰረታዊ ድርጅት የሚባሉ የአደረጃጀት አባላት ት/ቤት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ስብሰባ የሚያደርጉት ት/ቤት ውስጥ ነው፡፡ ለድርጅት ስብሰባ ተብሎ የትምህርት ጊዜ ይባክናል፤ የት/ቤት ንብረት ለፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ይውላል፡ ፡ የተማሪ አደረጃጀት የሚባል ነገርም አለ፡፡ በትምህርት ሽፋን የፖለቲካ ስራ የሚሰሩባቸው ናቸው፡፡››

እንደ መምህሩ አባባል፣ መምህራን ሁለት ሚዛን ላይ ሆነው ነው የሚመዘኑት፡፡ የኢህአዴግ አባል የሆኑት በአንድ ወገን፣ አባል ያልሆኑት በሌላ ወገን፡፡ በዚህም አባል ያልሆኑ መምህራን ከሌላው የበለጠ አስተዳደራዊ በደል ይደርስባቸዋል፡ ፡ በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ እየተለኩ ጫና ይደረግባቸዋል፡፡ ‹‹አንድ ለአምስት የሚባል አደረጃጀት አለ፡፡ መምህራንን በአመለካከታቸው ልዩነት ‹ታርጌት› ይደረጉበታል፡፡ ይህ አንድ ለአምስት የሚባለው አደረጃጀት የፖለቲካ ስራውን ለመከወን የተዘየደ መረብ ነው፡፡ አንዱ አንዱን እየሰለለ እርስ በእርሱ መተማመንን እንዳያጎለብት ነው እንዲህ የተደረገው፡ ፡ በእውነት ት/ቤቶች ዋና የፖለቲካ ማዕከላት እንደሆኑ ደግሜ ደጋግሜ ልነግርህ እችላለሁ፡፡››

የደመወዝ ማነስ፣ መገለልና ንቀት

ደመወዝና መምህራን አልተገናኙም፡፡ ጭማሪ ተደረገላቸው ሲባልም የይስሙላህ ይሆናል፡፡ ለአብነትም 2004 ዓ.ም ላይ መንግስት ለመምህራን የደመወዝ ጭማሪ አደረኩ ብሎ የጨመረውን መጠን ማስታወስ ይቻላል፡፡ የዛኔው የደመወዝ ጭማሪ የመምህራንን ሕይወት የሚለውጥና የሚያሻሽል ሳይሆን ክብረ ነክ እንደነበር ይታወሳል፡፡ እናም የተደረገው ጭማሪ ለመምህራን የማይመጥን እንደነበር በመግለጽ ተቃውሟቸውን ያሰሙ መምህራን (በተለይ በአዲስ አበባ) እንደነበሩ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ከመንግስት የተሰጣቸው ምላሽ ግን ህገ-ወጥ ተብለው ከስራ መሰናበት ነበር፡፡

የመምህራኑ ጥያቄ ግን ተገቢነት ነበረው፡፡ የኑሮ ውድነቱ እየጦዘ ባለበት ወቅት የሰባ ሦስት ብር ጭማሪን ከቁምነገር ቆጥሮ ‹ጭማሪ ተደረገላቸው፤ ጭማሪውም ህይወታቸውን ይለውጣል› እያሉ መልፈፍ በመምህራን ሞራል ላይ ክፉኛ መዘባበት ነበር፡፡ መምህራንም ይህን ሐቅ ይዘው የስራ ማቆም አድማ ሳይቀር አድርገው ነበር፤ ሰሚ አላገኙም፡፡

መምህራን አሁንም ዝቅተኛ ተከፋዮች እንደሆኑ ነው የሚናገሩት፡ ፡ አንድ መምህር በሶስት ዓመት

ወደ ገፅ 6 ይዞራል

ኢህአዴግ እንደ ናቡከደነፆር

ወይንሸት ንጉሴ

በአንድ ወቅት የዓለም ገናና ንጉስ የነበረው የባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር ለ43 ዓመታት ባቢሎንን ገዝቷል፤ በስተሰሜን ሶሪያ በምዕራብ በፍልስጤም እስከ ግብፅ ግዛቱን አስፋፍቷል፡፡ ይህ ንጉስ ህጎችን ከመቀዕበት ይደነግጋል፣ ይለውጣል፡፡ ለእሱ ስርዓት ተገዥ ያልሆኑትን ያስራል፣ ይገርፋል፡፡ ንጉስ ናቡከድነፆር በጣም የሚፈራ እና ኃይለኛ ንጉስ ቢሆንም ከመውደቅ ግን አልዳነም፡፡ ለማንኛውም የዚህ ንጉስ ታሪክና የሀገራችን መንግስት ስርዓት ብዙ የሚያመሳስላቸው ነገሮች ስላሉ እንዲህ አቅርቤዋለሁ፡፡

ንጉስ ናቡከድነፆር በዘመኑ በጣም የሚፈራ እና የማይደፈር እንደመሆኑ መጠን የፈለገውን የማድረግ መብት ነበረው፡፡ በዚህም መሰረት ነው የሌለባቸውንና መልክ መልከኞችን ጥበብና ዕውቀት የሞላባቸውን በብልሀት ዳኞችንና አስተዋዮች የሆኑትን በንጉሱም ቤት መቆም የሚችሉ ብላቴናዎችን በእስራኤል ልጆች ከነገስታቱ እና ከመሳፍንቱ ዘር ይመጣ ዘንድ ለጃንደራቦቹ አለቃ ለአስፋኔዝ ነገድ ዳንኤል 1,3,4፤ የተመረጡትም ወጣቶች ዳንኤል፣ አናንያ፣ ሚሳኤልና አዛርያ ነበሩ፡፡ በእርግጥም እነዚህ ወጣቶች ጤናማ አዕምሮና አካል እንዲሁም ጥልቅ ማስተዋል ጥበብና ዕውቀት ነበራቸው::

ንጉስ ናቡከደነፆር እነዚህን ወጣቶች ከባቢሎናውያን ስርዓት ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ ንጉስ የከላዳውያንንም ትምህርት ቋንቋ ያስተምራቸው ዘንድ ጃንደረቦቹን አዘዘ፡ ፡ ንጉሱም በእርሱ ዘንድ እንዲቆሙ ስለሚፈልግ ከንጉስ መጠጥና መብል በየዕለቱ እንዲወስድላቸው አዘዘ፡፡ ስማቸውንም ቀየረ፡፡ ንጉስ የእነዚህን ወጣቶች ስም የቀየረው በራሱ መስመር ለሱ እንዲስማማው እና የእሱ ተገዥ እንዲሆኑ ለማሳወቅ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ስማቸውንም ቢቀይረው የዓላማ ፅናታቸውን ግን መቀየር አልቻለም ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ናቡከደነፆር የግዛቱን አንድነት ለማጠናከር በማሰብ በዱር ሜዳ አንድ የወርቅ ምስል አቆመ፡፡ የምስሉ ርዝመት 60 ክንድ (27 ሜትር) ወርዱ 6 ክንድ (2.7 ሜትር) ነበር፡፡ ንጉስ በዚሁ ምስል የምረቃ ሰነ ስርዓት አዘጋጅቶ መሳፍንቱንና ሽማምንቶቹን፣ አገር ገዥዎቹን፣ አማካሪዎቹን፣ የህግ አዋቂዎችን ሰብስቦ ላሰራው የወርቅ ምስል የእምቢልታና የዘፈን ድምፅ በሰሙ ጊዜ ተደፍተው እንዲሰግዱ፣ ካልሰገዱ ደግሞ በሚነደው የእቶን እሳት ውስጥ እንደሚጣሉ ተነገራቸው፡ ፡ ሙዚቃው መሰማት ሲጀምር ያ ሁሉ ባለስልጣን ተደፍቶ ሲሰግድ እነዚያ አስተዋይና ጥበበኞች ወጣቶች ግን ቀጥ ብለው ቆሙ፤ የወጣቶችን አለመስገድ ያዩ የንጉሱ ታማኞች ንጉሱ ዘንድ ሄደው ወጣቶቹን ታማኝነት በማጉደልና ሀገርን በመክዳት ወንጀል እንዲያቃጥላቸ ጠየቁ፤ ንጉሱም ላሰራው ምስል እንዲሰግዱ፣ እምቢ ካሉ ግን እቶን እሳት ውስጥ እንደሚጥሏቸው ቢያስጠነቅቃቸውም አንሰግድም ብለው ከአቋማቸው ሳይነቃነቁ ቀሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ይህ አምባገነን የነበረ ንጉስ የፈቀደውን የሚገድል፣ የሚያስር፣ የሚመታ እና የሚያዋርድ እንዲሁም ለእሱ ተገዥ የሆኑትን ደግሞ ከፍከፍ የሚያደርግ ነበርና እነዚህን ሶስት ወጣቶች ከዚያ ከሚቀለቀል እቶን እሳት ውስጥ ከተቷቸው፡፡

ኢህአዴግ እንደ ናቡከደነፆር

በአሁኑ ሰዓት ኢህአዴግ እየሰራ ያለው ይህንኑ የንጉስ የናቡከደነፆር አይነት ስራ ነው፡፡ በፈለገው ሰዓትና ቀን ህገ መንግስቱን ይሽራል፣ ይለውጣል፡ ፡ ማሰር መምታትና መግደል ካሰኘው ያደርገዋል፡፡ እሱ በሚጠራው ሰልፍና ስብሰባ ላይ በግዳጅ እያስወጣ ፓርቲው ህብረትና አንድነት እንዲሁም ሙሉ ኃይል ያለው ያስመስላል፡፡ በትምህርት ውጤታቸው የላቁ ልጆችን በየትምህርት ቤቱ እየዞረ አባል እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ የ‹‹ኢህአዴግዝም››ንም እምነት ይከተሉ ዘንድ በወጣት ሊግና ፎርም አደረጃጀት ይጠይቋቸዋል፡፡ ከዚያም በየስብሰባው ሚሪንዳና ቦንቦሊኖ እያደለ በብሔር ብሔረሰቦች ዘፈን እያስጨፈረ ስለ ደርግ ጭፍጨፋነት እና ስለ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጭራቅነት እየሰበካቸው እሱን እሱን ብቻ እንዲያመልኩ ያደርጋቸዋል፡፡ ለዚሁ የኢህአዴግዝም እምነት ጠንካራ አምላኪ ከሆንክ ደግሞ ያለ ውድድር ስራ መግባቱ፣ ሹመትና እድገቱ፣ ቤትና መኪናው፣ 10ኛ ክፍልን ሳትጨርስ አመራር ቦታ ላይ መቆሙ፣ በቃ ምን አለፋህ... ሁሉ በእጅህ ነው፡፡

ኢህአዴግ ከድሮው ንጉስ ናቡከደነፆር የሚለየው ሳይሰራ ሊያሰግድ የሚጥር ግትር መሆኑ ነው፡፡ ማሰገዱ በጎ ባይሆንም የድሮው ንጉስ ያሰግድ የነበረው ለህዝብ የሚታይ ነገርን ሰርቶ ነበር፡፡ ኢህአዴግ ግን እንዲሰገድለት የሚፈልገው በማይታየው፣ በሌለውና ባልተሰራው ስራው ነው፡፡ በአጭሩ ያላዩት እንዲያምኑት የሚፈልግ የዘመኑ ነብይ ለመሆን ይሞክራል፡ ፡ ትራንስፎርሜሽን፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ልማታዊ መንግስትና ሌሎችም.... የሚጨበጡ የሚያዙ አይደሉም፡፡ እነዚህ የማይጨበጡ ነገሮችን ግን ከምንም በላይ አጋንኖ ያቀርባቸዋል፡፡ በእነዚህ ስራዎች፣ ለእነዚህ ‹‹መሃንዲስ›› ለተባሉት ካድሬና መሪዎቹ እንድንሰግድለት ይጠብቃል፡፡

በአጠቃላይ ልክ በድሮ ዘመን የነበረው ናቡከደነፆር ያደርግ እንደነበረው ለኢህአዴግና ለመሪዎቹ ለሰገደ ሁሉ ከሚገባው በላይ ከአገርና ከህዝብ ጥቅም ይሰጠዋል፡፡ ይዘርፋል ማለት ይቀላል፡፡ ኢህአዴግ ሳይቀር ያወጣውን ህግ ጠቅሶ ‹‹መብቴ ነው!›› እያለ፣ ለመስገድ አሻፈረኝ ያለ ግን እንደ ሶስቱ ወጣቶች የዘመኑን የእሳት ነበልባል ይቀምሳል፡፡ ወደ እስር ቤት ይወረወራል፡፡ ይደበደባል፡፡ ከስራ ይባረራል፡፡

ነገር ግን አንተ እውነተኛው የኢትዮጵያ ልጅ ከራስህ ጥቅም ይልቅ የሀገርህን ጥቅም የምታስቀድም ከሆነ እና ከምግብ ይልቅ ነፃነት፣ ከብሔር ይልቅ ኢትዮጵያዊነትን፣ ከውሸት ይልቅ እውነትን መርጠህ ይህን መንግስት ከተቃወምክ ወይም ከተቸህ የኢህአዴግ አምላኪዎች በገባህበት እየገቡ ዛቻና ማስፈራሪያ፣ ስድብና ዱላ መለያህ ያደርጉልሀል፡፡ ይህ ነገር ግን አቋምህን ሊያስቀይረው አለመቻሉን ሲያውቁ ደግሞ ደስ የምትል ውሸት አቀናብረው ፊልም ይሰሩ እና አሸባሪ፣ ከዳተኛ፣ የሀገር ጠላት ብለው ንጉስ ናቡከደነፆር እሳት ውስጥ እንደከተታቸው ሶስቱ ወጣቶች ሁሉ ኢህአዴግም ይወረውርሃል፡፡ ከደበርከውም ያስወግድሃል፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግ ዛሬም አናንያ፣ አዛርያ እና ሚሳኤልን የመሳሰሉ ወጣቶች እንዳሉ ያወቀ አልመሰለኝም፡፡

በእርግጥ ከ97ቱ ምርጫ በኋላ ወጣቱ ሀገራዊ ጉዳይ አያገባኝም ብሎ እርፍ ብሎ ቢታየውም ዛሬ ደግሞ እንደ አዲስ መታሰርም መደብደብም ሆነ መሞት የማይፈሩ፣ ባመኑበት እንጂ ለማያምኑበት ነገር የማይገዙና የማይንበረከኩ፣ ጥቅማ ጥቅም የማያታልላቸው፣ ለመብታቸው የሚታገሉ ለሀገራቸው ክብር የሚቆረቆሩ እና ከራሳቸው ጥቅም ይልቅ የሀገራቸውን ጥቅም የሚያስቀድሙ ወጣቶች ማቆጥቆጥ ጀምረዋል፤ በቅለዋል፡፡ እናም ኢህአዴግ ሆይ! እንደ ንጉስ ናቡከደነፆር ከመሆንህ በፊት መንገድህን አስተካክል!

የሽብርተኝነት እንቆቅልሽ

❖ የኢትዮጵያው አዋጅ ትርጓሜና ክፍተቶቹ

ጌታቸው ሺፈራው

መንግስታት በተለያየ መልኩ ትርጉመው ያቀረቡትን ሽብርተኝነት ለመዋጋት በሚል ህግ ያወጣሉ፡፡ በእርግጥ በአዲስ መልክ በሽብር ላይ የታወጀው ዘመቻ በአሜሪካ ግፊት የመጣ ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ2001 አሜሪካ ከደረሰባት የሽብር ጥቃት በኋላ ‹‹war on terror›› እንዲሁም ‹‹counter terrorism›› የተሰኙ ዘመቻዎችን ነድፋ ተንቀሳቅሳለች፡፡ አሜሪካ ወዳጅም ሆነ የቀዩ ባላንጣዎቿን ሳይቀር ደልላም ሆነ ተማጽና የጀመረችው ይህ ‹‹ጸረ ሽብር ዘመቻ›› መንግስታት በየ አገራቸው የራሳቸውን ጥቅም የሚያስጠብቁ አፋኝ ‹‹የጸረ ሽብር›› ዘመቻ እንዲያወጡ እድል ሰጣቸው፡፡ አሜሪካ የሰብአዊ መብት ይጥሳሉ እያለች ስትወቅሳቸው የነበሩ ስርዓቶች ሳይቀሩ የተደላደለ የዴሞክራሲያዊ መሰረት ባልተጣለበት ሁኔታ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን የሚደፈጥጡ አዋጆች አጽድቀው ሲተገብሩ ከሀያሏ አገር የገጠማቸው ወቀሳና ግፊት ከዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ በተቃራኒው አልቃይዳንና ቅርንጫፎቹ አሊያም ተያያዥ አሸባሪና አክራሪ የምትላቸውን ሁሉ እንዲያድኑ ወታደራዊ ድጋፍን አጋብሰዋል፡፡ ኢህአዴግ መራሹ የኢትዮጵያ መንግስት ከኒዮርኩ ጥቃት በኋላ አጋጣሚውን ከተጠቀሙት መንግስታት መካከል አንዱ ነው፡፡

አሜሪካ መራሹ ከሆነው በተጨማሪ በተለይም የምዕራባዊያን አገራት የደረሰባቸውን አደጋም አስከትለው ህጎችን አውጥተው ተግብረዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ጸረ ሽብር ህጎች መንግስታት ራሳቸው ያጸደቋቸውን ህጎች ሳይቀር ጥሰው ሽብርተኝነት ያሉንት ወንጀል እንከላከላለን የሚልባቸው ህግጋቶች ናቸው፡፡ በተለይ ዴሞክራሲ ባልተጠናከረባቸው አገራት እነዚህ ህጎች አምባገነኖች በአገራቸው ህዝብ ላይ ያሹትን እንዲፈጽሙ እና ህጉን ተገን አድርገው ለረዥም ጊዜ ስልጣን ላይ እንዲቆዩ ምክንያት እየሆነላቸው ይገኛል፡፡

የአዋጁ

አውድ

በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ የሚገኙት የተለያዩ የሽብር ትርጉሞች የሚተረጎሙት በዝርዝር ተግባራት (ግድያ፣ ጠለፍ፣ እገታ፣ በመሳሰሉት ድርጊቶችና) እና ከተፈጸሙት ድርጊቶች በስተጀርባ አሉ የሚባሉት (አብዛኛዎቹ መንግስታት ራሳቸው ከጥቅማቸው አንጻር የሚተረጉሟቸው ናቸው) በዓላማና ፍላጎትን በማጣመር ነው፡፡ የኢትዮጵያ የጸረ ሽብር አዋጅ ትርጓሜም ይህንኑ መንገድ የተከተለ ነው፡፡ አዋጅ 652/2001 በድርጊት በኩል ሽብርተኝነትን ሲተረጉም፡-

1. ሰውን የገደለ ወይንም በአካሉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ

2. የህብረተሰቡን ወይንም የህብረተሰቡን ክፍል ደህንነት ወይንም ጤና ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ እንደሆነ

3. እገታ ወይንም ጠለፋ የፈጸመ እንደሆነ

4. በንብረት ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ

5. በተፈጥሮ ሀብት፣ በአካባቢ፣ በታሪካዊ ወይንም የባህል ቅርስ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ

6. ማንኛውንም የህዝብ አገልግሎት ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ስር ያደረገ፣ ያቋረጠ ወይንም ያበላሸ እንደሆነ ወይንም

7. ከላይ የተጠቀሱትን ለመፈጸም የዛተ እንደሆነ በሽብርተኝነት እንደሚወነጀል ይገልጻል፡፡ ለጥፋቱም ከ15 አመት ጀምሮ የእድሜ ልክ ብሎም የሞት ቅጣት እንደሚያስወስንበት አስቀምጧል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት መካከል አብዛኛዎቹ ዝርዝሮች ህጉ ተወሰደባቸው ከሚባሉት የዴሞክራሲያዊ አገራት ጸረ ሽብር ህግ ያልተካተቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል ‹‹ማንኛውንም የህዝብ አገልግሎት ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ስር ያደረገ፣ ያቋረጠ ወይንም ያበላሸ›› የሚለው በሰላማዊ እምብይተኝነት ጊዜ የሚፈጸምና በሌሎች አገራት ሽብርተኝነት ቀርቶ ተራ ወንጀል ስምም አያስከስስም፡፡

ዝርዝሮቹ በቂ ባለመሆናቸው ትርጉሙን ለማጠናከር ዓላማና ፍላጎት የግድ መጨመር ነበረበት፡፡ በመሆኑም አዋጁ ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት ሽብርተኝነት ሊፈርጅ የሚችለው ‹‹ማንኛውም ሰው ወይንም ቡድን የፖለቲካ፣ የሀይማኖት ወይንም የአይዲዮሎጂዊ አላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግስት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር፣ ህብረተሰብን ወይንም የህብረተሰብን ክፍል ለማስፈራራት ወይንም የአገሪቱን የፖለቲካዊ፣ ህገ-መንግስታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይንም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት ወይንም ለማፍረስ›› የሚል አላማና ፍላጎት ይጨምርበታል፡፡ ይህ የሽብር ትርጉሙን ከተራ ወንጀልነት ወደ ሽብርተኝነት የሚቀይረው አብይ ክፍል ሲሆን መንግስታትም በዋነኛ ካርድነት ይጠቀሙበታል፡፡ በተለይ በአገራችን የተደላደለ ፖለቲካዊ ስርዓት ባለመፈጠሩ ምክንያት አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች ፖለቲካዊ መሆናቸው አልቀረም፡፡ ከዚህም ባሻገር መንግስትን የተቆጣጠረው ፓርቲ ጥቃቅን ጉዳዮቹን ወደ ‹‹ሽብርተኝነት›› ለመቀየር የሚያስፈልጉ ዓላማዎች ጋር በማገናኘት የሰላማዊ ትግሉን እያንዳንዱ እንቅስቃሴዎች ‹‹በሽብር›› ስም እየፈረጃቸው ይገኛል፡፡

ኢቲቪ ታህሳስ 19 ባስተላለፈው ዶክመንተሪ አቶ መለስ ዜናዊ ስለ አዋጁ ዴሞክራሲያውነት ሲናገሩ አሳይቷል፡፡ አቶ መለስ አዋጁን በቀጥታ ከአውሮፓ ህብረት፣ ከእንግሊዝና ከአሜሪካ ቃል በቃል የወሰዱት ቃል ቢቀይሩ ይተቹናል በማለት እንደሆነ ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ አቶ መለስ አዋጁ ከእነዚህ አገራት ቃል በቃል ስለተቃዳ ብቻ ምንም እንከን የማይወጣለት ብለውታል፡፡ ይህን የአቶ መለስ ንግግር የተጠቀሙበት አሁንም የኢህአዴግ አቋም (ማሳመኛ) ቢሆን ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከአሜሪካ፣ ከአውሮፓ ህብረትና ከእንግሊዝ የተለየ የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረት ያላት አገር እንደመሆኗ ለራሷ ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ህግ እንደሚያስፈልጋት ጥርጥር የለውም፡፡ ኢህአዴግ በውል የማይተረጉማቸው ‹‹አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ልማታዊ መንግስት›› ከአውሮፓ ህብረት፣አሜሪካና እንግሊዝ ኒዮ ሌብራሊዝም ይልቅ ከአገራችን (ከአፍሪካ) ነባራዊ ሁኔታ ተጣጥሞ የተቀረጸ መሆኑን ሲናገሩ ኖረዋል፡፡ የአውሮፓውያን ፖሊሲ ለአውሮፓውያን እንጅ ከአውሮፓ የተለየ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መሰረት ላላቸው አፍሪካውያን እንደማይጠቅም ‹‹AFRICAN DEVELOPMENT: DEAD ENDS AND NEW BEGINNINGS›› በሚለው ጽሁፋቸው ሊያስረዱ ሞክረዋል፡፡ ገና በመግቢያውም ‹‹የእኔ መከራከሪያ ኒዮ ሌብራሊዝም ያለቀለትና በአፍሪካ ህዳሴ ሊያመጣ የማይችል በመሆኑ የአፍሪካን ህዳሴ ለማምጣት ሌላ ስርዓት ያስፈልጋል የሚል ነው›› ይላሉ፡፡ ታዲያ ኢትዮጵያም ሆነች አፍሪካ ከምዕራባዊያን የተለዩ በመሆናቸው ከአውሮፓውያኑ የተለየ ስርዓት ካስፈለጋቸው የጸረ ሽብር ህጉንስ ለምን በቀጥታ መገልበጥ አስፈለገ? ዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብት፣ የግለሰብ ነጻነት፣ የመሬት ህግ፣ ኢኮኖሚውን ለግል ባለሃብት የማስተላለፍ ለምን እንደ ጸረ ሽብር ህጉ አቶ መለስ ስለጠኑ ከሚሏቸው ምዕራባዊያን በቀጥታ አልተገለበጡም? የሚሉት ጥያቄዎች ሊያስረዱ የሚችሉት የጸረ ሽብር ህጉ በመልካም ተሞክሮነት ተገልብጦ መጠቀሚያ መሆኑን ብቻ ነው፡፡

ኢህአዴግ

ያመነው ስህተት

ይህ ጸረ ሽብር አዋጅ የተለያዩ ክፍተቶች እንዳሉበት እየተተቸ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል ቀዳሚው ከህጋዊ ይልቅ ፖለቲካዊ ትርጉሙ ማመዘኑ ነው፡፡ አንድነት የጸረ ሽብር አዋጁን ለማሰረዝ ለሶስት ወር ባደረገው የድምጽ ማሰባሰብ ሂደት የተደናገጠው ኢህአዴግ ከወራት በፊት በአዋጁ ላይ ከተቃዋሚዎች ጋር ክርክር ማድረጉ ይታወሳል፡፡ በክርክሩ ወቅት ተቃዋሚዎችና ገዥው ፓርቲ የተስማሙበት ብቸኛው ነጥብ ቢኖር አዋጁ ከህጋዊ ይልቅ የፖለቲካ ትርጓሜ የተሰጠው መሆኑን ነው፡፡ ተቃዋሚዎች በህገ-መንግስቱ መሰረት ህግ ሊተረጎም የሚገባው በህግ አካላት እንጅ ፖለቲካዊ ሚናን በሚጫዎተው እንዲያውም የአንድ ፓርቲ አባላት በሞሉት ፓርላማ አይደለም በሚል ተከራክረዋል፡፡ በአንጻሩ ኢህአዴግ ሽብርተኝነት ከሌሎች ወንጀሎች ጋር ሊነጻጸር የማይችልና አንገብጋቢ በመሆኑ ፓርላማ ሊያጸድቀው የግድ መሆኑን በመጥቀስ ፖለቲካ ትርጓሜ እንደተሰጠው አምኗል፡፡ በጸረ ሽብር ህጉ መግቢያ ላይም ‹‹በስራ ላይ ያሉት (ህገ መንግስቱን ጨምሮ) የሀገሪቱ ህጎች በበቂ ሁኔታ ሽብርተኝነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ባለመሆናቸው ጠንካራ የህግ አቅም መፍጠር በማስፈለጉ ነው በሚል አዋጁ ከህገ መንግስቱ የተለየ (የጣሰ) መሆኑን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአንደበቱ ተናግሯቶታል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 25(1) ‹‹የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመንግስት አቅራቢነት አንድን ድርጅት በሽብርተኝነት የመሰየም እና የሽብርተኝነቱን ስያሜን የመሻር ስልጣን ይኖረዋል፡፡ ›› ሲልም ‹‹ሽብርተኝነት›› ከትርጉሙ ጀምሮ እስከ አፈጻጸሙ ፖለቲካዊ እንጅ ህጋዊ ማዕቀፍን የተከተለ እንዳልሆነ ያስረግጣል፡፡

ከኢትዮጵያውያን በተቃራኒ በሌሎች አገራት መንግስታት ከተቀናቃኞቻቸው ጋር የሚከራከሩት ህጉ ፖለቲካዊ ትርጉም ተሰጥቶታል አልተሰጠውም በሚለው ጉዳይ ላይ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ፖለቲካዊ ትርጓሜ የተሰጠው ‹‹ህግ›› ከህግነት ይልቅ መጠቀሚያ በመሆኑ ሲሆን ኢህአዴግ ግን የጸረ ሽብር አዋጁ ፖለቲካዊ ትርጉም እንደተሰጠው አምኗል፡፡ በዚህ ረገድ ኢህአዴግ የጸረ ሽብር ህጉን ለራሱ ጥቅም የተጠቀመ መሆኑን ያመነ ብቸኛው ፓርቲ ሳይሆን አይቀርም፡፡ የፖለቲካ ትርጉሙና አተገባበሩም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ህጎችና ህገ-መንግስቱ ህዝብንም ሆነ የአገር ድህንነትን ለመጠበቅ የሚደረግ የትኛውም የመንግስት እርምጃዎች የዜጎችን የመደራጀት፣ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽና ሚስጥራቸውን የመጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸው ቢያስቀምጡም የጸረ ሽብር አዋጁ እነዚህን ጨምሮ አብዛኛዎቹን ዴሞክራሲያዊ መብቶች በፖለቲካዊ አውዱ ጨፍልቋቸዋል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ አዋጁ ህገ መንግስቱን የማይጥስ፣ ህጋዊ ትርጓሜ እንጅ ፖለቲካዊ ትርጓሜ ያልተሰጠው (ለፖለቲካ ጥቀም የማይውል ነው) ሲል ይደመጣል፡፡

የጸረ ሽብር አዋጁ በፖለቲካዊ ትርጉምና አተገባበሩ ሁሉንም ነገር ከብሄራዊ ደህንነት ጋር ማገናኘቱ የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ሽብርተኝነት ዋነኛው የደህንነት ትኩረታቸው በሆኑት አገራት ሳይቀር ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትና ብሄራዊ ደህንነት አብረው እርስ በእርሳቸው በማይጋጨበት አሊያም መጠቀሚያ በማይሆኑበት መንገድ ተግባር ላይ ይውላሉ፡፡ ‹‹ሽብርን›› መዋጋት ለዜጎች ደህንነት ነውና የዜጎችን ነጻነት የሚነፍግ ተግባር ራሱ ሽብር ከመሆን አያልፍም፡፡ አንዳንዴ ለዜጎች ለራሳቸው እንዲሁም ለአገሪቱ ሲባልም ነጻነታቸው ለደህንነት በሚያመች መልኩ ይቃኛል፡፡ በመንግስታት ቅቡልነትና ባህሪ መካከል ያለው ትርጉምና አተገባበር የተለያየ ቢሆንም ሁለቱን በተገቢው

ከሙስሊሞች እንቅስቃሴ በስተጀርባ

ጌታቸው ሺፈራው

ካርል ማርክስ ሐይማኖትን ‹‹የድሃዎች ማደንዘዣይ›› ይለዋል፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ በረሃ በነበረበት ወቅት ሐይማኖትን በተመሳሳይ መልኩ ፈርጆ ቀስቅሶበታል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ከሐይማኖት ይልቅ ማርክሲስት ነን ያሉ ገዥዎች አገራትንና ቀጣይ ትውልዳቸውን አደንዝዘው አልፈዋል፡፡ አሁንም ቢሆን ጥቂት የማይባሉት ይህን ተግባራቸውን ቀጥለዋል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ አሁንም ድረስ ይህ ምልክት በጉልህ እየታየ ነው፡፡ ሐይማኖትን በማደንዘዣይነት ከመፈረጅም በተጨማሪ በሌላ ጎን ለስልጣን እንዲጠቅም አድርጎ መገልገል ከፊል ማርክሲዝምን ለስልጣን እርካብ መወጣጫ ያደረጉ የግራ ዘመም ፓርቲዎች አብይ ባህሪ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ህወሓት/ኢህአዴግ ሐይማኖትንም ሆነ ሐይማኖትን በማደንዘዣይ ጠላትነት የሚፈርጀውን ማርክሲዝንም ደቅሎ ለስልጣን ከሚጠቀሙ ጥቂት ቅሬት ገዥዎች መካከል ቀዳሚው ነው፡፡

የማርክስን አባባል ቃል በቃል ወስዶ

ሲጠቀምበት የቆየው ህወሓት ጎን ለጎን ሐይማኖትንም በመሳሪያነት ተጠቅሞበታል፡፡ ለምሳሌ ያህል ሙስሊሙን ማህበረሰብ የገዥው መደብ ሐይማኖት ነው ብሎ ከሚወቅሰው ኦርቶዶክስ ጋር ለማናከስ ተጠቅሞበታል፡፡ ህወሓት ለሙስሊሞች የቆመ ድርጅት ለማስመሰል ሲባልም አብዛኛዎቹ ታጋዮች የሙስሊም ስም እንዲጠቀሙ መደረጋቸውን በአንድ ወቅት የድርጅቱ ሊቀመንበር የነበሩት ዶክተር አረጋዊ በርሄ በመጽሃፋቸው ገልጸውታል፡፡ ከዚህ ባሻገር ህወሓት/ኢህአዴግ እስልምናን በስፋት ይከተላሉ ያላቸውን ማህበረሰቦች ለመቀስቀስ እምነትን በመሳሪያነት ተጠቅሞበታል፡፡ ለአብነት ያህል የሶማሌ፣ አፋርና ሌሎች ህዝቦችን ለመቀስቀስ አማራና ኦርቶዶክስ ጨቋኝ አድርጎ ሲቀሰቅስ ኖሯል፡፡ ይህ የገዥው ፓርቲ ሐይማኖትን በመሳሪያነት የመጠቀም ስልት ግን ስልጣን ከያዘ ከሁለት ዓመት በኋላ በታሰበው መልኩ ሊጓዝ አልቻለም፡፡ ህገ መንግስቱ ላይ በሰፈረውና ሐይማኖቱም በሚያዘው መሰረት እምነታቸውን ለመከወን የጣሩ ኢትዮጵያውያን ከስርዓቱ መልካም ምላሽ አልገጠማቸውም፡፡ ከ1980ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ መንግስት መብቱን አስከብሬለታለሁ በሚለው ሙስሊምና በሐይማኖቱ በእስልምና ጉዳይ ላይ ጣልቃ ሲገባ መቆየቱ ትልቅ ማሳያ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መብታቸውን ለማስከበር ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል፡፡ ከሁለት አመት በፊት ጀምሮ ደግሞ መንግስት የተለያየ ስም እየሰጠ የሚፈርጀው የሙስሊሙ ሰላማዊ እንቅስቃሴ በመንግስት ላይ ቀላል የማይባል ጫና ማሳደር ችሏል፡፡

ከሁለት አመት በላይ መንግስት በሐይማኖታቸው ጣልቃ እንደገባ በመግለጽ፣ ሲቃወሙ የቆዩት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እንቅስቃሴያቸውን መጋቢት 19/2006 ዓ.ም በአዲስ አበባው ታላቁ አንዋር መስጂድና በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ መስጂዶች በአዲስ መልክ ጀምረዋል፡፡ አዲስ አበባ ስታዲየም በሚከበረው የኢድ አልፈጥርና ሌሎች በዓላት እንዲሁም አርብ አርብ በየመስጊዱ የመንግስትን ጣልቃ ገብነት፣ መጅሊሱ በህጋዊ መንገድ የተመረጠ አለመሆኑንና የታሰሩትን የሙስሊም የመፍትሄ አፈላላጊዎች በተመለከተ ድምጻቸውን ሲያሰሙ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ባለፉት ጥቂት ወራት እንቅስቃሴያቸው ተቀዛቅዞ ታይቶ የነበረ ቢሆንም ባለፈው አርብ ያደረጉት ሰላማዊ ተቃውሞ እንቅስቃሴው አለመዳከሙን አስመስክሯል፡፡

እንቅስቃሴው ይደረግበታል ተብሎ ከታሰበው አርብ ሁለት ቀናትን ቀድሞ በፊስ ቡክ በተላለፈው መልዕክት መሰረት ‹‹ሰላታችንን በመስጂዳችን!›› በሚል መሪ ቃል እንቅስቃሴ እንደሚደረግና ለሰላማዊነታቸውም ነጭ ወረቀት ይዘው እንደሚገኙ ተገልጹዋል፡፡ ይህንንም በአርቡ መርሃ ግብር ተግብረውታል፡፡ በወቅቱ በተለይ በታላቁ አንዋር መስጂድ ከፍተኛ ቁጥር ያለው አማኝ የተገኘ ሲሆን ከቀኑ 6፡50 አካባቢ ጀምሮ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ነጭ ወረቀቶችን በማውለብለብ ተቃውሟቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ተቃውሞ መሰረት ከቆየው በተጨማሪ ‹‹ህዝቡን ከመስጂዱ ለመነጠል በመንግስት በኩል እየተሰራ ያለውን ህገ ወጥና ኢ-ህገ መንግስታዊ›› ስራ እየሰራ ነው የሚል መነሻም ያለው ነው፡፡

በፊስ ቡክ በተሰራጨው መልዕክት መሰረት ተቃውሞው እንደሚደረግ ያወቀው መንግስት በርካታ ፖሊሶችን የመደበ ሲሆን በወቅቱ ከ6፡10 ጀምሮ በአካባቢው የነበሩ የጎዳና ተዳዳሪዎችን፣ የቀን ሰራተኞችንና ሌሎችንም ከአካባቢው እንዲለቁ ተደርገዋል፡፡ በተወሰኑት ላይም ድብደባ ደርሶባቸዋል፡፡ ይሁንና በአንዋር የተገኙት አማኞች ስነ ስርዓቱን ሰላማዊ በሆነና በሰለጠነ መንገድ አከናውነው ተለያይተዋል፡፡

መጅሊሱ የማን ነው?

ለኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች እንቅስቃሴ አንደኛውና ዋና ምክንያት የመጅሊሱ ምርጫና ገለልተኝነት ጥያቄ ነው፡፡ ምንም እንኳ መጅሊሱ በመስጂዶች ይመረጣል ተብሎ ቢታሰብም በተቃራኒው ቀበሌ ውስጥ መመረጡ ምርጫው ላይ የመንግስት ጣልቃ ገብነት አለ የሚለውን ጥርጣሬ እጅጉን አጠናክሮታል፡፡ ተመራጮቹ ከመንግስት ጎን ሆነው የሙስሊሙን እንቅስቃሴ አባላት የሚከንኑ መሆናቸው ደግሞ የሙስሊሙን ማህበረሰብ ጥያቄ ተጨባጭነት የሚያጠናክር ሆኗል፡፡ ይህን ተከትሎም መጅሊሱ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያጣ አድርጎታል፡፡ በአርቡ ተቃውሞም መገንዘብ የተቻለው ይህንኑ ጉዳይ ነው፡፡ ከመስጅዱ አጥር ግቢ በተጨማሪ በራጉኤልም (በአንዋር በላይ) ሆነ በአንዋር በታች ያለው መተላለፊያ በአማኞቹ ተሞልቶ የነበር ሲሆን የስግደት ስነ ስርዓቱ እንዳለቀ በቦታው የነበሩት ሁሉም አማኞች በሚባል መልኩ ተቃውሞውን አሰምተዋል፡፡ ይህም በአንድ ታላቅ መስጂድ የተገኙ አማኞች መካከል አብዛኛው (ሙሉ ለሙሉ ቢባል ማጋነን አይሆንም) መጅሊሱን ከተቃወመ መጅሊሱ የማን ነው? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ የአንዋርን ቅጥር ግቢ ብቻ ሳይሆን ውጨኑንም ያጨናነቀው ህዝበ ሙስሊም የኮሚቴዎቹን መታሰር የሚቃወም ከሆነ የታሰረው አብዛኛው ህዝበ ሙስሊም ስለመሆኑም ግልጽ ነው፡፡

መንግስት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እንቅስቃሴን ከአልቃይዳ፣ አልሸባብ፣ እንዲሁም በኮሃራም ጋር ሳይቀር ለማገናኘት በመሞከር ‹‹ህገ ወጥ›› መሆኑን ለማሳየት ሞክሯል፡፡ በአገር ውስጥ ከሚገኙትም ሆነ በውጭ ካሉት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሳይቀር ከሙስሊሙ እንቅስቃሴ በስተጀርባ እየሰሩ ስለመሆናቸው በርካታ የኢቴቪ ዶክመንተሪዎችና መግለጫዎች ተላልፈውባቸዋል፡፡ ይሁንና እስካሁን የሙስሊሙ እንቅስቃሴ በሰከነና በሰላማዊ መንገድ፤ መንግስትና ከመንግስት ጋር ግንኙነት አለው የሚባለው መጅሊስ ከሚወቅሰው በተቃራኒ እንቅስቃሴውን ቀጥሏል፡፡ በተለይ ባለፈው አርብ የተደረገው እንቅስቃሴ ከሙስሊሙ እንቅስቃሴ

ወደ ገፅ 15 ይዞራል

የሂውማን ራይትስ ዎች የቴሌኮም እና ኢንተርኔት ቁጥጥር በኢትዮጵያ ሪፖርት

• ‹‹እያንዳንዷን እንቅስቃሴያችንን ያውቃሉ››

ጃፈር ስዩም

ተቀማጭነቱን በአሜሪካ ያደረገው ሒውማን ራይትስ ዎች የተባለው የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት በመላው ዓለም ላይ የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶችን በማጋለጥ የሰብአዊ መብቶችን ለማስጠበቅ የተቋቋመ አለም አቀፍ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ በተደጋጋሚ ጊዜ ከተጎጂዎች ጎን በመቆም የሰብአዊ መብት ረገጣዎችን አውግዟል፡፡ አጥቂዎች ለፍርድ እንዲቀርቡም ይወተውታል፡፡ የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪው ድርጅት ከሰሞኑ በኢትዮጵያ ያለውን የቴሌኮም እና የኢንተርኔት ቁጥጥር ላይ ያተኮረ የ145 ገጽ ሪፖርት አውጥቶ ነበር፡፡ ሪፖርቱ ከመስከረም 2005 እስከ መጋቢት 2006 በተደረገ ጥናት ላይ መሰረት አድርጎ እንደተሰራ ይገልጻል፡፡ ለጥናቱ ዝግጅትም በ11 ሃገራት የሚኖሩ (ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ደቡብ ሱዳን፣ እስራኤል፣ አሜሪካ እና በአውሮፓ 5 ሃገራት) የሚኖሩ ከ100 በላይ ሰዎች ቃለ-መጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡ ሆኖም ግለሰቦቹ ነጻ ሆነው እንዲናገሩ አብዛኛው ቃለ መጠይቅ ከኢትዮጵያ ውጭ እንደተደረገ ከሪፖርቱ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ሪፖርት የኢትዮጵያ መንግስት ቁጥጥሩን በቴሌኮም ስርአቱ ላይ የዘረጋበትን መንገድ በሰፊው ይዳስሳል፡፡

በአጭር መግለጫ የሚጀምረው ሪፖርቱ የተቃዋሚ ድርጅት አባል የነበረ ግለሰብን ንግግር ከሪፖርቱ መንፈስ ጋር በቀጥታ ስለሚያያዝ ለመግቢያነት ተጠቅሟል፡፡ “በፖሊስ ቁጥጥር ስር ስውል ሁሉንም ነገር አሳዩኝ፡፡ የተደወሉልኝን ስልኮች በሙሉ እንድመለከት አደረጉኝ፡፡ ከዛም የቀረጹትን ከወንድሜ ጋር በስልክ የተነጋገርኩትን ጭውውት እንዳዳምጥ ከፈቱት፡፡ በርግጥም ታስሬ የነበረው በስልክ ውጭ ሃገር ከሚገኝ ወንድሜ ጋር ፖለቲካ ነክ ነገር በማውራቴ ነው፡፡ ሆኖም በስልክ ስነጋገር ያለ ምንም ስለላ በነጻነት የማወራ ይመስለኝ ነበር” ብሏል፡፡

የሪፖርቱ መግቢያ የኢህአዴግን የኋላ ታሪክና ባህሪ ያስረዳና ገዢው ፓርቲን የመሰባሰብን እና ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን ይገድባል ብሎ ይተቻል፡፡ በተለይም ከ1997 ምርጫ በኋላ ጫናው ተጠናክሮ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን፣ ጋዜጠኞችንና ንቁ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ (activists) ግለሰቦችን ከህግ ውጪ የመክሰስና ማሰር ድርጊቶች መፈጸሙን የድርጅቱ ሪፖርት ያስረዳል፡፡ የጸረ-ሽብር ህጉና የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አዋጅ በርካቶችን ለውጥ ማምጣት የሚችለው ድምጻቸውን እንዳያሰሙ አፍኗል ሲል የእነዚህን አዋጆች መጽደቅ ሪፖርቱ ያጣጥላል፡፡

የሒውማን ራይትስ ዎች ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት ቃለ መጠይቆች ቁጥራቸው እጅግ የበዛ የኦሮሞ ተወላጆች ከህግ ውጪ ለሚደረግ ቁጥጥር እንደተጋለጡ ያስረዳል፡፡ በቁጥጥር ስር ውለው የታሰሩትም በኦነግ አባልነትና ደጋፊነት ተከሰዋል ሲል ሪፖርቱ ያብራራል፡፡ አንዳንዶቹ ተጠርጣሪዎችን በኦነግ አባልነት ወይም ደጋፊነት የሚያስጠረጥሩ በቂ ነገሮች ቢኖሯቸውም ብዙሀኑ ኦሮሞ ለክስና እስር የተዳረገው በኦሮሞነት የተሰባሰቡ የንግድና የባህል ማህበራትን እንዲሁም የኦሮሞ ባህልን

ለማክበር (በሙዚቃ እና ስነ-ጥበብ) በመሞከራቸው እና በሀገሪቷ ውስጥ ባሉ ህጋዊ ፓርቲዎች ስር ተመዝግበው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ በማድረጋቸው ነው ሲል ሂደቱን ያወግዛል፡፡ ልክ እንደ ኦነግ ሁሉ የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻ አውጪ ግንባር ወይም ኦብነግ የተባለው ድርጅትም የዚሁ ጥቃት ሰለባ እንደሆነ ሪፖርቱ ያያይዛል፡፡ አንድ የቀድሞ የደህንነት ሃላፊ ለሂውማን ራይትስ ዎች የሰጠው ቃል ሪፖርቱን ወደ እውነታነት ማዘንበሉን ያረጋግጥ ነበር፦ “ግለሰቦችን በመሰለል ከኦነግ፣ ኦብነግ ወይም ግንቦት 7 የመሳሰሉት ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ማድረጋቸውን የሚያሳይ ተጨባጭ መረጃ ለማግኘት እንሞክር ነበር፡፡ ግንቦት 7 ያን ያህል በሃገሪቷ ላይ ስጋት የሚፈጥር ድርጅት አይደለም፡፡ ግን አሁንም ድረስ ግለሰቦችን ለማጥቃት የግንቦት 7 ስጋትን መንግስት ይጠቀሙበታል፡፡” ይላል የቀድሞው የደህንነት ሀላፊ፡፡ ሌሎች በሽብርተኝነት የተፈረጁ ድርጅቶችን አስመልክቶ ደግሞ “አነግም በአሁን ሰአት የሽብር ጥቃትን ሊያደርስ ይችላል የሚባል አሸባሪ ድርጅት አይደለም፡፡ ብቸኛው እና እውነተኛው መሬት ላይ ያለ አሸባሪ ድርጅት የኦጋዴን ነጻ አውጪ ግንባር(ኦብነግ) ነው፡፡” ሲል ለመረጃ ቅርበት የነበረው የቀድሞ የደህንነት ባለስልጣን ለሂውማን ራይትስ ዎች ገልጿል፡፡

ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ቁጥጥርን በሰፊው በሚያደርግ መንግስት ስር ውስጥ እንደሚኖር ያውቀዋል የሚለው ሪፖርቱ ለዚህም የኢንተርኔት እና ሞባይል አገልግሎቶችን በመንግስት በኩል ብቻ ማግኘት መቻሉን በአስረጂነት ያቀርባል፡፡ ተቀማጭነቱን በኬንያ ያደረገ የፖለቲካ ጥገኝነትን የጠየቀ ግለሰብ ስለሁኔታው ጠቅለል ባለ ሁኔታ እንዲህ አስረድቷል፡፡ “የተሟላ ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡ እኔ መምህር ነበርኩ፡፡ ኢህአዴግን እንድቀላቀል ተጠየቅኩ፡፡ እምቢ ስላልኩም ከስራ ተባረርኩ፡፡ ቤተሰቦቼ ገበሬዎች ነበሩ፡፡ በኔ የተነሳ የሚተክሉትን ዘር እና ሌሎች ጥቅሞችን እንዳያገኙ ተደረጉ፡፡ ብዙ የማውቃቸው ሰዎች በመንግስታችን አካሄድ ላይ ተናደዋል ግን ለህይወታቸው እና ኑሯቸው በመፍራት በፖለቲካ ውስጥ አይሳተፉም፡፡.... ” እያለ ግለሰቡ ያስረዳውን ሪፖርቱ ቃል በቃል አስረድቷል፡፡

ሒውማን ራይትስ ዎች ያናገራቸው ብዙ ኢትዮጵያውያን የስልክ ጥሪዎቻቸው እና ኢ-ሜይላቸው ቁጥጥር እንደሚደረግበት ያምናሉ፡፡ ከኢትዮጵያ ውጪ በስደት ላይ ያሉም ዘመድ ወዳጆቻቸው “እጅግ አደገኛ ነው” በማለት እንዳይደውሉላቸው በተደጋጋሚ እንደሚያሳስቧቸው ሪፖርቱ ይናገራሉ፡፡ እንደ ሪፖርቱ ገለጻ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ሰዎች ስልካቸውን ያለ ምንም መልእክትና ንግግር ለቀጠሮ መቀጣጠሪያነት ብቻ ይጠቀሙበታል ብሏል፡፡ አንድ አርሶ አደር(ገበሬ) የሰጠውን አስተያየትም ሪፖርቱ አስፍሯል፡፡ “ሁላችንም እያንዳንዷ እንቅስቃሴያችንን እንደሚመለከቱ እናውቃለን፡፡ ያለ እነሱ እውቅና የትም መሄድ አንችልም፡፡ መንግስትን በተመለከተ ትችት የሚመስል አስተያየቶችን መስጠትንም አንችልም፡፡ እነሱን ሳንደግፍ ትምህርትንም ሆነ ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት ከባድ ነው፡፡ ስልካችን እንደሚጠለፍም

ወደ ገፅ 15 ይዞራል

የመምህራን ፍዳ . . .

ከ ገፅ 3 የዞረ

አገልግሎት 1700 ብር ገደማ ይከፈለዋል፡፡ ከዚህ ወርሃዊ ገቢ ላይ በትንሹ 800 ብር የቤት ኪራይ ይከፍላል፤ ግብር አለ፤ የተለያዩ መዋጮዎችም ይቀነሱበታል፡፡ ‹‹በቸርነቱ እንጂ ገቢያችንማ ሊያኖር የሚችል አይደለም፡፡ መምህር በነጻ እየሰራ እንደሆነ ነው የማምነው፡፡›› ይላል የአብዮት ቅርስ መምህሩ፡፡

የገቢ ልክ ማነስ መምህራን በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ቦታ ዝቅ እንዲል እንዳደረገ መምህራን ይናገራሉ፡፡ ‹‹እንደድሮው ሳይሆን አሁን ላይ መምህራን በማህበረሰቡ ዘንድ እጅግ ዝቅተኛ ተቀባይነት ነው ያለን፡፡ መምህር በምንም ሁኔታ ከተማሪው ተሽሎ መታየት አልቻለም፡፡ እስኪ አሁን ከተማሪና ከአስተማሪ የትኛው ነው ላፕቶፕ በእጁ የሚገኘው...ተማሪው ነው፡፡ መምህራን ላፕቶፕ እንኳ መግዛት ይከብዳቸዋል፤ ሳያስፈልጋቸው ቀርቶ ግን አልነበረም የማይገዙት፡፡››

እንደመምህራኑ ከሆነ ማህበረሰቡ ለመምህራን ቦታ አጥቷል፡፡ ‹‹መምህር የተናቀበት ማህበረሰብ ፈጥረናል፡፡ ወዴት እያመራን እንደሆነ አይገባኝም፡፡ ያለመምህር አንዲት ሀገር ወዴትም ልትደርስ አትችልም፡፡›› በእርግጥም መምህራን ቀደም ባለው ጊዜ የነበራቸው ክብር ከፍተኛ ነበር፡፡ እንዲያውም፡-

የእኛ ሙሽራ ኩሪ ኩሪ

አገባሽ አስተማሪ፤
ወሰደሽ አስተማሪ፤

ይባል ነበር፡፡ ‹‹...ዛሬ ላይማ ገና መምህር መሆንህ ሲታወቅ ሰው ይሸሽሃል፡፡ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች ሁሌም መምህሩን እያዩ ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡ መማርን ሲያስቡ የተማረውስ የት ደረሰ ብለው ይጠይቃሉ፤ የመምህሩን ህይወት በአጠገባቸው ያያሉ፡፡ ብዙ ተማሪዎች ወደ አረብ ሀገራት ለመሄድና መንጃ ፍቃድ ለማውጣት የሚያስችላቸውን ደረጃ ነው የሚያልሙት፡፡ ተስፋ አይታይባቸውም፡፡ ለምን አትምሩም የሚል መምህር ካለም አንተ የት ደረስክ ብለው ነው የሚጠይቁት፡፡›› ይላል የእንጦጦ አምባ መምህሩ፡፡

የአብዮት ቅርስ ወጣት መምህሩ በበኩሉ፣ ‹‹መምህራን የምንኖረው በኩሽና ቤትና በሽንት ቤት ውስጥ ነው ማለት እችላለሁ፡፡ ጥራት ሳይሆን ዋጋ የሚቀንስ ቤት ነው የምንፈልገው፡ ፡ ገንዘብ የለማ! ይህን ህይወታችንን ደግሞ ተማሪዎች ያያሉ፡፡ ምክንያቱም መምህሩ የሚኖረው በተማሪ ወላጆች ቤት ተካራይቶ ነው፡፡ የወረደ የሚባል ኑሮ ሲኖር እያዩ እንዴት መምህሩን ማክበር ይቻላቸዋል?›› ሲል ይጠይቃል፡፡

ይህ ሁሉ በመምህራን ላይ ለምን?

ያነጋገርኳቸው መምህራን መንግስት ሆን ብሎ መምህራንን የማዳከም ስራ እየሰራ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ አንድ ፀሐይ ጮራ ት/ቤት የሚያስተምር የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር እንዲህ ሲል ይገልጻል፤ ‹‹የመንግስት ዓላማ መምህራንን ከማንኛውም ለውጥ ለማግለል ነው፡፡ በቀደመው ጊዜ መምህራን ግንባር ቀደም የለውጥ ጠንሳሾችና አንቀሳቃሾች ነበሩ፡፡ በራሳቸው መብታቸውን ያስከበሩና ለሐገርም አለኝታ ነበሩ፡፡ ይህም የሆነው መምህራን በራሳቸው የቆሙ ስለነበሩ ነው፤ በገቢም በእውቀትም ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኙ ስለነበር ነው፡ ፡ ስለሆነም ማንኛውንም አይነት ጥያቄ ማንሳት ይችሉ ነበር፡፡ አሁን ግን ስለዕለታዊ ዳቦህ ብቻ እንድታስብ ነው የተፈለገው፡፡ የመብት ጥያቄ ለማንሳት እንዳይቻለን አድርገው ነው የያዙን፡፡››

በእርግጥም አብዛኛውን ጊዜ በማንኛቸውም የለውጥ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መምህራን ይኖራሉ፡ ፡ ራሳቸው ነቅተው ማህበረሰቡን በማንቃት የመብትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን በማንሳት መምህራን ግንባር ቀደሞች ናቸው፡፡ ለአብነትም በኢትዮጵያ አብዮት ወቅት መምህራን ተማሪዎችን በማስተባበርም ሆነ በራሳቸው ተደራጅተው በመንቀሳቀስ ጉልህ ድርሻ ነበራቸው፡፡

ስለዚህም መምህራን አሁንም ለስርዓቱ የማይመቹ ሊሆኑ እንደሚችሉ ኢህአዴግ የተገነዘበ ይመስላል፡፡ ‹‹...ስለዚህ መምህራንን አጥብቆ መያዝ አለበት፡፡ በገቢም በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችም መምህራን ከእጁ እንዳይወጡ መንግስት ሆን ብሎ የሚሰራ ይመስለኛል፡፡ እንዲያውም አንድ ለአምስት ይህን ለመቆጣጠር የተዘረጋ ነው፡፡ ስለሀገርህ ለውጥ እንዳትወያይ ተራ አጀንዳ በየጊዜው እያወረደ በስራ ይጠምድሃል፡፡ በገቢ እንዳትደረጅ ከልክሎሃል፡፡ ድሮ መኪና ያለው መምህር ነበር፡፡ የራሱ ቤት ነበረው፡ ፡ ሱፍ ለባሽ ነበር፡፡ አሁንስ? አሁን ይህ ሁሉ እንዲኖርህ አይፈለግም፡፡›› ይላል የፀሐይ ጮራ ት/ቤት መምህሩ፡ ፡

የእንጦጦ አምባ መምህሩም ይህን ሐሳብ ይጋራል፡፡ ‹‹...በእርግጥም መንግስት ይህ (መምህራንን ማዳከም) ዓላማዬ ብሎ የያዘው ነገር ባይሆን ኖሮ ህይወታቸውን መቀየር ቀላል ነበር፡፡ ግን አይፈልግም፤ ጥገኛ ሆነው እንዲኖሩ ብቻ ነው የሚፈልገው፡፡ አሁን መምህራን ላይ ቀልድ የማይቀልድ ማን አለ...እንደ መምህራን ደመወዝ ቡን ያድርገኝ የሚሉ ወጣቶች ስንት ናቸው? ይህ ምን ማለት ነው? በራስ እንዳትተማመን ማድረግ አይደለም? ይህ ሆን ተብሎ የተሰራ ስራ ነው፡፡››

ተቆርቋሪ ማጣት!

የኢትዮጵያ መምህራን በ1960ዎቹ መጨረሻና 70ዎቹ ጠንካራ የሙያ ማህበር ነበራቸው፡፡ ያን የመሰለ ጠንካራ መምህራን ማህበር አሁን ላይ ማግኘት እንዳልተቻለ ነው ያነጋገርኳቸው መምህራን የሚገልጹት፡፡ ‹‹ያን ጠንካራ ማህበር አሁን አታገኘውም፤ አፈራርሰውታል፡ ፡ ለምን ያልክ እንደሆን ማሽመድመድ ስለፈለጉ ነው፡፡ ማህበር ለይስሙላ አለ፤ ዳሩ ግን የመምህሩን ጥቅምና ሙያዊ ክብር ማስጠበቅ አልቻለም፡፡ ሲመስለኝ የማህበሩ ዓላማ መንግስትን ማገልገል ነው፡፡

‹‹የሙያ ማህበሩ ተለጣፊ ነው፡ ፡ ለሙያውና ለመምህራን ጥቅም ሳይሆን እንደማፈኛ መሳሪያ የዋለ አድርጌ ነው የማየው፡፡ የሆነ ጊዜ ማህበሩ አይወክለንም ብለን ፊርማ ብናሰባስብ ‹‹የህዝብ ክንፍ ለማፍረስ ተንቀሳቅሳችኋል›› ተብለን ፍዳችን ነው ያየነው፡፡ ይህ የሚያሳይህ ማህበሩ እንደ አንድ የፖለቲካ ክንፍ ሆኖ የሚያገለግል እንጂ ለመምህራን ጥቅም አለመቆሙን ነው፡፡›› ሲል ያብራራል የእንጦጦ አምባ የታሪክ መምህሩ፡፡

እንደ መምህራኑ ገለጻ የሙያ ማህበሩ በየጊዜው መዋጮ ይሰበስባል፡ ፡ ሁሉንም መምህራን በአባልነት እንዳቀፈ አድርጎ ራሱን ይስላል፡ ፡ እውነታው ግን ሌላ ነው፡፡ ‹‹... መምህር ከሆንክ የማህበሩ አባልነት ግዴታ ነው፡፡ ወደድህም ጠላህም ከደመወዝህ ላይ የአባልነት መዋጮ ተብሎ ይቆረጣል፡፡ ከአንድ መምህር በአማካይ 4 ብር ወርሃዊ መዋጮ አለ፡፡ አሁን ባለው መረጃ መሰረት በኢትዮጵያ ያለው የመምህራን ቁጥር ከ350000-400000 ይደርሳል፡ ፡ በአዲስ አበባ ብቻ ወደ 16000 መምህራን አሉ፡፡ ብዙ ገንዘብ እየገባ ግን መምህራን ምንም ሲደረግላቸው አታይም፡፡›› ሲል ይናገራል የአብዮት ቅርስ የኬሚስትሪ መምህሩ፡፡

‹‹ከመምህርነት ማምለጥ››!

እንደ መምህራኑ ገለጻ አሁን ላይ መምህርነት የሚሸሽ ሙያ እየሆነ ነው፡፡ የኬሚስትሪ መምህሩ ይናገራል፤ ‹‹በፊት በፊት መምህር ስትሆን የሞራል እርካታ ይኖርሃል፡ ፡ በማህበረሰቡ ዘንድም ተቀባይነትህ ከፍተኛ ነበር፡፡ ይህም መምህራን ሙያውን እንዲወዱት ያደረገ ነበር፡፡ አሁን ክብር ማጣት አለ፤ ትናቃለህ፡ ፡ መምህር ነኝ ካልክ እንደ አንዳች የሚዘገንን ነገር ፊቱን የሚያዞርብህ ነው የሚበዛው፡፡ እኔ መምህር ነኝ ብዬ አልናገርም፡፡ መምህር ነኝ ስል እንደ መጥፎ ሽታ ሰው የሚያርቀኝ ከሆነ ለምን መምህር ነኝ እላለሁ...? በሙያህ ማፈርን የመሰለ አሳዛኝ ነገር ምን አለ...? ግን እየሆነ ያለው ይህ ነው፡፡››

መምህሩ ከመምህርነት ሙያ መውጣት ይፈልጋለሁ፡፡ ለዚህም ሌላ ዲግሪ እየተማረ ነው፡፡ ‹‹ማምለጥ እፈልጋለሁ፡፡ መምህር ሆኜ መሞት አልፈልግም›› ሲል ተስፋ በቆረጠ ስሜት ይናገራል፡፡ እንደ መምህሩ እምነት መምህራን ሌላ አማራጭ ስራ ቢያገኙ ሁሉም በአንድ ሴኮንድ ት/ቤቶችን ትተው ሊሄዱ ይችላሉ፡ ፡ ‹‹አንዳንዶች ጡረታ ለማስከበር ነው ቀናቸውን የሚጠብቁት፡፡ በዚህ ከቀጠልን ት/ቤቶች ኦና ከመሆን አያመልጡም፡፡››

አሁን ባለው የደመወዝ ስኬል መሰረት አንድ መምህር ከ21 ዓመት በኋላ (በሚገባ እርከኖችን ካለፈ) 3060 ብር ላይ ነው መድረስ የሚችለው፡፡ ለዚያውም ታታሪ የሚባለው መምህር ነው፡፡ ‹‹ታዲያ ተስፋህ ምንድነው? ...በግሌ መምህርነት ትልቅ ሙያ መሆኑን አምናለሁ፤ ነውም ደግሞ፡ ፡ ግን አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ምክንያት እጠላዋለሁ፡፡ ከማስተማር ሙያ መውጣት አለብኝ፡፡››

የእንጦጦ አምባ ት/ቤት የታሪክ መምህሩም ይህን ሀሳብ ይጋራል፡ ፡ ‹‹እኔ በመምህርነት ዲግሪ አለኝ፡፡ ነገር ግን አሁን ከሙያው መውጣት እፈልጋለሁ፡፡ ለዚህም ወደታች ወርጄ ሌላ ትምህርት በዲፕሎማ እየተማርኩ ነው፡፡ ሙያውን ጠልቸው አይደለም፤ የሚያሰራኝ ሁኔታ ግን የለም፡ ፡ መኖር እኮ አልቻልኩም፡፡ ትዳር መመስረት አልችልም፤ ምን አለኝና ትዳር እመሰርታለሁ፡፡››

•በመጨረሻም የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ሁለት ነገሮችን ብቻ ማስቀመጥ ይፈልጋል፡፡ አንድ፣ የመምህራንን ጩኸት መንግስት እንዲሰማ ያሳስባል፡ ፡ ሁለት፣ መምህራን ህብረታችሁን አጠናክራችሁ በመታገል ጥቅማችሁን ማስከበር ይቻላችኋልና አድርጉት፡ ፡ ከሙያችሁ መሸሽ ዘላቂ መፍትሄ አይሆንም፤ ስርዓቱ ባይፈልጋችሁም ኢትዮጵያ ትፈልጋችኋለች! ሐገር ያለእናንተ ባዶ ነች፡፡

በመግቢያየ ላይ የጠቀስኩት አባባል የአንድ የባዮሎጅ መምህር የዘወትር ንግግር ነው፤ ታመነ ይባላሉ (ጋሽ ታመነ)፡፡ ይህን ግሩም የጋሽ ታመነ አባባል በድጋሜ ልዋስ፣ ‹‹እኔ ጆርጅ ቡሽን (ፕሬዚዳንት) አላደንቅም፤ ጠፈር ላይ የወጡትንም አላደንቅም፡፡ የማደንቀው እነዚህን ሰዎች ለትልቅ ደረጃ ያደረሷቸው መምህራንን ነው፡፡››

(በቀጣይ፣ ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ሌሎች ጽሑፎችን ለማስነበብ እሞክራለሁ፡፡)

ብሩህ ጊዜ ለመምህራን ይሁን!

በል ግፋ በል ግፋ ጨምር . . .

ከ ገፅ 8 የዞረ

የሚሰጠው ሆኗል፡፡

በዚህ ሂደት የኢትዮጵያ ህዝብ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን ለመመከት በቁርጠኝነትና በዓላማ ፅናት እንዲነሳ ተከታታይ አዋጆች መውጣታቸውም በታሪክ ይታወሳል፡፡ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተፈርመው የወጡት እነዚህን ተከታታይ አዋጆች ለማይጨው ዘመቻ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል፡ ፡ በወቅቱ አንዳንድ አዋጆች መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ማዕከል አድርገው የወጡ ሲሆን የተቀሩት ግን በጠቅላይ ግዛት ደረጃ ህዝቡን ለማነሳሳት የታለሙ እንደነበሩ ታውቋል፡፡ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከቀረቡት አዋጆች አንዱን እነሆ!

ሞዓ አንበሳ በእምነገደ ይሁዳ

ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ

ስዩመ እግዚአብሔር ንጉስ ነገስት ዘኢትዮጵያ

ጦርነቱም እንደ ተጀመረ እንዳስታወቅናችሁ ቃል የኢትዮጵያ ህዝብ ልብ በአንድነት ሆኖ የመጨረሻው ጠብታ ደም እስኪፈስ ለመመከት እኛም ከጦር ሰራዊታችን መካከል ለመገኘትና ፈተናውን ለመካፈል ቆርጠን ስለተነሳን ይህንኑ እንኳን የኢትዮጵያ ህዝብ መላው ዓለም ተረድቶታል፡፡ አሁንም የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆንክ ስንቅ ለሌለህ ስንቅ፤ መሳሪያ ለሌለህ መሳሪያ እሰጥኃለሁና ባውራጃው በግንባር እንደተቆጠርክና እንደተፃፍክ ቆይተህ እኔ በማስታውቅህ የጦር አበጋዝ ትዘምታለህና ተሰናድተህ ተቀመጥ፡፡

በመቀጠል ደግሞ በጠቅላይ ግዛት ደረጃ ለህዝብ ከተሰራጨው ወታደራዊ አዋጅ አቅርበናል፡፡

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ

ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ

ስዩመ እግዚአብሔር ንጉስ ነገስት ዘኢትዮጵያ

የወሎ ሰው

የመጣው ጠላት በመላ ኢትዮጵያ ላይ ስለሆነ የንጉስ ሚካኤል አሽከር የነበርክ ብረትና ማደሪያ ያለህ ብረትህን ይዘህ ዝመት! ብረት ኖሮህ ማደሪያ የሌለህ ስትመለስ ማደሪያህን ላሁንም ስንቅህን እሰጥኃለሁ! ብረትም የሌለህ ጠብመንጃ እሰጥኃለሁ ዝመት!

በዚሁ በማይጨው ጦርነት አያሌ ጀግኖች በክብር ወድቀዋል፡፡ በእርግጥ የሁሉንም ስም በዝርዝር ማስቀመጥ አይቻልም፡፡ ነገር ግን በታሪክ ላይ ተመዝግበው ያገኘናቸውን ያህል በጥቂት ይዘናል፡፡

1. መንገሻ ይልማ (ደጃዝማች) በጦር ሚኒስቴር ዋና ዴሬክተር የነበረ ጀግና 2. ወንድይራድ (ደጃዝማች) የመርሳቤቴ ገዥ የነበረ ጀግና 3. አበራ ተድላ (ደጃዝማች) የማይጨው ገዥ የነበረ ጀግና 4.አሸናፊ (ፊታውራሪ) የግቢ ሚኒስቴር ባልደረባ የነበረ ጀግና 5. ኃይለ ማርያም ሳሹ (ፊታውራሪ) 6. ነጋሽ ተስፋዬ (ፊታውራሪ) 7. በየነ በላይነህ (ቀኝ አዝማች) 8. አበበ ረዴ (ቀኝ አዝማች) 9.ተናኘ ዳርጌ (ግራአዝማች) 10. እሸቱ ሸዋርካብህ (ግራ አዝማች) 11. ዳኜ ወዳጀ (ሻለቃ) እና 12. ሺበሺ ደያስ (ሻለቃ) በታላቅ ጀግንነት ተሰውተዋል፡፡

ክብር በማይጨው ጦር ሜዳ በታላቅ ጀግንነት ለተሰው ለኢትዮጵያ ሰራዊት አባላት! ክብር ዛሬም ለሕሌናቸው ታማኝ ለሆኑ ኢትዮጵያውያን! ክቡር ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ጨርሶ ከማጥፋት ለማዳን በሀገር ውስጥ እንዲሁም ከሀገር ውጭ ለሚታገሉ ጥቂት ቆራጥ ኢትዮጵያውያን! ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ! ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ያሸንፋል!

የጥንቅሩ ምንጮች፡- የማጨው ዘመቻና የንጉሡ ታሪክ በገብረወልድ እንግዳ ወርቅና ከአዜ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡፡

አንድነት ዕሁድ የተቃውሞ . . .

ከ ገፅ 1 የዞረ

የቴሌኮም አገልግሎት የለም የሚባልበት ደረጃ ላይ መድረሱን አንድነት በመግለጫው አስረድቷል፡፡

አንድነት የሰልፉን ማሳረጊያ በጠ/ሚኒስትር ጽ/ቤት ፊት ለፊት ለማድረግ ያስታወቀ ሲሆን፣ የከተማ አስተዳደሩ በበኩሉ ቦታው የዕለት ከዕለት ከፍተኛ የመንግስት ስራ የሚከናወንበት መሆኑን በመጥቀስ ለሰልፉ ዕውቅና ለመንፈግ ያለመ ደብዳቤ መጻፉን የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሀብታሙ አያሌው ለነገረ-ኢትዮጵያ አስረድተዋል፡፡ ኃላፊው አክለው እንዳስረዱት አንድነት ባሳወቀው መሰረት ሰልፉን ለማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

በአዲስ አበባ የመብራት ኃይል አቅርቦት አለመቀረፉ የከተማይቱ ኢንዱስትሪዎች፣ የንግድ ተቋማትንና ነዋሪውን እያማረረና ህይወቱን እያመሰቃቀለ ከመሄድ ውጭ ምንም አይነት ለውጥ አለማሳየቱ፣ በከተማይቱ ውሃ ማግኘት እንደ ትልቅ እድል መቆጠር በመጀመሩ ጊዜያቸውን በትምህርት ገበታቸው ላይ በመገኘት ማሳለፍ ይገባቸው የነበሩ ተማሪዎች ውሃ ለመቅዳት ረዥም መንገድ ለመጓዝ በመገደዳቸው የትምህርት ጊዜአቸው እንዲበደል ማድረጉን ፓርቲው ጨምሮ በመግለጽ ይህን በመቃወም ሰልፉን ማድረግ እንዳስፈለገ ገልጿል፡፡

በዚህም የአንድነት ፓርቲ የአዲስ አበባ ምክር ቤት ‹‹የእሪታ ቀን›› በሚል ስያሜ ዕሁድ ሠላማዊ ሠልፉ ለማድረግ መወሰኑን አስታውቋል፡፡ የአዲስ አበባና አካባቢዋ ነዋሪዎች ሰላማዊ ሰልፉ በሚደረግበት ቀን በነቂስ በመውጣት በስርዓቱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ለመግለፅ እንዲችሉም ፓርቲው ጥሪ አቅርቧል::

የሰማያዊ ፓርቲ አባላት . . .

ከ ገፅ 1 የዞረ

የደም መፍሰስ ምክንያት የሚከሰት የእናቶች ሞትን ለመቀነስ ባደረገው በዚህ ፕሮግራም ላይ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ መሳተፍ የሚችል መሆኑን የፓርቲው የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ ወ/ሮ ሀና ዋለልኝ ለነገረ ኢትዮጵያ ገልጸዋል፡፡ ይህን የደም ልገሳ ፕሮግራም አስመልክቶም ነገ ቅዳሜ መጋቢት 27 ከቀኑ 9 ሰዓት ጀምሮ ስለ ጉዳዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንደሚሰጥ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የማዕድኑ ሙስና በኢትዮጵያ

አለማየሁ ገብረማርያም (ፕ/ር)

ከሰሞኑ የ “አምራች ኢንዱስትሪዎች የግልጽነት ተነሳሽነት /Extractive Industries Transparency Initiative (EITI) ሊቀመንበር የሆኑት ማዳም ክላሬ ሾርት ስልጣናቸውን ከህግ አግባብ ውጭ በመጠቀም እና በማስፈራራት በኢትዮጵያ ያለው ገዥ አካል የሙስና ማጋበሻ ቡድናቸው አባል እንዲሆን ለማስቻል የEITI የቦርድ አባላት ድምጻቸውን እንዲሰጡ በማድረጉ ጥረት ሲያካሂዱት የቆዩት ዥዋዥዋዊ ጨዋታ ተሳክቶላቸዋል። ማዳሚ አሮጌውን እና ያረጀ ያፈጀውን የአሰራር ሂደትን ማለትም እጅ በመጠምዘዝ፣ በኃይል በማስፈራራት፣ ስልጣንን ከህግ አግባብ ውጭ በመጠቀም በማስገደድ፣ ከኋላ ሆኖ በማስተኮስ፣ ስልጣንን መከታ በማድረግ ከህግ አግባብ ውጭ በግድ እንዲያምኑ በማድረግ፣ አሰልቺ እና የምጸት ቃላትን በመጠቀም እና የህጻናት ዓይነት እሽሩሩ ዘይቤ ቁጣን በመከተል ለርካሽ ጥቅም ሲባል የሞት ሽረት ትግል በማድረግ ሀቅን በመደፍጠጥ በሸፍጥ ለጊዜውም ቢሆን ሀሳባቸውን አሳክተዋል።

ማዳሚ በእንደዚህ ዓይነት እኩይ ምግባራቸው የተካኑ ናቸው። እ.ኤ.አ በ2003 እንግሊዝ እና አሜሪካ በኢራቅ ላይ ወረራ ለማካሄድ በተዘጋጁበት ጊዜ ማዳም ሾርት በቶኒ ብሌር ላይ ጠንካራ የሆነ ትችት በማቅረብ ከመንግስታቸው ዓለም አቀፍ የልማት ጸሐፊነት ስልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው እንደሚለቁ በማስፈራራት ሁኔታውን በመቃወም የኃይል ትችት አቅርበው ነበር:: ብሌርንና የአሜሪካን መንግስት ሲተቹ እንዳሉት “ሆኖም ግን በዚያም ተባለ በዚህ የጦርነቱ መካሄድ አይቀሬነት በተረጋገጠበት ወቅት፣ ሌሎችን አገሮች በኃይል እና በማስፈራራት ለጦርነቱ መካሄድ ድጋፍ እንዲሰጡ ያስገድዱ ነበር።

እንደ ኢራቁም ጉዳይ ማዳም ክላሬ “በኢትዮጵያ ያለው ገዥ አካል ድምጽ በማግኘት የEITI አባል እንዲሆን ከህግ አግባብ ውጭ ስልጣንዎን በመጠቀም የቦርድ አባላትዎን ያስገድዱ እና ያሳምኑ እንደነበር እናውቃለን። እንኳን ደስ ያለዎት! ድል ተቀዳጅተዋል፡ ፡ የድል ደረጃ አድርገው ይውሰዱት፣ ጣራውን ከፍ ያድርጉት። “ለሰብአዊ መብት የሚሟገቱትን ድል አድርገዋል፣ በእራስዎ ቦርድ ያሉትን የሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮችን በመላው ዓለም ፊት አዋርደዋል፣ እናም ዕድለቢሶችን እና ድምጽ አልባ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ማህበረሰብ አባላትን አባርረዋል፣ “መብቶቻቸውንም” ደፍጥጠዋል፤ አሁን አዲስ አበባ በመሄድ የስኬት በዓልዎን ቸበርቻቻ ማክበር ነው። በትግል ያገኙት ውጤት ነውና። ቻምፓኝ እና ኮኛክ እንደ ጅረት ውኃ ይፍሰስ። አሁን EITIን የእርስዎ የግል ንብረት አድርገውታል፡ ፡ የእራስዎ ህጻን ነው! ለEITI አዲስ ስም ያውጡለት። የማዳም ክላሬ የሙስና ማጋበሻ ድርጅት በሉት? ጥሩ የእምነተቢሶች የመጠሪያ ስምን ይዟል።

በኢትዮጵያ ያለውን ገዥ አካል የEITI አባል በማድረጉ እረገድ ማዳም ሾርት የማዕድን ሙስናን ለመቆጣጠር የሚያስችል ቀላል እና በሚከተለው ዳህራ ላይ ትኩረት ያደረገ በአጭር ርቀት ላይ የተመሰረተ ድሁር ህልዮት ቀምረዋል፤ ህልዮቱም እንዲህ ይላል፣ “በዓለም ላይ በጣም በሙስና የተዘፈቁ ገዥ አካላት የይስሙላ የግልጽነት እና ተጠያቂነት ካባን ደርበው የEITI አባል እንዲሆኑ መፍቀድ።“ ከዚያም እግሮችን በማንሸራተት መደነስ እና ማቀንቀን። ስለግልጽነት እና መልካም አስተዳደር ጥቂት አስመሳይ ቃላትን እና ሀረጎችን በማነብነብ የህዝብ እምነትን ለማግኘት የማታለያ ጥረት ማድረግ፡ ፡ የውሸት በእመኑኝ ላይ የተመሰረቱ ጥሩ የሚመስሉ የቢሮክራሲ ፍሬ ከርስኪ የታጨቁበት የማመልከቻ ቅጽ መሙላት፡ ፡ ከዚያም በማዕድን ዘርፍ ስራው ጥሩ ተሞክሮ እና ታማኝ መሆናቸውን በመግለጽ የአባልነት ጥያቄውን የምስክር ወረቀት ለማግኘት መጠየቅ፡ ፡ በመጨረሻም ከደስታ የመጨረሻው ከፍተኛ እርከን ላይ በመድረስ ሰርግ እና ምላሽ ማድረግ ትልቁ ግባቸው ነው፡ ፡ በሌላ አገላለጽ ማዳም ክላሬ ሾርት ገዥውን አካል የጸረ ሙስና ተዋጊ ጦር አስመስሎ በማቅረብ እንዲሁም ወሮበላ ዘራፊዎችን እና ሽፍጠኛ ወንጀለኞችን በእራሳቸው ተለክቶ የተሰፋ የማስመሰያ ካባ በማልበስ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ፊት የተከበሩ የአገር መሪዎች አስመስሎ ለማሳየት እና ለቀጣዮቹ ሶስት ዓመታት ያለምንም እንከን የጥሩዎች ሁሉ ተምሳሌት አድርጎ ለማቅረብ የተቀመረ ስሌት ነው። እንግዲህ በዚህ መንገድ ነው በአፍሪካ እና በሌሎች አገሮች ያለው በሙስና የበከተው የማዕድን እና የተፈጥሮ ጋዝ ዘርፍ በማዳም ክላሬ ሾርት ከሙስና የማጽዳት የአሰራር ዘይቤ የተቃኘው።

በኢትዮጵያ ያለው ገዥ አካል የEITI አባል እንዲሆን የተሰጠው ውሳኔ ፍጹም በሆነ ሙስና የተደረገ እና የማስመሰያ የአባልነት ተውኔት ነው። እ.ኤ.አ በ2010 ገዥው አካል ለአባልነት ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ በተደረገበት ጊዜ የተሰጠው ምክንያት፡- “የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት እና ማህበራት አዋጅ’ የሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖች በነጻነት እንዳይንቀሳቀሱ በሂደትም ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዳያደርጉ ደንቃራ ሆኗል ወደፊትም ይሆናል፤ ስለሆነም ‘የበጎ አድራጎት እና ማህበራት አዋጅ’ እስካልተወገደ ድረስ ኢትዮጵያ የEITI አባል እንድትሆን እንደማይወስን በተጨባጭ ገልጾ ነበር። በ EITI ታሪክ በእንደዚህ ያለ የአፋኝነት ህግ መሰረት ከሰብአዊ መብት አጠባበቅ ጋር በተያያዘ መልኩ አንዲት አገር የድርጅቱ አባል እንዳትሆን የአባልነት ጥያቄው ውድቅ ሲደረግ የመጀመሪያው እና ብቸኛው ክስተት ነው። (የተሰመረው አጽንኦ ለመስጠት ነው)።

ታዲያ ኢትዮጵያን በአሁኑ ጊዜ በአባልነት ለመቀበል የተቻለው በስራ ላይ እየተተገበረ ያለው “የበጎ አድራጎት እና ማህበራት አዋጅ” ተለውጦ ነው? እ.ኤ.ኤ ከ2010 ጀምሮ በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ እንቅስቃሴ ላይ ምን የተለወጠ ነገር አለ? “በአዋጁ” መውጣት እና በስራ ላይ መዋል ቀጥተኛ እንደምታ ምክንያት እ.ኤ.አ በ2010 ብዛታቸው 4,600 የነበሩት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በአስደንጋጭ ሁኔታ ቁጥራቸው አሽቆልቁሎ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ በዓመቱ መጀመሪያ አካባቢ 1,400 ሊሆኑ ችለዋል። “ከእነዚሁ ከተረፉት እና በሞት የሽረት ትግል ውስጥ በመንፈራገጥ ላይ ከሚገኙት ድርጅቶች ውስጥ ደግሞ በአዋጁ አሳሪነት ምክንያት 90 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነውን የሰው ኃይላቸውን እንዲቀንሱ ተገደዋል። ” በሶስት ወራት ውስጥ በአንድ ጊዜ እርምጃ ብቻ “አዋጁ” በኢትዮጵያ 70 በመቶ የሚሆኑትን የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን ከስራ ውጭ አድርጓቸዋል፡ ፡ እ.ኤ.አ በፌብሯሪ 2010 ገዥው አካል ከተመሰረተ ብዙ ጊዜያትን ያስቆጠረውን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤን እና የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበርን በተጨባጭ የእነዚህን ሁለት ጠንካራ ተቋማት አቅም ሽባ ለማድረግ፣ እንዲሁም ደግሞ ሊያሳኩ የሚያስቧቸውን የተቋቋሙባቸውን ዝንባሌዎች እና ዓላማዎች ከህግ አግባብ ውጭ በሆነ መልኩ ለማስተጓጎል በማሰብ ሀብታቸውን እንዳያንቀሳቅሱ አገደ።

የEITI የቦርድ አባላት እ.ኤ.ኤ በ2010 የገዥውን አካል የአባልነት ጥያቄ ውድቅ ካደረገ በኋላ በእርግጠኝነት አንድ ነገር ተለውጧል። እ.ኤ.አ በማርች 2011 ማዳም ክላሬ ሾርት የEITI የቦርድ ሊቀ መንበር ሆነው ተመርጠዋል። ማዳም ሾርት ለብዙ ጊዜ ተደናቂ መሪ እና በኢትዮጵያ ላለው ገዥ አካል ሻምፒዮን እንዲሁም በቅርቡ የአረፉት የአቶ መለስ ዜናዊ ከፍተኛ አድናቂ ናቸው። በአቶ መለስ ዜናዊ ላይ ያመልካሉ። የሚያመልኳቸውግን በጥሩ ነገር ተምሳሌትነታቸው አይደለም። ምናልባትም እ.ኤ.አ በ2010 ገዥው አካል የድርጅቱ አባል እንዳይሆን ውድቅ ያደረጉትን የEITI የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮች እና የስራ ባልደረቦቻቸውን ክብር እና ሀሳብ ለማንኳሰስ እንዲሁም በወሰንየለሽ አፍቅሮ የተዘፈቁበትን ገዥ አካል ሽንፈት ለመበቀል ያደረጉት ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል። ከሁሉም በላይ ደግሞ የገዥው አካል የአባልነት ጥያቄ ውድቅ በተደረገበት ጊዜ በ EITI ታሪክ በእንደዚህ ያለ የአፋኝነት ህግ መሰረት “በግልጽ ከሰብአዊ መብት አጠባበቅ” ጋር በተያያዘ መልኩ አንዲት አገር የድርጅቱ አባል እንዳትሆን ውድቅ ሲደረግ የመጀመሪያው እና ብቸኛው ክስተት ስለነበረም ነው። ማዳም ሾርት በአቶ መለስ ዜናዊ እና ኩባንያቸው ላይ የደረሰውን “ውርደት” ለመበቀል ዕቅድ በማውጣት በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ፊት የአቶ መለስን የመጀመሪያ የአባልነት ጥያቄ ውድቅ በማደረግ ቁልፍ ሚና የተጫወቱትን የEITI የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮችን ማዋረድ ላይ ያጠነጠነ ነበር። ማዳም ክላሬ፣ በቀልተኛዋ አሁን የበቀል እርምጃዎን ወስደዋል።

ማዳም ክላሬ በኢትዮጵያ ላለው ገዥ አካል በመወገን እ.ኤ.አ ማርች 11/2014 ግልጽ ደብዳቤ በመጻፍ ድፍረት የተሞላበትን የዘመቻ ውትወታ (በማስገደድ አላልኩም) ሲጀምሩ በEITI በቦርድ አባልነት ባሉት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮች እንደ አላዋቂ ልጅ አጥፊዎች ያህል አውርደው በመመልከት የቁጣ ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ አምባርቀውባቸዋል። እብደትን የተላበሰ የሚያስገርም ምልከታም አድርገዋል፡ ፡ እንዲህ የሚል ምልከታ፣ “የEITI መርሆዎችን የሚተገብሩ አገሮችን ሁኔታ በመምለከትበት ጊዜ በኢትዮጵያ ያለው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሁኔታ በሌሎች አገሮች ከሚታየው በብዙ መልኩ የከፋ ነው የሚለውን አባባል አልቀበለውም፣“ በማለት ለእራስ ታላቅ ክብርን የሰጠ የድንፋታ ንግግር አሰምተዋል። ማዳሚ ይህንን ንግግር ሲያደርጉ ምን ለማለት ፈልገው ነው? ለመሆኑ የEITI አባላት እነማን ናቸው? EITI በአሁኑ ጊዜ 40 ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ አባል አገሮች አሉት፡ ፡ ብዙዎቹ አባል አገሮችም በዓለም ላይ በሙስና በበከቱ እና ጨቋኝ መንግስታት መዳፍ ስር እግር ከወርች ተተብትበው የሚገኙ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ አፍጋኒስታን፣ ቡርኪናፋሶ፣ ካሜሩን፣ የመካከለኛው አፍሪካ ሬፐብሊክ፣ ቻድ፣ የኮንጎ ዴሞክራቲክ ሬፑብሊክ፣ ጊኒ፣ ካዛኪስታን፣ ላይቤሪያ፣ ማሊ፣ ማውሪታንያ፣ ሞዛምቢክ፣ ኒጀር፣ ናይጀሪያ፣ የኮንጎ ሬፑብሊክ፣ ሴኔጋል፣ ሴራሊዮን፣ ካዛኪስታን እና የመን ይገኙበታል። “የኢትዮጵያ ሁኔታ ከሌሎች የከፋ አይደለም” ከሚለው ማነጻጸሪያቸው አንጻር ማዳም ሾርት በእርግጠኝነት አንድ ሊካድ የማይችል ሀቅን ተናግረዋል፣ ይኸውም በኢትዮጵያ ያለው ገዥ አካል ከሌሎች በገፍ የሰብአዊ መብት ድፍጠጣ ከሚፈጽሙት የEITI አባል አምባገነን አገሮች የከፋ አይደለም፣ ወይም ደግሞ ከብዙዎቹ የተለየ አይደለም ብለዋል። ሁሉም በሙስና የበከቱ ናቸው፡ ፡ ሁሉም የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን ህልውና ግብአተ መሬት የፈጸሙ ናቸው፡ ፡ እናም የመመንተፊያ የቆዳ ቦርሳዎችን ተሸክመው ክው ክው የሚሉ ዘራፊዎች እና ወሮበሎች ናቸው። ማዳሚ ለቦርድ አባላቱ፣ ለሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እና ለኢትዮጵያውያን/ት የዲያስፖራ ማህበረሰብ አባላት ለማስተላለፍ የፈጉት ትክክለኛው መልዕክት ግልጽ ነበር። “ሁሉንም ጸጥ ለማድረግ” ነው። ከተሰጣችሁ ቁመት በላይ አትንጠራሩ። በሙስና የበከቱ ዘራፊዎችን ሊፒስቲክስ በመቀባት የተለመደውን የቢዝነስ ስራ እናስቀጥል። በዚህ መንገድ መጓዝ እንችልምን?

ባራክ ኦባማ እጩ ፕሬዚዳንታዊ ተመራጭ በነበሩበት ጊዜ ከተናገሩት ጋር እስማማለሁ፣ “አሳማን ለማቆንጀት ሊፒስቲክ (የከንፈር ቀለም) መቀባት ይቻላል፣ ሆኖም ግን አሁንም ያው አሳማ ነው። አንድን ትልቅ አሳ በወረቀት መጠቅለል ይቻላል፣ እናም ለውጥ ብለን ልንጠራው እንችላለን፣ ሆኖም ግን መጠንባቱን አያቆምም። “ EITI ለዘራፊዎች በልክ ዩኒፎርም አሰፍቶ ማስመሰያ በማልበስ “ግልጽነት” እና “ተጠያቂነት” ብሎ ሊጠራቸው ይችላል፣ ሆኖም ግን ያው አሁንም ዘራፊዎች ናቸው። ሙስናን በEITI አርማ መጠቅለል ይቻላል እናም ንጹህ ብሎ መጥራት ይቻላል፣ ሆኖም ግን እስከ አሁንም መጠንባቱን አያቆምም፡ ፡ EITI የአፍሪካ ዘራፊ ገዥዎችን ንጹህ እና ጨዋ ለማስመሰል የሚቀባ ሊፒስቲክ ነው።

አዲስ በሆነ መልኩ ማዳም ሾርት በእርግጠኝነት ትክክል ናቸው፡ ፡ ለተፈጠረው ስህተት ይቅርታ እጠይቃለሁ! ብዙዎቹ በEITI አባል የሆኑ የአፍሪካ አገሮች በተኩላ ዘራፊ ሙሰኛ ገዥ ቡድኖች የሚሸከረከሩ ናቸው፡ ፡ “ዘራፊነት የአፍሪካ አምባገነናዊነት ከፍተኛው ደረጃ” በሚል ርዕስ ባቀረብኩት ትችት ህልዮት ቀምሬ ነበር፡ ፡ ማዳም ሾርት በገንዘቡ በኩል ትክክል ናቸው። በኢትዮጵያ ያለውን ዘራፊ ገዥ አካል በEITI ካለው ከትክክለኛ ቦታው ታላቁ የሙስና ጠረጴዛ ላይ ለምን ነጠሉት? በእውነት ይህ ጉዳይ ፍትሀዊ አይደለም። የበለጠ ከዚህ በተለየ መልኩ ማዳም ሾርት የእኔን ነጥብ በትክክል አረጋግጠውታል። በእርግጥ EITI ማዕከላዊ የማዕድን ሙስና ቡድን ነው። አሊባባን እና 40ዎቹን ሌቦች አስታወሰኝ፡ ፡ አሁንም በጣም በተለየ መልኩ ማዳም ሾርት በኢትዮጵያ ያለው ገዥ አካል የአባልነት ጥያቄው ተቀባይነት እንዲያገኝ እና በEITI ሲስተም እንዲገባ ለማድረግ በግልጽ ደብዳቢያቸው ላከናወኑት የሞት የሽረት ትግል በጣም ላመሰግናቸው እፈልጋለሁ። ከልብ በመነጨ መልክ ላደረጉት የትግል መንፈስ አደንቃቸዋለሁ፡ ፡ ማዳም ሾርት በእርሳቸው መንገድ የማይቆሙትን ማንንም ቢሆን የማዋረድ ስብእና ያላቸው ሰው ናቸው።

የገዥውን አካል የአባልነት ጥያቄ ቦርዱ እንዲያጸድቀው በማስገደድ ማዳም ሾርት ታላቅ አገልግሎት አበርክተውልናል። ምንም በውል ሳያጤኑት EITI በእውን ምን ዓይነት ተቋም እንደሆነ እንዲሁም በህገወጥ መንገድ ጥቅም ለማግኘት የማስጠበቂያ የጫጫታ ቡድን መሆኑን አጋልጠዋል። በተደራጁ የወንጀለኞች ድርጅቶች የጥቅም ማስጠበቂያ የጫጫታ ቡድኖች የፖሊስ እና የፍትህ አካላቱ በትክክል ህዝቡን ማገልገል ሲሳናቸው ወይም ደግሞ ለማህበረሰቡ የህግ ጥበቃ ማቅረብ ሳይችሉ ሲቀሩ የሚከሰቱ ናቸው። “በጥቂት የክፍያ ገንዘብ” ሰበብ በሸፍጥ የተካነው ወንጀለኛ ለደንበኞቹ “ህግ እና ስርዓትን” ያስከብራል፣ እናም በሌሎች ወሮበሎች እና አዲስ ወንጀለኞች እንዳይዘረፉ ጥበቃውን ሊያረጋግጥ ይችላል።

አብዛኞቹ የEITI አባል አገሮች በራሳቸው የህግ ተቋማት ሙስናን የመቆጣጠር አቅሙ የላቸውም። ብዙዎቹ አባል አገሮችም የአንድ ሰው፣ የአንድ ፓርቲ የፈላጭ ቆራጭነት ስርዓትን የሚያራምዱ ናቸው። የፖሊቲካ ተቋማቱ እስከ አጥንታቸው ድረስ በዘለቀ የሙስና ነቀርሳ የበከቱ ናቸው። የይስሙላ ፓርላሜንታሪ ስርዓቶች አሏቸው፡ ፡ አቃቤያነ ህጎቻቸው በትምህርት፣ በማህበራዊ እና በሞራል ስብዕና አቅመቢስ የሆኑ ድሁር ወሮበላ ዘራፊዎች እና ጽናት የሌላቸው የእመኑልኝ የህግ መጽሐፍትን በብብታቸው ሸጉጠው የሚዞሩ የፓርቲ አባላት ናቸው። የፍትህ ስርዓቱ ከገዥው አካል አመራሮች የኋላ ኪስ የሚገኝ ስርዓት ነው። የጸረ ሙስና ኮሚሽኖች የፖሊቲካ ተቀናቃኞቻቸውን፣ በገዥው አካል ላይ የሚነሳሱትን ሰላማዊ አመጾችን ጨምሮ ለማጥቂያነት በእራስ የተሞሉ የርቀት አነጣጣሪ ሚሳይሎች ናቸው። የህግ የበላይነት የለም፣ ያለው የደናቁርት የዘራፊዎች ህግ ብቻ ነው።

በአሁኑ ጊዜ EITI በአፍሪካ እና በሌሎችም አገሮች ለዘመናት የሚዘልቅ የማዕድን ሙስና የተንሰራፋበት አዲስ ዓለም አቀፋዊ ስርዓት ለማንበር ዝግጅቱን አጠናቅቋል። ላለፉት አስርት ዓመታት EITI ያከናወናቸው ተግባራት እንግዲህ ይህንን ጉዳይ እውን ለማድረግ ነው። እውነት ለመናገር EITI በእራሱ የሙስና ቡድን በሙስና የተዘፈቁ ገዥዎችን ለመከላከል የተቋቋመ ቡድን ነው። የአገራቸውን የተፈጥሮ ሀብት የዘረፉትን እና የመዘበሩትን ወሮበላ ዘራፊዎች መልሶ ለመዝረፍ የተቋቋመ ሰላማዊ ድርጅት ነው። ሁሉም በሙስና የተዘፈቁ ገዥ አካላት እንደገና ለመወለድ እና የEITIን ስርዎ መንግስት ለመቀዳጀት የሚከተሉትን ሂደቶች መከተል ይጠበቅባቸዋል። 1ኛ) የአባልነት መጠየቂያ ቅጹን መፈረም እና የEITIን የጥያቄ እና መልስ መዝሙሩን ደጋግሞ ማነብነብ፣ 2ኛ) መጠመቅ እና በ EITI ቁሶቹ መቀባት፣ 3ኛ) ቀደም ሲል ለተሰሩት ጥፋቶች በህዝብ ፊት ጥቂት ንስሀ የመግባት ተግባራትን ማከናወን፣ 4ኛ) ቀደም ሲል ለተፈጸሙ የሙስና ተግባራት ሁሉ ይቅርታ ማድረግ፣ 5ኛ) ከሙስና ወደ ንጹህነት እስኪመለሱ ድረስ የሶስት ዓመታት የዝግጅት ጊዜ መስጠት የሚሉት ናቸው።

ለዘራፊ ገዥ አካላት ይህ ታላቅ ቅሌት ነው። የEITIን የከሀዲነት ባጅ ለማጥለቅ እና ከሙስና ምን ያህል ነጻ እንደሆኑ በባዶ ኩራት በታጀለ መልኩ ለማሳመን በዝግጅት ላይ ናቸው። የEITI ባጅ በኢትዮጵያ ላሉት በሙስና የተዘፈቁ ዘራፊዎች የባዶ ዲስኩር የጉራ ችርቻራ መብትን ያጎናጽፋቸዋል፡ ፡ የEITIን የአባልነት ፈቃድ በማግኘት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እና በኢትዮጵያውያን/ት የዲያስፖራ ማህበረሰብ አባላት ላይ በእውነተኛነት ላይ ተመስርቶ የተገኘ ፈቃድ አስመስሎ ለመቅረብ በሸፍጥነት መጠቀሚያ ያድርጉታል። "ሂዩማን ራይትስ ዎች አፍንጫችሁን ላሱ! የኢትዮጵያ የዲያስፖራ አፍንጫችሁን ላሱ! እዩ እንግዲህ ተመልከቱ እንደ አዳኝ ውሻ ጥርስ ንጹህ ነን፤ እናም ከዚህ በላይ ማረጋገጫ የለም ይህንን ልናረጋግጥላችሁ እንችላለን!“:: የማዕድን ሙስናውን ከጥርጣሬም በላይ ከተጨባጩ ሁኔታ በላይ፣ ከቦርዱ በላይ እና ከህግ በላይ አጠናክረው

ወደ ገፅ 12 ይዞራል

በኢትዮጵያ ያለው ገዥ አካል የEITI አባል እንዲሆን የተሰጠው ውሳኔ ፍጹም በሆነ ሙስና የተደረገ እና የማስመሰያ የአባልነት ተውኔት ነው።

በል ግፋ በል ግፋ ጨምር፣ ያልፋል አንድ ሰሞን ችግርና ጦር፡፡

ከፋኩራ ስነ - ቃል የተወሰደ

ታዴዎስ ታንቱ

የመ.ሣ.ቁጥር 43414

አሁን የምንገኘው በትግሬ ጠቅላይ ግዛት በማይጨው መሬት ላይ ነው፡፡ ሰዓቱ ውድቅት ሌሊት በመሆኑ የኢትዮጵያ ሠራዊት በየአቅጣጫው በከፍተኛ የውጊያ ሥነ-ልቦና በተጠንቀቅ ላይ ይስተዋላል! ዕንቅልፉን የተኛ የሠራዊት አባል ማንም አልነበረም፡፡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ዕንቅልፍ አልወሰዳቸውም፡፡ ዓይኖቻቸውን ጨፍነዋል! በአዕምሮአቸው ግን ከአዕምሮአቸው ጋር ውይይት ይዘዋል! ማለቂያ የሌለውን ሐሳብ በሐሳብ ሲያስተናግዱ ይስተዋላል! ሐሳብ መቼ ማለቂያ ኖሮት ያውቃል? ሰው ያስባል! ያስባል! ያስባል! ሐሳብ በሐሳብ ይሻራል! ሐሳብ በሐሳብ ይተካል! ሁሉም ያስባል! ያስባል! ያስባል! ራሶች፣ ደጅአዝማቾችና በልዩ ልዩ ባህላዊ ወታደራዊ ማዕረግ እስከ ዝቅተኛ እርከን የነበሩ ሁሉ በሐሳብ ባሕር ሰምጠዋል! በዘመናዊ ወታደራዊ ማዕረግ ከክቡር ዘበኛ የዘመቱ መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረግተኞችም በውድቅት ሌሊት በሐሳብ ነጉደዋል! ማንም እንዳይፎክር በቀጥታ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትዕዛዝ ወርዷል! ይህ የታሪክ ድምፅ ነው! በቀዳሚ ዘማች መካከል እሳትም እንዳይነድድ ወታደራዊ ትዕዛዝ ተሰምቷል፡፡ መጠራራትም ተከልክሏል! በሩቅ ርቀት ከኋላ በመሆን እሳት ማንደድ ግን ፈቅዷል! ወራሪው ኃይል የኢትዮጵያ ጀግኖች በዚያው ርቀት ልክ እንደነበሩ አድርጎ ግምት እንዲወስድ ታስቧል! የማሳሳቻ ዘዴ መሆኑ ታውቋል! አሁን የኢትዮጵያ ጀግኖች ወራሪው ኃይል ከመሸገበት ለመድረስ ጥቂት ርቀት ይቀራቸዋል! ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሌሊቱ በአሥር ሰዓት በእንቅስቃሴ ላይ ታይተዋል፡፡ ሠራዊቱ ለውጊያ ዝግጁ! ለእናት ሀገሩ መስዋዕት ለመሆን ዝግጁ! ከትግሬ ጠቅላይ ግዛት ከማይጨው ጦር ሜዳ! መጋቢት 22 ለመጋቢት 23 አጥቢያ 1928 ዓ.ም! የውጊያ ትዕዛዝ ግን አልተሰጠም፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ወራሪው ኃይል ምሽግ ተጠግቷል፡፡ በዚህ መካከል በድንገት የተኩስ ድምፅ ተሰማ፡፡ በተከታታይ ሦስት ጥይቶች ተተኮሱ! ማን እንደ ተኮሳቸው አይታወቅም፡፡ ሦስቱንም ጥይቶች አንድ ሰው ተኩሷል ወይስ የተለያዩ ሰዎች? ለማወቅ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ሦስቱም ጥይቶች ከኢትዮጵያ ሠራዊት እንደ ተተኮሱ ግን ታውቋል! ያም ሆነ ይህ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ለአፀፋ ተኩስ አልዘገየም፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊትም ተኩሱን አቀለጠው፡፡ ጦርነቱ ተፋፋመ! በማይጨው ላይ እሳት ነደደ! ፍልሚያው ተጋጋለ! የኢትዮጵያ ሠራዊት በኋላ ቀር መሣሪያ በርትቶ ይዋጋ ገባ! ከፍተኛ ወኔ አሳይቷል! ቁርጠኝነትንም አንፀባርቋል! በዚህ ሂደት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን አምስት ምሽጎችም አስለቅቋል! ጦርነቱ እየጋለ ሔዷል! ድም! ድም! ድም! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ካካካካ! ካካካካ! ካካካካ! ቡም! ቡም! ቡም! ይህ የጥንታዊት ኢትዮጵያ የማይጨው ጦርነት የጦር መሣሪያ ተኩስ ድምፅ ነው! መጋቢት 22 ለመጋቢት 23 አጥቢያ! 1928 ዓ.ም!

የፋሽሽት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሹማምንት የኢትዮጵያ ሠራዊትን ጀግንነት ለመገንዘብ ጊዜ አልወሰደባቸውም፡፡ ኋላ ቀር የጦር መሣሪያ የታጠቀ ቢሆንም በቀላሉ አልተበገረም፡፡ በዚህ ሂደት ብዙ የወራሪው ኃይል ተዋጊዎችን ደመሰሰ! የወራሪው ኃይል ወታደራዊ ሹማምንት እንደ ተነበዩት በቀላሉ ድልን ለመጎናጸፍ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በዚህ ምክንያት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ቁጥሩ የበዛ የጦር አይሮፕላኖችን ከሰሜን ኢትዮጵያ አስነስቶ በጀግናው የኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ቦምብ አዘነበ! በምድር ላይ ባልተመጣጠነ የጦር መሣሪያ እየተዋጉ ሲሆን አሁን ደግሞ የአይሮፕላን ቦምብ ሲጨመርበት የኢትዮጵያ ሠራዊት ጉዳት የከፋ ሆኗል! ግፈኛው ወራሪ ኃይል የመርዝ ጭስም በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ በብዛት አርከፈከፈ፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ሰራዊት ከመዋጋት አላፈገፈገም! ለሕይወቱ ሳይሳሳ ተዋግቷል፡፡ ጦርነቱ በነጋታው መጋቢት 23 ቀን 1928 ዓ.ም በከፋ መልኩ ቀጠለ፡፡ በማይጨው ጦር ሜዳ የኢትዮጵያ ጀግኖች ደም ጎረፈ! የሰው ስጋ ተበለተ! የቆራጥ ጀግኖች አካል በከባድ መሣሪያ ተበተነ! ለሀገሩ አንድነትና ሉዓላዊነት ቀናዒ የሆነው የኢትዮጵያ ጀግና በተለይ ከአውሮፕላኖች በተለቀቁ ቦምቦችና የመርዝ ጭስ ክፉኛ ተጎድቷል! ውጊያው ግን አሁንም ቀጥሏል! መጋቢት 23 ቀን 1928 ዓ.ም! በየመስመሩ ተኩሱ ተፋፍሟል! እስከ ማታም ተኩስ ይሰማ እንደነበር ታውቋል! በዚህ ሂደት በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ የደረሰው ጉዳት የውጊያ ሥነ ልቦናውን በመበታተኑ ጦርነቱን በመቀጠል ውጤት ማስመዝገብ አዳጋች ሆነ፡፡ በዚህ ምክንያት በየመስመሩ የተሰማራው ዘማች ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ትዕዛዝ ወረደ፡፡ ትዕዛዙም ተፈጻሚ ሊሆን በቅቷል፡፡ የማይጨው ጦርነት ተጠናቀቀ፡፡ ይህ በታሪካችን በጥንታዊት ኢትዮጵያ በማይጨው ጦርነት የኢትዮጵያ ሠራዊት የትግልና የመሥዋዕትነት ድምፅ ነው! ከትግሬ ጠቅላይ ግዛት ከማይጨው ጦር ሜዳ! መጋቢት 22 ለመጋቢት 23 አጥቢያ 1928 ዓ.ም! የውጊያ ትዕዛዝ ግን አልተሰጠም፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ወራሪው ኃይል ምሽግ ተጠግቷል፡፡ በዚህ መካከል በድንገት የተኩስ ድምፅ ተሰማ፡፡ በተከታታይ ሦስት ጥይቶች ተተኮሱ! ማን እንደ ተኮሳቸው አይታወቅም፡፡ ሦስቱንም ጥይቶች አንድ ሰው ተኩሷል ወይስ የተለያዩ ሰዎች? ለማወቅ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ሦስቱም ጥይቶች ከኢትዮጵያ ሠራዊት እንደ ተተኮሱ ግን ታውቋል! ያም ሆነ ይህ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ለአፀፋ ተኩስ አልዘገየም፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊትም ተኩሱን አቀለጠው፡፡ ጦርነቱ ተፋፋመ! በማይጨው ላይ እሳት ነደደ! ፍልሚያው ተጋጋለ! የኢትዮጵያ ሠራዊት በኋላ ቀር መሣሪያ በርትቶ ይዋጋ ገባ! ከፍተኛ ሰራዊት በማይጨው ጦርነት ለምን ተረታ?

1. በማይጨው ጦርነት የኢትዮጵያ ሠራዊት በአሰላለፍ ዘመናዊ አልነበረም፡፡ የጦር አበጋዞቹ ዘመናዊ የውትድርና ትምህርት ያልቀሰሙ ከመሆናቸውም በላይ የሠራዊቱ አሰላለፍ ባህላዊ እንደ ነበር ይታወቃል፡፡ በአድዋ ጦርነት ወቅት ከነበረው ተመሣሣይ ነበርና፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከኮሎኒያሊስት ኢጣሊያ ጊዜ ብዙ መሻሻል አድርጎ ተመልሷል፡፡ ይህ ሁኔታ የኢትዮጵያ ሠራዊት እንዲያፈገፍግ አስገድዶታል፡፡ አንዱ ምክንያት እንግዲህ የአሰላለፍ ችግር ነበር ማለት ይቻላል፡፡

2. ባልታሰበና ባልተጠበቀ ሁኔታ በጦርነት ወቅት አንዳንድ የጦር አበጋዞች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ክሕደት ፈፅመዋል፡፡ በዚህ ምክያት በጦር መሪዎች መካከል አንድነት አልነበረም፡፡ ባሕር ምድር በኢጣሊያ ሥር እንደነበረች ይታወሣል፡፡ ወራሪው ኃይል መሃል ሀገርን ለመያዝ የተንደረደረው ከባሕር ምድር ነበር፡፡ ወራሪው ኃይል ወታደራዊ አቅሙን ሁሉ ሰብስቦ በባሕር ምድር ላይ ተደራጅቶ በነበረበት ወቅት ራሱን እንደ መስፍን ይቆጥር የነበረው ደጅአዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉልማ የተባለ ግለሰብ ሁለት ሺህ ያህል ሰዎች አስከትሎ ከመቀሌ ተነስቶ በመሄድ እናቱን ኢትዮጵያን በመካድ ለፋሽሽት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አድሯል፡፡ ወራሪውን ኃይል ግማሽ መንገድ ድረስ ሄዶ የተቀበለው ይህ ግለሰብ ቀደም ሲል የንጉሠ ነገሥቱን ልጅ ልዕልት ዘነበ ወርቅ ኃይለ ሥላሴን አግብቶ ተከብሮ ይኖር የነበረ ከመሆኑም በላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታማኝ በመምሰል ለንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤዎችን ይጽፍ እንደ ነበር በታሪክ ተመልክቷል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በወቅቱ አስመራ እየሔደ ኢትዮጵያን ለማስያዝ በሚችለበት ሁኔታ ላይ የወራሪው ኃይል ወታደራዊ ሹማምንትን ያማክር እንደነበር ታውቋል፡፡ ይህ ባንዳ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከሀገራችን ሲባረር ወደ ስዌልስ ደሴት ፊርጥጦ ነበር፡፡ በእንግሊዞች እገዛ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ለፍርድ ሊቀርብ ችሏል፡፡ እናት ሀገርን በመክዳት ወንጀል ተከስሶ በሞት እንዲቆጣ ተወስኖ እንደነበርም ታውቋል፡፡ ነገር ግን በውል ባልታወቀ ምክንያት የሞት ቅጣቱ ሳይፈፀምበት ቀርቶ እስከ ደርግ ዘመነ መንግስት ድረስ በሕይወት እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ወራሪውን የፋሽስት ኢጣሊያ ኃይል በማይጨው ላይ መክቶ ለመመለስ የኢትዮጵያ ሠራዊት ማቁን ጨርቁን ሳይል በወኔ በተነሣበት ወቅት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ክሕደት ከፈፀሙት መካከል አንዳንድ የጎጃም የጦር አበጋዞች ይገኛሉ፡፡ ይህንኑ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ራሣቸው ለጎጃም ሕዝብ ባስተላለፉት ዐዋጅ ጠቅሰዋል፡፡ እንዲህ ይነበባል!

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ!

- - -

- - - ደጅአዝማች ገሠሠ፤ ፊታውራሪ ተአምራት፤ ፊታውራሪ ገሠሠ ንጉሤ፤ ፊታውራሪ ዘለቀ ካሣ፣ ፊታውራሪ ዘለቀ ወሌ፤ ቀኝአዝማች አየለ ኃይሉ፣ ቀኝአዝማች መርዕድ ዋሴና ቀኝአዝማች ዘለቀ አሠጌ አገራቸውን ኢትዮጵያንና ንጉሣቸውን እኔን ከድተው ከዘመቻ መመለሳቸው እንክርዳድ ከስንዴ መካከል እንደሚበቅል ያህል ነው፡፡ ቢሆንም ለጊዜው ያገርህን የጎጃምን ስም ለማጥፋት ነው እንጂ ሌላው ይቅርና ራሳቸውንም ለማዳን እንዳይችሉ አንተው ታውቃለህ፡፡

- - - - ይህን አዋጅ ከሰማህ በኋላ ወታደር በወታደርነትህ እነዚህን ጠላቶቼን ተከትለህ ስትወሰልት የተገኘህ እንደሆነ ምሕረት የሌለው ቅጣት እቀጣሃለሁ፡፡

እንግዲህ ልብ እንበል! እያንዳንዱ የጦር አበጋዝ ብቻውን ሳይሆን ሰው ይዞ እንደሚከዳ አንርሣ! በዚህ ምክንያት ከኢትዮጵያ ሠራዊት የሰው ኃይል ይቀንሳል፡፡

3. ኢትዮጵያ በቀድሞ ዓለም ማህበር ላይ ከፍተኛ እምነት መጣሏ ሠራዊቱ በማጨው ጦርነት ድል እንዳይቀዳጅ የበኩሉን አሉታዊ አስተዋፅኦ ማድረጉም በምክንያትነት በታሪክ ተመልክቷል! በእርግጥም ኢትዮጵያ በማህበሩ ላይ ከፍተኛ እምነት ጥላ ነበር፡፡ ምክንያቱም እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ ኢጣሊያም የማህበሩ አባል ስለነበረች የወረራ አቋም እንደማታራምድ ገምታ ነበርና ነው፡፡ ይህም ብቻ አልነበረም፡፡ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረድ ብትንቀሳቀስ የተቀሩት አባል ሀገሮች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በተግባር እንደሚሰለፉ መገመቷም ትልቅ ስሕተት እንደ ነበር ታውቋል! በዚህ አቋም የኢትዮጵያ የጦር አበጋዞች የሰራዊቱን የውጊያ ዝግጁነት ከማሳደግ ይልቅ ማንም ሀገራችንን እንደማይነካ ወደ ማመን አዘንብለው ተስተውለዋል፡፡ ይህ ተስተውለዋል፡፡ ይህ ደግሞ የሠራዊቱን የውጊያ ስነ ልቦና በከፍተኛ ደረጃ ጎድቶታል!

4. የጦር መሳሪያ ያለመመጣጠን በማጨው ጦርነት ለኢትዮጵያ ሰራዊት መፈታት አንድ ተጨባጭ ምክንት እንደ ነበር ታውቋል፡፡ እርግጥ ነው፡፡ በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልና በኢትዮጵያ ሰራዊት መካከል በጣም ሰፊ የትጥቅ ልዩነት ነበረ፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በጣም ብዙ ታንክና የጦር አይሮፕላን ታጥቆ መጥቷል፡፡ የኢትዮጵያ ሰራዊት ግን ባመዛኙ በነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያ ተሰልፏል፡፡ በውስን መልኩ የቡድን የጦር መሳሪያዎች በእርግጥ ነበሩት፡፡ ነገር ግን ከቁጥር የሚገቡ አልነበሩም፡፡ በዚህ ምክንያት ሰፊ የጦር መሳሪያ ልዩነት ተስተውሏል፡፡ በጣም ሰፊ ልዩነት ታየ! የኢትዮጵያ ሰራዊት ያለ ጥርጥር በጀግንነት ይበልጥ ነበር፡፡ ከፍተኛ የሀገር ፍቅር ስሜትም ነበረው፡፡ ሆኖም በኋላ ቀር የጦር መሳሪያ ይህን በዘመኑ እጅግ ዘመናዊ ትጥቅ የነበረውን ኃይል መክቶ መመለስ የሚቻል አልነበረም፡፡ በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ሰራዊት የግድ ማፈግፈግ ነበረበት፡፡

እንግዲህ ልብ እንበል! የኢትዮጵያ ሰራዊት በኋላ ቀር የጦር መሳሪያ ግዳጁ የጠየቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍሏል፡፡ ታሪክ የጣለበትን የወር ተረኝነት ግዴታውን ተወጥቷል፡፡ ነገር ግን ከአቅም በላይ ሆኖበታል፡፡ ከአየር ላይ በተለቀቀ የመርዝ ጭስ ብዙ ጀግኖች ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የአሸናፊነት ስነ ልቦና እንደ ታጠቀ የማይጨው ጦርነት ሊቋጭ በቅቷል፡፡ ይህ የኢትዮጵያ ሰራዊት የፀረ-ፋሽስት ተጋድሎ ቀጥታ ድምፅ ነው! ከትግሬ ጠቅላይ ግዛት ከማይጨው ጦር ሜዳ! መጋቢት 23 ቀን 1928 ዓ.ም!

ስለማይጨው ጦርነትና ስለኢትዮጵያ ሰራዊት ተጋድሎ ስናወጋ በዘመኑ ህዝቡን ለጦርነት ለማነሳሳት የተደረጉትን ቅስቀሳዎችንና አዋጆችንም ማውሳቱ አግባብነትን እንዳለው ይሰማናል፡፡ በእርግጥ በየዘርፉ የተደረጉትን ቅስቀሳዎችና አዋጆች አንድ ባንድ በዝርዝር ለማቅረብ አይቻልም፡፡ ሰፊ ቅስቀሳ መደረጉ ግን በታሪክ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ቅስቀሳው ደግሞ በግዜው በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ህዝቡን ለዘመቻ ለማነሳሳት በቂው እንደ ነበረ ታውቋል፡፡ በዘመኑ የጦርነት ቅስቀሳ ነጋሪት በማስጎሰም ተከናውኗል፡፡ ፉከራዎችና ሽለላዎችም የቅስቀሳ ስራ አካል እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ የማይጨው ጦርነት ከመከፈቱ በፊት በእነዚህና በመሳሰሉት ስልቶች በህዝቡ መካከል ቅስቀሳ ተደርጓል፡፡ የሐይማኖት አባቶችም በየቤተ ክርስቲያኑ ግፈኛ ወራሪ ኃይል መምጣቱን በማስረዳት ህዝቡን ቀስቅሰዋል፡፡ ቅስቀሳው ህዝቡ ለነፃነቱና ለአንድነቱ በፀረ ፋሽስት ትግል እንዲነሳሳ በማድረግ በኩል ያደረገው አስተዋፅዖም ከፍተኛ ግምት

እንግዲህ ልብ እንበል! የኢትዮጵያ ሰራዊት በኋላ ቀር የጦር መሳሪያ ግዳጁ የጠየቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍሏል። ታሪክ የጣለበትን የወር ተረኝነት ግዴታውን ተወጥቷል። ነገር ግን ከአቅም በላይ ሆኖበታል። ከአየር ላይ በተለቀቀ የመርዝ ጭስ ብዙ ጀግኖች ጉዳት ደርሶባቸዋል፡ ፡ በዚህ ምክንያት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የአሸናፊነት ስነ ልቦና እንደ ታጠቀ የማይጨው ጦርነት ሊቋጭ በቅቷል። ይህ የኢትዮጵያ ሰራዊት የፀረ-ፋሽስት ተጋድሎ ቀጥታ ድምፅ ነው! ከትግሬ ጠቅላይ ግዛት ከማይጨው ጦር ሜዳ! መጋቢት 23 ቀን 1928 ዓ.ም!

ወደ ገፅ 6 ይዞራል

ሰላማዊ ትግል - ጽንሰ ሀሳብ እና አፈጻጸም (2)

ግርማ ሞገስ

የሰላማዊ ትግል ማራመጃ መሳሪያዎች

የሰላማዊ ትግል ማራመጃ መሳሪያዎች ቁጥር 200 ይደርሳል። ለጥናት እንዲያመች እነዚህ 200 መሳሪያዎች በሶስት አብይ ክፍሎች ተከፍለዋል። እነሱም፡- (1ኛ) ተቃውሞ እና ማግባባት (Protest and Persuasion)፣ (2ኛ) ትብብር መንፈግ (non-cooperation)፣ (3ኛ) ጣልቃ መግባት (intervention) የተባሉት ናቸው። የኢትዮጵያን ባህል ከግንዛቤ በማስገባት ከ200 መቶ ውስጥ በኢትዮጵያ ሊሰሩ ከሚችሉት ውስጥ ዋና ዋናዎች ናቸው ካልኳቸው ውስጥ ጥቂቱ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

(1ኛ) ተቃውሞ እና ማግባባት (Protest and Persuasion)፡- በዚህ አብይ ክፍል በውስጡ ከተካተቱት መሳሪያዎች ውስጥ ጥቂቱ የሚከተሉት ናቸው።

(ሀ) በድረ ገጾች ወይንም በጋዜጣዎች በሚቀርቡ ጽሑፎች ወይንም ህዝብ በተሰበባቸው አደባባዮች በሚደረጉ ንግግሮች (በሚሰጡ መግለጫዎች) ተቃውሞን (ወይንም ድጋፍን) ማሳወቅ... ወ.ዘ.ተ.

(ለ)መፈክሮች እና ባነሮች (Banners) መጠቀም፣ ጽሑፎች ማሰራጨት፣ በግድግዳዎች ላይ መጻፍ፣ እንዲሁም ሲዲ፣ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን በመጠቀም መልዕክት ለህዝብ ማድረስ ማድረግ ወ.ዘ.ተ.

(ሐ) ድራማዎች እና ሙዚቃዎች በመጠቀም በህብረተሰቡ ውስጥ የሚፈጸሙ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሞራላዊ ስህተቶችን መቃወም። ሁለት ምሳሌዎች ልስጥ፡- የመጀመሪያው ምሳሌ አንድነቶች በአዲስ አበባ ቀበና ባደረጉት የሚሊዮኖች ለነፃነት ዘመቻ ላይ ያሳየው ሶስት የእስር ቤት ልብስ የለበሱ ወጣቶች ጥሩ ድራማ ነው። ድራማው ብዙ ይናገር ነበር። ሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ ‹‹ዋሽቶ ለመኖር›› የሚለው የቴዲ አፍሮ ዘፈን ነው። ዘፈኑ ሙስናን ከሞራል አንጻር ይቃወማል። ጥሩ የሰላም ትግል መሳሪያ ነው።

(መ) በሰላም ትግል ላይ ለተገደሉ (ሰማዕታት) ክብር በመስጠት ገዳዮችን እና ድርጊቱን መቃወም፣ ለተገደሉ የፖለቲካ ሃዘን ባደባባይ ማድረግ፣ እሬሳን ተሸክሞ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ እና የቀብር ስርዓት መፈጸም፣ ‹‹የሰማዕታት ቀን›› መሰየም፣ በሰማዕታት መቃብሮች ላይ ሐውልት ማሰራት እና በሐውልታቸው ላይ የሞቱበትን ምክንያት መጻፍ... ወ.ዘ.ተ.

በዚህ አብይ ክፍል በትንሹ 54 ያህል የሚሆኑ የተለያዩ የሰላም ትግል መሳሪያ አይነቶች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ የሰላም ትግል መሳሪያዎች ብቻቸውን የመንግስትን የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ለመቆጣጠር እና ለማዳከም አያስችሉም። በአብዛኛው ተምሰሌታዊ (symbolic) ናቸው። ፋይዳቸው ህዝብ ማነቃቃት ስለሆነ በፖለቲካ ኃይል ምንጮች ላይ የሚያደርሱት ጥቃት ቀጥተኛ ሳይሆን ተዘዋዋሪ ነው።

(2ኛ) ትብብር መንፈግ፡- የመንግስትን የፖለቲካ ኃይል ምንጮች በመቆጣጠር እና በማድረቅ የመንግስትን የፖለቲካ ኃይል (አቅም) ለመቆጣጠርም ሆነ ከስልጣን ለማውረድ መድሃኒት የሆነ የሰላም ትግል መሳሪያ ነው። ለምሳሌ ያህል ምርጫን ተከትሎ መንግስት የምርጫን ውጤት አልቀበልም ሲል ትብብር የመንፈግ ሰላማዊ ትግል ይደረጋል። በዚያን ጊዜ የሚደረግ ትብብር መንፈግ የሚያስተላልፈው መልዕክት፡- ‹‹እኛ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ (We the People of Ethiopia) ቀደም ሲል የለገስንህን ትብብር ነፍገንሃል እና ከስልጣን ውረድ!›› የሚል ነው። ትብብር መንፈግ የተባለው አብይ ክፍል ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ማህበራዊ ትብብር መንፈግ የሚለውን ክፍል (ከ 10 በላይ የተለያዩ መሳሪያዎች አሉት) ወደጎን በመተው የቀሩትን ሁለቱ ክፍሎች እንደሚከተለው በአጭር በአጭሩ አቅርቤያቸዋለሁ።

(ሀ) ኢኮኖሚያዊ ትብብር መንፈግ፡-

ኢኮኖሚያዊ ትብብር መንፈግ በሁለት ይከፈላል። የመጀመሪያው የንግድ ግንኙነት በማቋረጥ (የንግድ እገዳ ወይንም እቀባ) ከፖለቲካ ባላንጣ ጋር አለመገበያየት ነው። በውስጡ 26 ያህል የሰላም ትግል መሳሪያዎች አሉት። መገበያየት ማቋረጥ በአገር ውስጥ እንዲሁም በአገሮች መካከል ይፈጸማል። ሁለተኛው ኢኮኖሚያዊ ትብብር መንፈግ ደግሞ ስራ ማቆም (Strikes) ሲሆን 22 ያህል የሰላም ትግል መሳሪያዎች አሉት። ምሳሌ፡- የእርሻ፣ የኢንዱስትሪ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የትራንስፖርቴሽን (የባቡር፣ የአውቶቡስ፣ የታክሲ፣ የአየር መንገድ፣ ወ.ዘ.ተ.)፣ የማዕድን፣ የመንግስት መስሪያ ቤት፣ ወ.ዘ.ተ. ሰራተኞች ለየብቻቸው ወይንም በህብረት የሚያደርጉት የስራ ማቆም። ይህ ሁለተኛው ትብብር መንፈግ በኃይል ወይንም በመፈንቅለ መንግስት ስልጣን ላይ የወጣን ወይንም የህዝብ ድምጽ አጭበርብሮ በስልጣን ለመቆየት የሚሞክር መንግስትን ደሞዝ የመክፈል አቅም በመንፈግ የፖለቲካ ኃይል (አቅም) ይቆጣጠራል። ይህ ሰላማዊ ትግል ቀጣይነት ካለው የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ያደርቃል። ይህ ከሆነ ደግሞ መንግስት ለወታደሩ፣ ለጦሩ፣ ለመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞች የሚከፍለው ደሞዝ ሊያጣ እና እንደቀድሞው መግዛት ሊያቅተው ይችላል። ለማንኛውም ዴሞክራሲን ለማምጣት በሚደረግ ሰላማዊ ትግል ውስጥ ይህ የትግል መሳሪያ ስራ ላይ ሲውል በዘር እና በሃይማኖት ክፍፍል እንዳይበከል (contaminate እንዳይደረግ) ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

(ለ) ፖለቲካዊ ትብብር መንፈግ፡-

ይህ ክፍል 38 ያህል የሰላም ትግል መሳሪያዎች አሉት። ለናሙና ያህል አራት ምሳሌዎች እንመልከታለን።

(ሀ) የመጀመሪያው የፖለቲካ ታማኝነትን መንፈግ፡- (የመንግስትን የገዢነት ስልጣን መፈፍ) (Rejection of authority) የሚለው ሲሆን ምሳሌ፣ ዜጎች በየድረ ገጹ፣ በየመጽሐፉ፣ በየመጽሔቱ እና በየጋዜጣው ላይ የሚፅፉት የፖለቲካ ትችት፣ ኩነና እና የትግል ቅስቀሳ፡ እንዲሁም የመንግስት ባለስልጣኖች፣ ጀነራሎች እና በውጭ የሚሰሩ ዲፕሎማቶች ስልጣናቸውን እየለቀቁ ሰላማዊ ትግሉን ሲቀላቀሉ የፖለቲካ ታማኝነታቸውን ነፈጉ ማለት ነው።

(ለ) ሁለተኛው ዜጎች ለመንግስት የፖለቲካ ትብብር ሲነፍጉ (Citizens' non-cooperation with government) ተፈጻሚ ይሆናል። ምሳሌ፣ ዜጎች በምርጫ ወቅት ድምጻቸውን በስልጣን ላይ ለሚገኘው ፓርቲ በመንፈግ ለተቃዋሚ ፓርቲ ሲለግሱ፣ ዜጎች በነፃነት አደባባይ በሚሊዮኖች ሆነው በመውጣት መንግስት ከስልጣን እንዲወርድ ሲጠይቁ፣ ወ.ዘ.ተ.

(ሐ) ሶስተኛው የመንግስት ሰራተኞች (ሲቪል ሰርቫንቱ/ቢሮክራሲው) ለመንግስት የፖለቲካ ትብብር ሲነፍጉ (Government personnel's non-cooperation with government) ተፈጻሚ ይሆናል። ምሳሌ፡- የአስተዳደር ስራ በተገቢው አለመስራት፣ የጸጥታ ክፍል ሙሉ ትብብር ሲነፍግ፣ ፖሊስ ፈልገህ እሠር የተባለውን ግለሰብ እያየ እንዳላየ ሲሆን፣ ፖሊስ ግደል ሲባል ከመግደል ወደ ሰማይ ሲተኩስ ወይንም እንቢ ሲል፣ ወ.ዘ.ተ.

(መ) አራተኛው የዓለም አቀፍ መንግስታት ለመንግስት የፖለቲካ ትብብር መንፈግ (International governmental action) ነው። ምሳሌ፡- ተቃዋሚዎች ባደረጉት ከፍተኛ ዝግጅት በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ምርጫውን በድብቅ መስረቅ እንዳይችል በማድረጋቸው አይን ባወጣ መንገድ የምርጫውን ውጤት አልቀበልም ሲል ዓለም አቀፍ ህብረተሰብ በስልጣን ላይ ለሚገኝ መንግስት ህጋዊ ዲፕሎማሲያዊ እውቅናን ሲነፍግ ወይንም ሲገፍ ወይንም ሲያቋርጥ።

(3ኛ) ጣልቃ መግባት (intervention)

ይህ ሶስተኛው አብይ ክፍል ድምራቸው ከ40 በላይ የሚሆኑ ሰላማዊ መታገያ መሳሪያዎች አሉት። እነዚህ የሰላም ትግል መሳሪያዎች በግልጽ የሚታዩ ናቸው። ለባለስልጣኖችም የሚደቅኑት ፈተና ቀጥተኛ በመሆኑ ፈጥኖ መልስ የማግኘት እድላቸው ከፍተኛ ነው። ከባለስልጣኖች የሚሰነዘረው ምላሽ ወከባ እና ቅጣት ሊሆንም ይችላል። ትብብር ከመንፈግ የሰላም ትግል መሳሪያዎች ይልቅ ጣልቃ መግባት የሰላም ትግል መሳሪያዎች አምባገነኖችን ይበልጥ ሊያስቆጣ እና ፈጣን ቅጣት ሊያስከትልም እንደሚችል የሰላም ትግል መሪዎች ሊገነዘቡ ይገባል። አራት ምሳሌዎች እንመልከት፡-

(ሀ) አንደኛው ሳይኮሎጂያዊ ጣልቃ ገብነት (Psychological intervention) የተባለው ነው። ይህ የትግል መሳሪያ እራስን በመጉዳት የሚደረግ ትግል ነው። አንድነት ፓርቲ ‹‹እየሞትን ስንገድል›› ትግላችንን እንቀጥላለን የሚለውም ከዚህ ሊመደብ ይችላል። የረሃብ አድማም ከዚሁ ክፍል ይካተታል።

(2) ሁለተኛው አካላዊ ጣልቃ ገብነት (Physical intervention) የሚለው ነው። ጥቂት ምሳሌዎች፡- (ሀ) በሚሊዮኖች በመሆን የግብጽ ወጣቶች የግብጽ ካይሮን የነጻነት አደባባይ (ታህሪርን) መውረር እና የድንኳኖች ከተማ መስርቶ ጥያቄ መልስ እስኪያገኝ በአደባባዩ መኖራቸው (Sit-ins)፣ (ለ) የ1997 ምርጫን ተከትሎ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎችን ወደ እስር ቤት በሚወሥደው የፖሊስ መኪና መንገድ ላይ የኮተቤ ተማሪዎች እና ያካባቢው ዜጎች መንገድ መዝጋታቸው (ከፖሊስ አዛገቦች መሐይምነት የተነሳ የዜጎች ድርጊት ወንጀል ተደርጎ የተገደሉ ቢኖሩም ትግሉ ሰላማዊ ትግል ነበር) እና የመሳሰሉት የሰላም ትግል መሳሪያዎች።

(3) ሶስተኛው ኢኮኖሚያዊ ጣልቃ ገብነት (Economic intervention) ነው። ጥቂት ምሳሌዎች፡- (ሀ) የባለስልጣኖች ገንዘብ እና ንብረት እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ (የሊቢያው መሪ የጋዳፊ ሃብት በአሜሪካ፣ የግብጹ ሙባረክ ሃብት በስዊዝ ባንክ፣ እንዳይንቀሳቀስ እንደተደረገው)፣ (ለ) ነባር የንግድ ደንበኛ የፖለቲካ ባላንጣ ሲሆን ከሱ ጋር ንግድ በማቆም እና አዲስ ደንበኛ በመያዝ የቀድሞ ደንበኛን ኢኮኖሚ ማዳከም የማሳሰሉትን ያካትታል።

(4) አራተኛው ደግሞ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት (Political intervention) የሚባለው ነው። ጥቂት ምሳሌዎች፣

(ሀ) የመንግስት አሰተዳደር በስራ እንዲወጠር እና የእለት ከእለት ስራውን መስራት እንዳይችል ማድረግ፣ የሰላዮችን ስም ይፋ በማድረግ መንግስት እንደቀድሞው መሰለል እንዳይችል ማድረግ፣ የሰላዮች ስም ይፋ ሲደረግ ስህተት እንዳይፈጸም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በስም አጥፊነት ሊያስከስስ እና ሊያስቀጣ ይችላል።

(ለ) በምርጫ ደግሞ በአገር አቀፍ ደረጃ ፓርላማን ማሸነፍ ካልተቻለ የተወሰኑ ክልሎችን ወይንም ከተሞችን ወይንም ወረዳዎችን ማሸነፍ የመሳሰሉት ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው።

(ሐ) ምስራቅ ሊቢያ የምትገኘው ቤንጋዚ የተባለችው ከተማ በሰላማዊ ህዝባዊ አመጽ ነፃ ስትወጣ የጋዳፊ መንግስት ትሪፖሊን ጨምድዶ ቢይዝም ህዝብ በቤንጋዚ ከተማ የመሰረተው ትይዩ መንግስት (Parallel government) የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነው። ለጥቀን የምናጠናው ለውጥ ማምጫ መንገዶችን ነው።

ይቀጥላል.....

የመንግስት አሰተዳደር በስራ እንዲወጠር እና የእለት ከእለት ስራውን መስራት እንዳይችል ማድረግ፣ የሰላዮችን ስም ይፋ በማድረግ መንግስት እንደቀድሞው መሰለል እንዳይችል ማድረግ፣ የሰላዮች ስም ይፋ ሲደረግ ስህተት እንዳይፈጸም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

በወላይታ ዞን አፈናና ወከባው ቀጥሏል

መጋቢት 20/ 2006 ዓ.ም ሶዶ ውስጥ ስብሰባ ለማድረግ ዝግጅት እያደረጉ በነበረበት ወቅት ለእስር የተዳረጉት የወላይታ ዞን የሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች ድብደባና ወከባ እንደተፈጸመባቸው የፓርቲው የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ አቶ ጌታነህ ባልቻ ገለጹ፡፡

በወቅቱ ታስረው ከነበሩት መካከል ወጨፎ ሳዳሞ የወላይታ ዞን ምክትል ሰብሳቢ፣ ታደመ ፍቃዱ የወላይታ ዞን አደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ፣ አቶ ጻድቁ ወ/ስላሴ የወላይታ ዞን የፋይናንስ ኃላፊ፣ አቶ ቴዎድሮስ ጌታ የዞኑ የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ እና አቶ ቦጋለ የፓርቲው አባል ይገኙበታል፡፡ ጠዋት 4 ሰዓት ላይ የታሰሩት የዞኑ አመራሮች ምግብ፣ ውሃና ልብስ እንዳይገባላቸው ተከልክሎ እንደነበርም የአካባቢው አመራሮች ለነገረ ኢትዮጵያ ገልጸዋል፡፡

‹‹ከዚህ በፊት ሁለት የፓርቲው አመራሮች በአራዳ ፖሊስ ጣቢያ ታስረው ለፓርቲው ስራ የሚገለገሉባቸውን ሰነዶች ተወስዶባቸዋል፡፡ የዞኑን መዋቅር ለመጎብኘት ከአዲስ አበባ ወደ አካባቢው የተጓዙ ሶስት የፓርቲው አመራሮችና የአካባቢው ተወካዮች ታስረው ስራቸው ከመስተጓጎሉም ባለፈ መገልገያ እቃዎቻቸውን ተቀምተዋል፡፡›› ያሉት አቶ ጌታነህ በአሁኑ ወቅት የሚደረገው እስርና ወከባ ከቀደመው የቀጠለ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ቅዳሜ መጋቢት 20 የታሰሩት የወላይታ ዞን የፓርቲው አመራሮች ከምሽቱ 4፡00 አካባቢ ከእስር ቢለቀቁም ሲም ካርዳቸውን በመስበር ከጥቅም ውጭ እንዳደረጉባቸው እና በራሪ ወረቀቶችን፣ ሰነዶችንና ሌሎች የመገልገያ መሳሪያዎችንም እንደቀሟቸው ታውቋል፡ ፡ ከዚህም በተጨማሪ በምሽት የተፈቱት ታሳሪዎች ወደ ቤታቸው በሚያቀኑበት ወቅት የአራዳ ፖሊስ አዛዥ ኮማንደር ታጠቅ፣ በሶዶ ከተማ የአራዳ ክ/ከተማ አስተዳደር አቶ ጌታቸው መኮንን፣ የአራዳ ክ/ከተማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዝናቡ ተክሌ፣ የአራዳ ክ/ከተማ ደንብ አስተባባሪ አቶ መስከረም፣ እንዲሁም አቶ ተሾመ፣ አቶ ደጉና ሌሎች ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች የሰማያዊ ፓርቲ ወላይታ ዞን አደረጃጀት ኃላፊ የሆነውን አቶ ታደመ ፍቃዱ እና የዞኑ ም/ሰብሳቢ የሆነውን አቶ ወጨፎ ሳዳሞ በመደብደብ ጉዳት እንዳደረሱባቸው ከአካባቢው መዋቅር የተገኘውን መረጃ በመጥቀስ አቶ ጌታነህ ባልቻ ለዝግጅት ክፍላችን አስረድተዋል፡፡

ግሉኮስ ኢትዮጵያ ውስጥ ጠፍቷል

‹‹የሚያስመጣው መንግስት ስለነበር እሱ ሲያቆም እጥረት ሊፈጠር ችሏል›› መድሃኒት ቤቶች

ሀናን ትባላለች፤ አንገቷ ላይ በተፈጠረ ህመም ለቀናት ምግብ መመገብ አልቻለችም፡ ፡ ከአሁን ቀደም ተመሳሳይ ችግር ሲያጋጥማት ወደ ሀኪም ቤት በመሄድ የሚታዘዝላትን ‹‹ፎርቲ ፐርሰንት›› አሊያም ጉልኮስ በመውሰድ በህመሟ ምክንያት ምግብ ባለመውሰዷ የሚገጥማትን የኃይል እጥረት ‹‹40 ፐርሰንት›› በመውሰድ ከህመሟ ታገግም እንደነበር ትገልጻለች፡፡ በቅርቡ በተመሳሳይ ሁኔታ በመታመሟ ይህን መድሃኒት ለመውሰድ ያደረገችው ጥረት መድሃኒቱ በየትኛውም መድሃኒት መደብር ባለመገኘቱ ከህመሟ በቀላሉ ልታገግም አልቻለችም፡፡

የተለያዩ መድሃኒት ቤቶችን ለማነጋገር እንደሞከርነው ‹‹40 ፐርሰንት›› አገር ውስጥ አይገኝም፡፡ ስድስት ኪሎ አካባቢ የሚገኝ አንድ መድሃኒት ቤት ውስጥ የሚሸጥ አንድ ባለሙያ እንደሚለው ይህን መድሃኒት ያስመጣ የነበረው መንግስት በመሆኑ በአሁኑ ወቅት መንግስት መድሃኒቱን እያስመጣ ባለመሆኑ በአገሪቱ እጥረት ሊፈጠር ችሏል፡፡ እንደ ባለሙያው ከሆነ በርካታ ታማሚዎች ይህንን መድሃኒት ፈልገው ወደ መደብራቸው የሚመጡ ቢሆንም በእጥረቱ ምክንያት ሳያገኙ ይመለሳሉ፡፡ ወጣቱ ባለሙያ እንደሚለው ‹በበሽታ ምክንያት ምግብ መመገብ ያልቻሉ፣ በበሽታና በሌሎች ምክንያቶች ከፍተኛ ድካም ያለባቸው ሰዎች መድሃኒቱን በመውሰድ ባለባቸው ወቅታዊ ችግር መፍትሄ ያገኛሉ፡፡ ይህ መድሃኒት አገር ውስጥ ባለመኖሩ እነዚህ ህመምተኞች የሚገባቸውን አገልግሎት እያገኙ አይደለም፡፡›

ካዛንቺስ አካባቢ የሚገኝ መድሃኒት መደብር ውስጥ የሚሰራ ሌላኛው ባለሙያ ‹‹40 ፐርሰንት›› መሰረታዊ መድሃኒት ባይሆንም እጥረቱ ከተፈጠረ መቆየቱን ይገልጻል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ በተመሳሳይ ሙያ የተሰማሩት ግለሰብ ‹‹መድሃኒቱ ምግብ በተገቢው መንገድ መውሰድ ያልቻሉ ህሙማን ካሉበት ሁኔታ ለማገገም የሚጠቅም በመሆኑ መሰረታዊ አይደለም ሊባል አይችልም፡፡ እንደየትኛውም መድሃኒት አገር ውስጥ መኖር ይገባው ነበር፡፡ አብዛኛዎቹ ጉዳዮች በመንግስት በመያዛቸውና የግል ባለሃብቶች በራሳቸው አቅም እንደዚህ አይነት መድሃኒቶችን ለማስገባት ያላቸው ፈቃድ፣ አቅምና ልምድ ለእጥረቱ እንደ ትልቅ ምክንያት እንደሚቆጠር›› ይገልጻሉ፡፡

የካቲት 12 ሆስፒታል ያገኘናቸው ሌላኛው ባለሙያ ‹‹40 ፐርሰንት›› ከጠፋ መቆየቱን ገልጸው መንግስት ያስመጣው የነበረው ይህ መድሃኒት በመቋረጡ የህሙማንን ፍላጎት ማስተናገድ እንዳልቻሉ ገልጸውልናል፡፡

በጉዳዩ ዙሪያ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር የህዝብ ግንኙነት የሆኑትን አቶ ሽምሰዲን ባምቦሮን ለማነጋገር የእጅ ስልካቸው ላይ በተደጋጋሚ ብንደውልም ስልካቸው ባለመነሳቱ ሀሳባቸውን ማካተት አልቻልንም፡፡

የሽብርተኝነት እንቆቅልሽ...

መንገድ የማጣጣም ሀላፊነት የሚወስደው ደግሞት መንግስት ነው፡፡

በህዝብ ይሁንታ ስልጣን ላይ ወጥተው ህዝብን የሚያስተዳድሩ መንግስታት አዋጁን የዜጎችንና ብሄራዊ ደህንነትን በማጣጣምና ለማስጠበቅ ይጠቀሙበታል፡፡ በተቃራኒው አምባገነን መንግስታት የጸረ ሽብር ህግ የተፈቀዱና ሰላማዊ የፖለቲካና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በመቀፍደድ ለራሳቸው ስልጣን ማራዘሚያ በመሳሪያነት ይጠቀሙበታል፡፡ ‹‹ARTICLE 19›› የተሰኘ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለ ነጻ ሀሳብና የመረጃ ነጻነት የሚከራከር ተቋም ‹‹COMMENT on Anti-Terrorism Proclamation, 2009, of Ethiopia›› በሚል ጥናቱ የኢትዮጵያው ጸረ ሽብር አዋጅ የህዝብንም ሆነ የብሄራዊ ደህንነትን የማያስጠብቅ የኢህአዴግ መሳሪያ መሆኑን ይደመድማል፡፡ በተቃራኒው አዋጁ ተጠቅሞ ከብሄራዊ ደህንነት ጋር በማይጋጭ መልኩ ለዜጎች ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት መቆም የነበረበት መንግስት ፖለቲካዊ ትርጉም የሰጠውን አዋጅ ተጠቅሞ መሰረታዊ መብቶቻቸውን እየጨፈለቀ እንደሚገኝ ይከሳል፡፡

የትርጉም ግልጽነት

አካላት ህግን ከራሳቸው ጥቅም አንጻር እንደፈለጉ እንዲጠመዝዙ ከሚያችላቸው አጋጣሚ አንዱና ዋነኛው ህጉ የሚኖረው የግልጽነት ችግር ነው፡፡ የግልጽነት ችግር በተለይም ጉዳዩን ለራሱ ጥቅም ለመጠምዘዝ ለሚችለው የበላይነት ያለው አካል መጠቀሚያ ሲሆን አቅም (ወቅታዊ ስልጣን) የሌላቸው ግልጽነት በጎደለው ህግ ተጎጅዎች ይሆናሉ፡ ፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያውያ መቼም ቢሆን የህይወት ስምምነት ውልን አይረሱትም፡፡ ጣሊያንኛውና አማርኛው በተምታታና ግልጽነት በጎደለው መልኩ የተጻፈው ውል በብዙ መልኩ ሀይሉ የነበራቸው ጣሊያኖች በፈለጉት መልኩ እንዲጠመዝዙት ሲያስችላቸው ኢትዮጵያውያኑ ደግሞ ተጎጅዎች ሆነዋል፡፡

የኢትዮጵያ ‹‹የጸረ ሽብር›› አዋጅ ከህይወት ስምምነት የሚለየው ውሉ በኢትዮጵያ መንግስትና በአገሪቱ ህዝቦች መካከል፤ እንዲሁም የትርጉሙ ችግር ከቋንቋ ይልቅ አድበስብሶ የማለፍና ወደሚፈልጉት ለማስጠጋት አመች መሆኑ ብቻ ነው፡፡ አዋጁ ከመጠን በላይ ሰፊና ግልጽነት የሚጎድለው ነው፡፡ ከላይ በዝርዝሩ እንዳየነው በርካታ ተራ ወንጀል እንኳን የማይሆኑ የሰላማዊ ትግል አካላትን ጭምር በትርጉሙ አካቷል፡፡ ተራ ወንጀልነት በሌላ ህግ ሊታዩ የሚችሉትን ተግባራትም ከበስተጀርባቸው የራሱን ዓላማና ትርጓሜ በመጨመር ወደሚፈልፈው ‹‹የሽብር›› አይነት ይቀይራቸዋል፡፡ አዋጁ ‹‹ንብረት››፣‹‹በሽብርተኝነት የተገኘ ንብረት››፣ ‹‹እገታ ወይንም ጠለፋ››፣ ‹‹ማነሳሳት››፣ ‹‹የህዝብ አገልግሎት››፣ ‹‹መንግስት››፣ ‹‹ፍርድ ቤት››፣ ‹‹ፖሊስ››፣ ‹‹ሰው›› የሚሉትን ተራ ቃላት በግልጽ ደግሞ ደጋግሞ በተረጎመበት ‹‹ሽብርተኝነት›› የሚለውን ተግባር ግን ግልጽነት እንደጎደለው በአከራካሪነት እንደተሞላ አልፎታል፡፡ ይህም የሆነው አሸባሪነት በግልጽነት ከሚተረጎም ይልቅ በድፍኑ ለመግዢያ መሳሪያነት ስለሚያገለግለው ነው፡፡

ከምንም በላይ አዋጁ በሰላማዊ ትግል፣ ሽብር፣ የትጥቅ ትግልና ተራ ወንጀል መካከል ያሉትን ልዩነቶች ለይቶ ለማወቅ አለማስቀመጡ አዋጁንም ስልጣን ላይ ያሉት ለጥቅማቸው የሚጠመዝዙት የዘመኑ የህይወት ውል ያደርገዋል፡፡ በአንቀጽ 3(6) ማንኛውንም የህዝብ አገልግሎት ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ስር ያደረገ፣ ያቋረጠ ወይንም ያበላሸ እንደሆነ ይላል፡፡ ይሁንና እነዚህ ተግባራት በሰላማዊ እምብይተኝነት ላይ የተለመዱ ስልቶች በመሆናቸው ከሽብርተኝነት ይልቅ ለሰላማዊ ትግል አካል ናቸው፡፡ ይሁንና ከ1997 አብዛኛዎቹ ተግባራት ሲተገበሩ ያየው አሊያም ሊተገሩ ሲሉ ፈርቶ በሀይል ያስቆመው ኢህአዴግ ወደ ሽብር አስጠግቷቸዋል፡፡ አዋጁ በሰላማዊ ትግል፣ ሽብር፣ የትጥቅ ትግልና ተራ ወንጀል ላይ ግልጽነት ቢኖረው እና ከፖለቲካዊ ይልቅ ህጋዊ ትርጉም ቢሰጠው ፓርላማ በአሸባሪነት የፈረጃቸው የአገራችን ድርጅቶች እና አልቃይዳ መካከል በአንድ አውድ ውስጥ ሊቀመጡ እንደማይችሉ ግልጽ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ለጸረ ሽብር አዋጅ መሰረት የሆነችው አሜሪካ የኢትዮጵያ ፓርላማ መካከል ያለውን ልዩነት መግለጽ ተገቢ ነው፡፡ ኢህአዴግ በበላይነት የሚመራው ፓርላማ የኢትዮጵያዎቹ ድርጅቶችና ግለሰቦች እንዲሁም አልቃይዳና አልሻባብ በአንድ አውድ አጭቋቸዋል፡፡ በተቃራኒው አሜሪካ የኢትዮጵያዎቹና አልቃይዳ እጅጉን የተለያዩ መሆናቸው ለማመን የሚያስችላት ህጋዊ ማዕቀፍን የተላበሰ ‹‹ጸረ ሽብር ህግ›› በማጽደቋ ኢህአዴግ ለሚያሳድዳቸው መጠለያ ሆናለች፡፡

መንግስታት ዜጎች፣ ቡድኖችንን በምርመራ፣ በእስራትና በመሳሰሉት ህዝቦችን በርዕዮታዊ፣ ሀይማኖታዊና ፖለቲካዊ አቋማቸው ከመፈረጅ ይድኑ ዘንድ የጸረ ሽብር ህጉን ግልጽ በሆነ መንገድ ሊተረጉሙ ይገባቸዋል፡፡ በሽብርተኝነት ምክንያት ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ለህዝብም ሆነ ለአገር ደህነት ሲባል እንዲወሰን ግድ የሚለው ሀሳብን የመግለጽ መብት ርዕዮታለማዊ፣ሀይማኖታዊ፣ ወይንም የተደራጀ ወንጀልን በማራመድ በመንግስትና ባለስልጣናት እንዲሁም በህዝብ ላይ ‹‹ሽብር›› ይፈጥራል በሚል ነው፡፡

የጸረ ሽብር ህጉ ሽብርተኝነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚሳተፉትን ፈርጇል፡፡ ሆኖም ህጉ እንዲህ አከራካሪና ፖለቲካዊ አላማ በያዘበት ሁኔታ በአንቀጽ 6 ሽብርተኝነትን ስለማበረታታት፣ አንቀጽ 7 በሽብርተኝ ድርጅት ውስጥ ስለመሳተፍ፣ በአንቀጽ 8 ለሽብርተኝነት ድርጊት መፈጸሚያነት እንዲውል ንብረት መያዝ ወይም መጠቀም፣ በአንቀጽ 9 በሽብርተኝነት ድርጊት የተገኘን ንብረት ስለመያዝና መገልገል፣በአንቀጽ 10 ምስክር ማባበል ወይንም ማስፈራራትና ማስረጃ ማጥፋት፣ በአንቀጽ 11 በሀሰት የሽብርተኝነትን ድርጊት ስለማስፋፋት፣ በአንቀጽ 12 የሽብርተኝነት ድርጊቶችን አለማስታወቅ የሚሉት ከህጋዊ መሰረት ይልቅ አወዛጋቢና በህዝብ ላይ አሉታዊ መሆናቸው የማይቀር ነው፡፡

የሽብርተኝነትን ጉዳይ የሚከታተሉ ተቋማት ውስጥ (1) አቃቢ ህግና ፖሊስ፣ (2) የደህንነት ሰራተኞች፣ (3) የጸረ ሽብር አስተባባሪ ኮሚቴ፣ (4) በሽብርተኝነት ወንጀል የዳኝነት ስልጣን በሚል ሲቀመጥ ዳኞች በአራተኛ ደረጃ ላይ ነው የተቀመጡት፡፡ ምንም እንኳ ዳኝነቱም በገዥው መንግስት ቁጥጥር ስር የወደቀ ቢሆንም መጀመሪያ ሽብርተኝነትን ደህንት፣ የጸረ ሽብር አስተባባሪ ኮሚቴ የመሳሰሉት ከገዥው ፓርቲ ጋር ልዩነት የሌላቸው አካላት ስለ ሽብርተኝነት ቀድመው የመወሰን አቅም አላቸው ማለት ነው፡ ፡ ይህም የሚያሳየው ገዥው ፓርቲ ከተጽዕኖው ያልወጣውን ፍርድ ቤትም ቢሆን የደህንነትና የጸረ ሽብር ግብረ ኃይልን ያህል ‹‹አላማየን ያስፈጽምልኛል!›› ብሎ እንደማያምነው ነው፡፡

የተበይዎች አለመሥማማት ለበይዎች ይበጃል

ደረጀ መላኩ

Tilahungesses@gmail.com

የዛሬውን ፅሁፍ (መልዕክት) ለማድረስ ከአይምሮዬ ጓዳ ጋር በምሟገትበት ቅፅበት ውስጥ የዝነኛው ማዕከላዊ እዝ ኦርኬስትራ (የቀድሞ ክቡር ዘበኛ ኦርኬስትራ) ባልደረባ የነበረውን ጋሼ ጥላሁን ገሠሠ ‹‹ለእውነት እሞታሁ!›› የሚለውን ግሩም ጥዑም ዜማ እያዳመጥኩ ነበር፡፡ ዛሬ ያ! ሀገር ወዳድ ተውረግራጊ ዘፋኝ በአጠገባችን የለም፡፡ ህያው ሥራዎቹ ግን ዝንተ ዓለም ይኖራሉ፡፡ ለማንኛውም አፈሩን ገለባ ያድርግለት! እያልኩ ወደ መልእክቴ እወስዳችኋለሁ፡፡ ላለፉት አርባ ዓመታት የኢትዮጵያ ህዝብን ለሥልጣን እናበቃለን በማለት የተነሡ እውነተኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች አንድ ላይ በማበር እንደ መኾርገር ተጣብቀው ደማችንን የሚመጡትን ገዥ መደቦች ከሥልጣን ኮርቻ ለማውረድ ለምን ተሳናቸው?

ህዝባዊ መንግሥት ለመመሥረት የሚያሥችሉ በርካታ እድሎች ለምን ባከኑ? እባካችሁ ውድ ወገኖቼ ጠይቁ፡፡ በእኔ በኩል እውነተኞቹ የአንድነት ፍልሥፍና አራማጆች እራሳቸው በሚያሠሟቸው ነጥቦች ዙሪያ አንድ መሆን ባለመቻላቸው ይመሥለኛል እንዲህ ተዋርደን የቀረነው፡፡ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ እያለ ክልትው ብሎ የቀረው ያ ትውልድ ድክመቱ ህዝባዊ መንግስትን በመመሥረት ሂደት ላይ በመከፋፈሉ ነበር፡፡

የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት በህዝባዊ አመፅ በየካቲት 1966 ዓ.ም ሲገረሰስ ሀገሬ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ለማግኘት ታሪክ እድሉን ሠጥቷት ነበር፡፡ ይሁንና በልጆቿ ያለመሥማማት (የታሪካዊ ጠላቶቿን ውሥብስብ ሴራ ሳንዘነጋ ማለት ነው) ያ ወርቃማ እድል አምልጧታል፡፡ በጊዜው ሥልጣን ለመጨበጥ በለስ የቀናው የወታደሮች ስብስብ የነበረው ደርግ ቢሆንም የደርግ ተቀናቃኝ የነበሩት እንደ ኢህአፓና መኢሶን የመሣሰሉት ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ በህብረት ቢቆሙ ኖሮ ደርግ ወደ ህዝባዊ መንግስት ምስረታ እንዲገባ ማስገደድ ይችሉ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ይሄ እውን መሆን አልቻለም፡፡ ውጤቱም በኢትዮጵያ ህዝብ የታወቀ በመሆኑ ሳልጠቅሰው አልፈዋለሁ፡፡

ግራም ነፈሠ ቀኝ ደርግ በአንዲት ኢትዮጵያ ፍልሥፍና ስም ሥልጣኑን ለማንም ሳያካፍል ከአሥራ ሰባት አመታት አገዛዝ በኋላ ኤርትራና የተፈጥሮ ባህራችን የነበረውን ቀይ ባህርን አሣጣን፡፡ በአጭሩ ጉሮሮአችን ተዘጋ፡፡ ደርግ ይሄን ያህል ዓመት በሥልጣን ላይ የቆየው ፍርሃትን አሸንፈን በአንድ ላይ መቆም ስላቃተን ነው፡፡ የደርግ አሥር አለቆች እና ካድሬዎቻቸው በጭንቅላታችን ላይ የጨፈሩብን፡፡ በነገራችን ላይ ደርግ ምንም እንኳን አምባገነን አገዛዝ የነበረ ቢሆንም የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማስከበር የዋጀ በህብረተሰብ መሀከል የጥላቻ መርዝ ያልረጨ ሥርዓት ነበር፡፡ ታሪክ አይሸጥም፡፡

ደርግን በጦር ሜዳ ገጥመው በጠመንጃ ኃይል ያሸነፉት የያኔዎቹ ፋኖዎች ዛሬ የቅምጥል ኑሮ ተቋዳሾች እና እንደ ትሮይ ፈረሥ የሚጋልቡን ገዥዎቻችን በዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ውትወታ (በተለይ በምዕራቡ ዓለም) የመድብለ ፓርቲ ምሥረታ በዚች ሀገር ላይ እውን እንዲሆን ፈቅደዋል፡፡ ውስብስቡን የፖለቲካ ሴራቸውን ሳንዘነጋ ማለቴ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ተዋናዮች የህወሓት እና ሻዕቢያ ታጋዮች ቢሆኑም ቅሉ የታሪካዊ ጠላቶቻችን ሴራ እና የኢትዮጵያ ህዝብ ልብ በደርግ ላይ መሸፈት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

አፍሪካውያን ከቅኝ አገዛዝ መዳፍ ወጡ ከተባለ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ሆኗቸው፡ ፡ ሆኖም ግን ዛሬም በርካታ የአፍሪካ ክፍሎች ከችጋርና ዋይታ አልተላቀቁም፡፡ ምክንያቱም ምን ይሆን? ዛሬም በቅኝ ገዥዎች ላይ ጣት መቀሠር ያዋጣልን? በእኔ በኩል በአንዳንድ የአፍሪካ ክፍል የሚኖሩ ህዝቦች በአንቀልባ ያዘሏቸውን ጨካኝ እና አፋኝ ገዥዎችን በህብረት ተነሥተው ከጫንቃቸው ላይ ማውረድ ባለመቻላቸው ነው ፍዳቸውን የሚቆጥሩት፡፡ ዛሬ የመካከለኛው የአፍሪካ ሪፐብሊክ ህዝብ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሊፈፀም ይችላል ተብሎ የማይታመን ግፍን እያስተናገደ የሚገኘው በህብረት ሆ! ብሎ ባለመነሣቱ ነው፡፡ ጎበዝ! አምባገነን እና ጎሠኛ ሥርዓትን በሕብረት ፍልስፍና ቆመን ሃይ ካላልነው ከምድረ ገፅ ያጠፋናል፡፡

እስቲ አሁን ደግሞ ወደ ሀገራችን እንመለስ፡ ፡ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ የኢትዮጵያ ስነ-ምድር አቀማመጥ ቅርጹዋም ሆነ የገዢዎቿ ፖለቲካዊ ፍልስፍና ተቀይሯል፡፡ ዛሬ ሀገሬ ኢትዮጵያ አንገቷ ተቆርጦ የባህር በር የሌላት ናት፡፡ ገዢዎቿም የጎሣ ፖለቲካን በማራመድ ይታወቃሉ፡፡ የሥልጣን ተቀናቃኝ ፓርቲዎች ደግሞ ገሚሶቹ የብሔር ፖለቲካን ሲያራምዱ ሌሎች በጣም ጥቂቶች የአንድነት ፍልስፍናን ያቀነቅናሉ (ያራምዳሉ)፡፡ የርዕዮት ዓለም ልዩነታቸውን ሣንዘነጋ ማለቴ ነው፡፡ ዛዲያ ለምንድነው በዚህ መጥፎ ዘመን ከሠላማዊ ትግል አኳያ የመንግስት ለውጥ ለማምጣት ቆርጠው የተነሡ እውነተኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች አብረው ለመሥራት የተሣናቸው? ምን ይሆን ችግሩ? ያለችን እኮ አንድ አገር ናት፡፡ ለምንድን ነው የኢትዮጵያን ህልውና ማስቀደም የተሣነን? ኧረ ጎበዝ እየሞትን መኖር አንጀምር፡፡

ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ለቁጥር የሚታክቱ የፖለቲካ ፓርቲ ተብዬዎች እንደ እንጉዳይ መፍላታቸውን ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም ግን ለኢትዮጵያ ምንም የጠቀማት ነገር የለም፡፡ እንኳን እንዲህ ዓይነት የሥም ፓርቲዎች ቀርቶ እውነተኞቹ በሴረኞች እና ቅጥረኞች የተነሣ አላማቸውን ከዳር ለማድረስ ተስኗቸዋል፡፡ ከፓሪሱ የትብብር መድረክ ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ በርከት ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውህደትና አንድነት በመካከላቸው ቢደረግም ብዙም ሣይቆይ አንድነቱም ሆነ ውህደቱ ፈርሷል፡፡ እርግማን ይሆን?

ግንቦት 1997 ዓ.ም ላይ የኢትጵያን ህዝብ ታላቅነት ለዓለም ያሳየው ቅንጅት ያሰባሰባቸው ፓርቲዎች ህብረት ከምርጫው በኋላ በመክሰሙ በእውነቱ አንገትን ያሣደፋል፡፡ ከ1997 ዓ.ም ወዲህ ደግሞ ህብረ ብሄር ፓርቲዎች እና ብሔር ተኮር ፖለቲካ ፍልሥፍና የሚያራምዱትን ፓርቲዎች አቅፎ ሊይዝ ነው የተባለው “መድረክ” የአንድነት ፓርቲን ለጊዜው ከአባልነት አግዷለሁ በማለቱ በትብብሩ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ቸልሶበታል፡፡

በቅርቡ ደግሞ የአንድነትና መኢአድ ውህደት ወይም ህብረት እውን ሊሆን ነው ተብሎ በጉጉት ሲጠበቅ ከቆየ በኋላ ከሽፏል፡ ፡ ከመኢአድ ሰዎች የተነገረውን ባልሰማም አንድነት ፓርቲ አመራር ወዲውኑ ባወጣው መግለጫ በመኢአድ ፕሬዝዳንትና አመራሮች እምቢተኝነት የቅድመ ውህደት ፊርማው እንዳልተደረገ አርድቶናል፡፡ ሆኖም ግን የተወሰኑ የመኢአድ አመራሮችና አባላት ለመዋሀድ ዝግጁ እንደነበሩ አንድነት በመግለጫው ለህዝብ ይፋ አድርጓል፡፡ በእውነቱ ለመናገር ለኢትጵያ ህዝብ ትልቅ መርዶ ነው፡፡ የመከራ ፅዋው ሞልቶ በፈሰሰበት በዚህ ጨለማ ዘመን አብሮ ለመሥራት (ለመዋሀድ) አለመፈለግ ትዝብት ውስጥ ይጥላል፡ አሁንም ቢሆን ደግማችሁ፣ ደጋግማችሁ አስቡበት የሚል መልእክቴን ለሁለቱም አመራሮች (አባላት) አደርሣለሁ፡፡

ህዝባዊ መንግሥት ለመመሥረት የሚያሥችሉ በርካታ እድሎች ለምን ባከኑ? እባካችሁ ውድ ወገኖቼ ጠይቁ፡፡ በእኔ በኩል እውነተኞቹ የአንድነት ፍልሥፍና አራማጆች እራሳቸው በሚያሠሟቸው ነጥቦች ዙሪያ አንድ መሆን ባለመቻላቸው ይመሥለኛል እንዲህ ተዋርደን የቀረነው፡ ፡ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ እያለ ክልትው ብሎ የቀረው ያ ትውልድ ድክመቱ ህዝባዊ መንግስትን በመመሥረት ሂደት ላይ በመከፋፈሉ ነበር፡፡

እንደ መደምደሚያ

ጎበዝ በሠለጠነው 21ኛው ክፍለ ዘመን የሰለጠኑት አውሮፓውያን ድንበር እያፈረሡ እኛ እንዴት አንድ መሆን አቃተን? ለምንድነው ድንበራችንን የምናጠበው? እናንት ፍፁም ሠላማዊ በሆነ መንገድ ሥልጣን እንይዛለን ያላችሁ አንድነት ሳይኖራችሁ ይሄን የለየለት አምባገነን ስርዓት ማንበርከክ ትችላላቹህ? እርግጥ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ የፍርሀት ቆፈኑን ሰብሮ ሲወጣ የሚሆነው ይሆናል፡ ፡ የብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ ወገኖቼ ስጋት ግን ከለውጡ በኋላ ችግር (ቀውስ) ሊፈጠር ይችላል የሚል ነው፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ህልውና የሚያሳስባቸው ሠላማዊ ታጋዮች በአንድነት ሆነው ኢትዮጵያን እንዴት ሊታደጓት ይችላሉ የሚለው ነው፡፡ ግራም ነፈሰ ቀኝ እናት ኢትዮጵያ በመስቀለኛ መንገድ ላይ ትገኛለች፡ ፡ ስለሆነም በአስቸኳይ የአንድነት ፍልሥፍና ከሠላማዊ ታጋዮች ይጠበቃል፡፡ በተለይ መንፈሰ ጠንካሮች የሠማያዊ ፓርቲ አመራርና አባላት፣ የአንድነት ፓርቲ እና መኢአድ ህብረትን መስርቱ፡፡ ከኢትዮጵያ የበለጠ ነገር ያለ አይመስለኝም፤ ጥሪው ሀገርን የማዳን ጥያቄ ነው፡፡ እባካችኹ ውድ የሶስት ፓርቲ ፊት አውራሪዎች እና አባላት አሁን ጊዜ የለም በጣም መሽቷል፡፡ አገዛዙ ወደ ፍፁም አምባገነናዊ ሥርዓት ተቀይሯል፡፡ በ2007 ዓ.ም ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቀው ሀገራዊ ምርጫ ሁለት ዋና ዋና አማራጮችን ይዟል፡፡ አንደኛው የኢትዮጵያን ህልውና ለማሥጠበቅ የሚደረግ ትግል ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ አገዛዙ በፍፁማዊ አምባገነንነት ለመቀጠል የሚያደርገው መሯሯጥ ይመስለኛል፡፡

ውድ በሀገር ፍቅር ስሜት ልባችሁ የነደደ እውነተኛ የሠላማዊ ትግል አራማጆች፣ መጀመሪያ ኢትዮጵያን እናድን እና የምርጫውን ፌሽታ እናዘጋጅ፡፡ ከዛ በኋላ እዳው ገብስ ነው፡፡ በሁሉም የእድገት መለኪያዎች እኮ የዓለም ጭራ እየሆንን ነው፤ ለምሣሌ በኢትዮጵያ 90 ሚሊዮን ህዝብ ውስጥ ከ43 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት ዜጎች ንፁህ ውሃ አያገኙም ሲል ዓለም አቀፍ የጤና ድርጅትና የተባበሩት መንግስታት የህፃናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) በጋራ ባወጡት መግለጫ አስታውቀዋል፡፡

በዚህ መሰረትም ኢትዮጵያ ከዓለም ውሃ ለዜጎች በሚያደርሱ አገሮች ከመጨረሻዎቹ 10 አገሮች ውስጥ ትገኛለች፡፡ UNICEF ባለፈው ባወጣውም መግለጫ ኢትዮጵያ ካሏት ህዝቦች ውስጥ 38 ሚሊዮን የሚደርሱት መፀዳጃ ቤት የላቸውም፡፡ እንዲያውም በየጢሻውና በየሜዳው ይፀዳዳሉ ሲል መናገሩ ይታወሣል፡ ፡ የኢቲቪ (ETV) ኢትዮጵያ ከህልም የዘለለች አይደለችም፡፡ ምስጋና ለእነ ሻምበል አበበ በቂላ፣ ሻምበል ማሞ ወልዴ፣ ባሻ ዋሚ ቢራቱ፣ አሠልጣኝ ንጉሤ አሮባና ወልደ መስቀል ኮስትሬ በእነሱ ታላቅነት ምሣሌ ዛሬ ብዙ ጀግኖች አትሌቶች አፍርተናል፡፡ በዚህም በሩጫው ዓለም ፊት አውራሪ ለመሆን በቅተና፡፡ በተረፈ በሁሉም ነገር እንዝጭ ብለን ወድቀናል፡፡ ስለሆም የእናቴ ቀሚስ ጠለፈኝ እያልን ከማሳበብ በአስቸኳይ አንድ ሆነን ከወደቅንበት እንነሣ እላለሁ፡፡

በየጊዜው የሚደረጉ የውህደት እንቅስቃሴዎች ሊፈርሱ የሚችሉት በበርካታ ምክንያቶች ቢሆንም እንደኔ የሥልጣን ጥም፣ ንዋይ መፈልግና ብሔርተኝነት (ጎሠኝነት) ዋነኞቹ ምክንያቶች ሣይሆኑ አይቀሩም፡፡ በርካታ ፓርቲዎች እንደ እቁብና ማህበር በብሔርና በመንደር ተሠባስበው ገዥውን ፓርቲ ጎሠኛ፣ ጎጠኛ፣ ከፋፋይ ብለው ይወቅሳሉ፡፡ መጀመሪያ የነጠረ አቋም ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከ60 በላይ ፓርቲዎች በሀገሪቱ አሉ፡፡ ይህ እንደ ትሮይ ፈረስ የሚጋልበንን አምባገነን አገዛዝ ለማጀብ ነው ወይስ ለመታገል? ፓርቲዎች ራሳቸውን ሊጠይቁ ይገባል፡፡ እኔ ለይቼ ለመውቀስ አይደለም፡፡ ሁሉም ላይ ችግር አለ፡፡ ውህድ ፓርቲ ከመፍጠር (ከትብብር አኳያ) ማለቴ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነው፡፡ ስለሆነም እውነተኞቹ ሠላማዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሙሉ ትብብር በማድረግ ይህነን አስከፊ ሥርዓት በሠለጠነ መንገድ ከሥልጣን አውርደው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እውን እንዲሆን እንቅልፍ አጥተው መታገል አለባቸው፡፡ ያኔ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከጎናቸው ይሆናሉ፡፡ ስለሆነም ተደናብረው ሕዝቡን ከሚያደናብሩ ለስልጣን ሳይሆን ለለውጥ ሊሰሩ ይገባል፡፡

ለዚች ሀገር ለለውጥ የሚሠራ ፓርቲ እግዚአብሔር ያድላት፡፡ አሜን!

(አቶ ደረጀ መላኩ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ናቸው)

ወጣት ተማሪዎች - የሰላማዊ ትግል ፈር ቀዳጆች

እያስፔድ ተስፋዬ

የአሁኑ ትውልድ ጠንቅቆ መገንዘብ ያለበት አብይ ሀቅ ኢትዮጵያውያን ለጭቆና መቼም እጅ ሰጥተዉ የማያዉቁ መሆናቸውን ነው። ሸፍተዋል፤ አምጸዋል፤ ጠላት በስተፍጻሜዉ እስኪንበረከክም ወደር የሌለዉ መስዋዕት ከፍለዋል። የምዕራቡ ዓለም ለወራሪው የሙሶሊኒ ጦር እጅ ስጡ ብሎ ሲሰብክ፤ ታንክን በምንሸርና ጦር ሊጋፈጡ በተነሱት ዜጎቻችን ላይ ሲያሾፍ፤ ጀግኖች አርበኞች ‹‹ሕይወቴ ለሀገሬ›› ብለው ተዋጉ፤ ተሰዉ እንጂ ‹‹እርሱ ያመጣዉን እርሱዉ ይመልሰዉ›› በሚል በዝምታ አልተገዙም። የነጻነት ሞገስ ያላበሱን እነዚያ አይበገሬ ጀግኖች አባት እናቶች ደግሞ በጊዜዉ አብዛኛዎቹ ጋራ ተራራ ወጥተዉና ወርደዉ ጠላቶቻቸዉን በተኮስ ከአፈር የሚለዉሱ ወጣቶች ነበሩ።

በቅርብ ጊዜዉ ታሪካችን ደግሞ፤ ለየካቲት 66 አብዮት ትልቁን አስተዋጾ ያደረገው የወቅቱ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ መሆኑን የማያውቅ የለም። ተማሪዎች የአጼውን ስርዓት ሲታገሉ፤ ድል ያለመስዋዕትነት እንደማይገኝ ጠንቅቀዉ የተረዱ ቢሆኑም ትግሉን የጀመሩት ብረት አንስተው አልነበረም። ያካሄዱት ትግል ፍጹም ሰላማዊ ነበር፡ ፡ በተቃውሞ ሰልፍ መብታቸውን ለማስከበር በመነሳት። የህብረተሰቡን ዋና ዋና የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግሮች እያነሱ (መሬት ለአራሹ፤ ድህው ይማር፤ ድህነት ወንጀል አይደለም፤ በአርሶ አደሩ ላይ ግብር አይጫን፤ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ይከበር፤ የሰላማዊ ሰልፍ መብትን የሚያግደው አዋጅ ይሰረዝ ወዘተ) የሚሉ መፈክሮችን አንግበዉ ሲሰለፉ አፈናው ይመጣ የነበረው፤ የኃይል እርምጃው ይወሰድ የነበረው (ከዱላ ወደ አስለቃሽ ጋዝና ከዚያም ወደ ግድያ ተሸጋግሮ፤ ጥላሁን ግዛውን፤ ደመቀ ዘውዴን ወዘተ...የገደለዉ) መንግስት ነበር። የውቅቱን የተማሪ እንቅስቃሴ ልዩና ታሪካዊ እንዲሁም ውጤታማ ያደረገው (የየካቲት 66 አብዮት ውጤቱ ነውና) በቅድሚያ በመፈክሮቹና በትግሉ ዙሪያ አምኖና ግልጽነትን የነበረዉ መስመር ይዞ የተሰባሰበ መሆኑ ነው።

ይህ እንቃስቃሴ አገዛዙና ደጋፊዎቹ ባዕዳንም የዘረጉበትን ከፋፋይ ሜራና የተከተረ አደረጃጀት ጥሶ በማለፍ በጋራና በተቀናጀ ማህበራዊ (የአዲስ አበባ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበር፤ የኢትዮጵያ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ብሔራዊ ማህበር..) ስብስቦች ስር መሰለፉና መታገሉም በአዎንታዊነቱ መጠቀስ ይኖርበታል። ተማሪዎች በፖለቲካ ገለባነት ራሳቸውን አጫጭተው የታገሉ ሳይሆኑ በጥልቅ ንባብ ስለፖለቲካ የነበራቸዉን ግንዛቤ ከማበልጸጋቸዉም በላይ ንቃታቸውን ለማሳደግና ለራዕያቸውም መልክ ለመስጠት የጣሩ በመሆናቸው ትግላቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊጠናከር በቅቷል። ከሁሉም በላይ ግን የኢትዮጵያ ተማሪዎች በዘር በጾታና በሀይማኖት ሳይከፋፈሉ በኢትዮጵያዊነትና በአንድነት ለኢትዮጵያ መታገላቸው ጠንካራ አድርጓቸዋል። ትግላቸው ብልጭ ድርግም የሚል ሳይሆን ቀጣይና ደፋርም እንደነበር መጥቀሱ ለዛሬ ትምህርት አለው። ታገሉ እንጂ ስለ ትግል በማውራት ብቻ አልተገደቡም። ሞት አይፈሬነታቸውንም ደማቸውን ለኢትዮጵያ አፍሰው የአጼውንም የደርግንም ሥርዓቶች አምርረዉ በመታገል አስመክረዋል። ለተከታዩ ትዉልድም አርዓያ ሆነዋል።

የተማሪዎቹ ጽኑና ሰላማዊ ትግል ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለ በመሄዱ ዉሎ አድሮ ወደ ፖለቲካ ድርጅት ምስረታ በማቅናት ለአብዮትና ለሥርዓት

ለውጥ መሠረት ሊሆን በቅቷል። ሰላማዊ ትግልን እንደ ትግል ስልት አማራጭ ስንወስድ ይህን ምርጫ በወሬ ደረጃ ቀይዶ ለማቆየት ሳይሆን በቀጣይ መልኩና ይዘቱ በተጨባጭ ትግል ህልው ለማድረግ ነው። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሕዝቡን ብሶት የሚያንጸባርቁ መፈክሮች አልጠፉም--እንዲያውም በርክተዋል። ለም መሬታችን ለባዕዳን አይሸጥ፤ ሕዝብ አይፈናቀል፤ የግድ ሰፈራ ይቁም፤ የኑሮ ውድነት ይቀንስ፤ ደሞዝ ጭማሪ ያስፈልገናል፤ በሀገራችን መሬት የውጭ ሀገር ወታደሮችና የጦር ሰፈሮች ቦታ የላቸውም፤ በሀይማኖቶች ውስጥ ጥልቃ መግባቱ ያክትም፤ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፤ የፕሬስ ነጻነት ይከበር፤ ወዘተ አሰባሳቢና ሰልፍ አስወጪ መፈክሮች ናቸው።

ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሰብዐዊ መብት ጉባዔ (ኢሰመጉ) መቼ ነው ‹‹የፖለቲካ እስረኞችን ይፈቱ ብለን በመስቀል አደባባይ ሻማ አብርተን ጨኸት እናሰማ›› ብሎ የሚያውቀው? ሰማያዊ ፓርቲ በቅርቡ በጎንደር ካደረገው ውጪ ማነው ለም መሬት ለሱዳን ተሰጠ ብሎ ሰልፍ የወጣው? በቀድሞ ተማሪዎች ጊዜ እንደነበረው ሁሉ ዛሬ ሀገር ውስጥ ያሉትና በውጭ ሀገር ያሉት ተማሪዎች ለጋራ ትግል ተቀናጅተዋል? ብዙ ጥያቄዎች አሉ፣ ሰላማዊ ትግልን በሚገባው ስፋትና ጥንካሬ ገና እንዳላደረግን የሚመስክሩ። በሕዝብ በኩል ያለው የግንዛቤ አነስተኛነትና ሌሎች ድክመቶችም እንዳሉ ሆነው በ1997ቱ እንደታየው የሚያደራጀውና በሚገባ የሚመራው ካገኘ ሕዝብ ሊታገልም መስዋዕትነትንም ሊክፍል ዝግጁ ነው። ከፍተኛ የደም ግብር ከተከፈለበት ከራሳችን ተመክሮ ለመማር እንቦዝን።

በአሁኑ ጊዜ፤ ከወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል ጋር በቀጥታ የተያያዙና በህይወቱም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ችግሮች ተበራክተዋል። እነዚህ ችግሮች በራሳቸዉ ለመፍትሄያቸዉ የወጣቱን ቁርጠኝነትና ያላሰለሰ ትግሉን የሚጠብቁ ናቸዉ። በሃገሪቱ ዉስጥ ሥራ አጥነት በጣሙን ተንሠራፍቷል። በዉጤቱ ተጎጅዉ በይበልጥ ወጣቱ ስለመሆኑ ብዙ ክርክር የሚያሻዉ ጉዳይ አይደለም። ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ተመርቀዉ ያለሥራ የተቀመጡ አያሌዎች ናቸዉ። አድጓል ተመንድጓል የሚባልለት የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት ከአንድ ዲግሪ በላይ ላላቸዉ የተማሩ ልጆቿ እንኳ ከድንጋይ ማንጠፍ በላይ የሥራ ዕድል ሊፈጥርላቸዉ አለመቻሉ የሚዘገንን ዕዉነት ነዉ። የዚያኑ ያህልም በሀገሪቱ ዉስጥ በአራቱም ማዕዘናት በመቁቋም ላይ ያሉት የሙያ ማሠልጠኛዎችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተሰጣቸዉን ስም መሸከም የማይችሉ፤ ከስታትስቲካዊ ፍጆታ ማሟያነት ወዲያ በጥራት ረገድ እዚህ ግቡ የማይባሉ ናቸዉ።

ብቁ መምህራንና የትምህርቱን የሥራ ሂደት መርጃ ዉስጣዊ ድርጅቶች ያልተሟሉላቸዉ ናቸዉ። በዚህ ሁኔታ፤ አገር ተረካቢዉን ትዉልድ ተገቢዉን የንድፈ ሃሳብና የሙያ ዕዉቀት ሳያስታጥቁ በገፍ ተቀብለዉ በገፍ ለሚያስመርቁት ተቋማት ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ የሚመደብላቸዉ ከፍተኛ ሀብት በከንቱ አልባከነም ማለት አይቻልም። የትምህርቱ ሥርዓት ደካማነት ደግሞ በዉጤቱ አገርንም ወጣቱንም የሚያሸመደምድ ነዉ። ለነገ የምናልማት ኢትዮጵያ ጥንካሬ በተተኪዉ ትዉልድ ብቃትና በዛሬዉ የትምህርት ይዞታ ላይ የተመሠረተ መሆኑ በአንክሮ ሊጤን የሚገባዉ ቁም ነገር ነዉ ።

ከትምህርትና ሥልጠና ጋር ተያይዞ በተለይ ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ዉስጥ የሚስተዋል ሌላም ጉልህ ችግር አለ። ይህም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛዎቹ ደረጃዎች የሚመደቡት ተቋማት አንዳችም አካዳሚያዊ ነጻነት የሌላቸዉ መሆኑ ነዉ። ተቋማቱ በየግቢዎቻቸዉ ዐጸድ ዉስጥ እንኳ መምህራኑና ተማሪዎቻቸዉ አከራካሪ በሆኑ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ላይ ያለማንም ጣልቃ ገብነትና ተጽዕኖ፤ ነጻ ሆነዉ ለመወያየትም ሆነ ምርምር ለማድረግ በፍጹም አይችሉም። የደኅንነቱ መንግሥታዊ መዋቅር የራሱን ባልደረቦች በተማሪ ስም በተማሪዎች መሃከል በመመሰግ የሚወራ የሚደረገዉን ይከታተላል። በዛሬዉ ዘመን የኮሌጆና የዩኒቨርስቲ ግቢዎች ከመካነ ዕዉቀትነታቸዉ ይልቅ፤ ነጻ አስተሳሰብ ያለዉ ዜጋ ከሚታነጽበት ሥፍራነታቸዉ ይልቅ፣ ካድሬ ካድሬ የሚሸቱ መሆኑ የአዋጁን በጆሮ እንደሚሉት ነዉ። በተገደበ መጠነ ርዕይ የሚገበይ ዕዉቀት ደግሞ ሁለ-ሰብዕናዉ የተሟላ ሰዉ ለመፍጠር አያበቃም፤ እግሮቹ በተሰነከሉ ሠንጋ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ጉግስ ከመግጠም የሚቆጠር ነዉ።

በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ታሪክ ዉስጥ ለትምህርት ተቋማት አካዳሚያዊ ነጻነትን ለማስገኘት የተደረገዉ ትግል በጊዜዉ ዉጤት ሊያስገኝ በቅቷል። የኋላ ኋላ አምባገነናዊዉ ደርግ ሁኔታዉን በጉልበት እስከለወጠበት ጊዜ ድረስ ተማሪዎች በዚህ ረገድ መብታቸዉን አስከብረዉ ነበር ማለት ይቻላል። በቅጥር ግቢዎቻቸዉ ዉስጥ እስከተወሰኑ ድረስ በወቅቱ አይነኬ በነበሩት የኢኮኖሚ፤ የማኅበራዊና የፖለቲካ ሁኔታዎች ላይ በግልጽ በመወያየት የመፍትሔ ሃሳቦችን ለማመንጨት የሚያስችል አንጻራዊ ነጻነት ነበራቸዉ። ከኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ታሪክ ጋር ሁሌም ሲጠቀሱ የሚኖሩት ‹‹መሬት ለአራሹ››ን የመሳሰሉት ታላላቅ ሕዝባዊ ጥያቄዎች የተጸነሱት፤ በፖለቲካዉ መስክ ዘለዓለም የሚታወሱት ዲስኩሮችና የሥነ ግጥም ሥራዎች በይፋ ሊደመጡ የበቁት በዚህ ረገድ በተገኘዉ ነጻነት ነዉ። በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ይታተሙ የነበሩት የተማሪዉ እንቅስቃሴ ልሳናትም እንዲሁ። ይህ ብቻም አይደለም፤ ተማሪዎቹ ከመምህራኑ ጋር ኃይላቸዉን አቀናጅተዉ ባደረጉት ቁርጠኛ ትግል፤ በወቅቱ በተለይ ከዝቅተኛዉ የኅብረተሰብ ክፍል አብራክ የተገኙ ወጣቶችን ህይወት የሚያዳጭ ጉዳት ያስከትላል ተብሎ የታመነበትንና የክፍለ ትምህርት ክለሳ (ሴክተር ሪቪዉ) ተብሎ የሚታወቀዉን መንግሥታዊ ፖሊሲ ከታተመበት ወረቀት አልፎ እንዳይተገበር ለማድረግ በቅተዋል ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ተማሪዎቹ ከሚያስተጋቧቸዉ መፈክሮችና በስሜት ከሚዘምሯቸዉ መዝሙሮች ወዲያ መሳሪያ አልነበራቸዉም። ትግላቸዉም ፍጹም ሰላማዊ ነበር። ቢደበድብም፣ ቢያስርም፣ ቢተኩስም ቢገድልም ያዉ፤ ለዚሁ ተግባር የታጠቀዉ መንግሥታዊ መዋቅር ነበር ዝግጁነቱ የነበረዉ። ነገር ግን ትግሉ መሥዋዕት መጠየቁ በታጋዮቹም ሆነ በእንቅስቃሴዉ መሪዎች ዘንዳ ያልታሰበ አልነበረም። ሥረ ምንጩ ሕዝባዊ ያልሆነ መንግሥት፤ ከሕዝብ ፈቃድ ዉጭ የቆመ አገዛዝ! ሰጥ ለጥ ብሎ አልገዛ ለሚል፣ ለመብቱ መከበር አሻፈረኝ ብሎ ለሚያምጽ ሕዝብም ሆነ የሕብረተሰብ ክፍል (የማባበያ ርምጃዎቹን አስቀድሞ)፣ ሁሌም መደምደሚያዉ የሞት ድግስ መሆኑን ከጥልቁ ንባባቸዉ ከተረዱት ሰንብተዋል። ነባሩን ሥርዓት እስከሚያርድ፣ ድምጻቸዉን አነባብረዉ በማስጮህ፣

‹‹ሕዝባዊዉን መንግሥት የምትሹ

ተዋጉለት አትሸሹ!››

‹‹አይገዛም አይገዛም ሕዝቡ ሳለ እየታገለ

ለአምባገነን መንግሥት ሕዝቡን ላልወከለ››

በጎብር ያስተጋቧቸዉ ዝማሬዎች ቋሚ ምስክሮች ናቸዉ። በዝማሬዎቻቸዉ የገቡትን ቃል ኪዳን አክብረዉ አልሸሹም። ያነሷቸዉ የመብትና የሕዝብ ጥያቄዎች የዋዛ እንዳልነበሩም ጥላሁን ግዛዉን የመሳሰሉ ቀዳሚዎቹ መሪዎቻቸዉ በመሥዋዕትነቱ ተርታ ከፊት ለፊት ቀድመዉ ሲወድቁ ተመስክረለት።

የትናንትናዎቹ ወጣቶች ካደረጉት ሰላማዊ ትግል ዉስጥ በዛሬዎቹ ተረኞች በአብነት ሊወሰዱ ከሚገባቸዉ ጥንካሬዎች አንዱ፤ በተቃራኒዉ ወገን የተሰለፈዉ አገዛዝ ተቀናቃኞቹንን ለመበተን ከሚያካሄደዉ መልክ ብዙ የመከፋፈል ዘመቻ ራስን የመጠበቅ ችሎታ ነዉ። የትም ይሁን በማን መሃከል፤ መከፋፈል የጥንካሬን፤ የመተባበርን ብረት አቅም የሚበላ ጨዉ ነዉ። እናም በአንድነት ጎልብቶ የሚጋፋን ኃይል ጥረት ለማምከን መደብ ወይም ዘርን፤ ዝቅ ካለም ጎሣን አጥር የሚያደርግ አፍራሽ መንግሥታዊ ዘመቻ ይከናወናል። የዚህ ዘመቻ ዉጤታማነት፤ የናዚዎቹ የፕሮፓጋንዳ ሰዉ እንደሚለዉ፤ የተገላቢጦሽ ‹‹ጥቁሩን ነጭ፤ ነጩን ጥቁር›› አድርጎ ለማሳመን ከበቃ ነዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ለምንገኘዉም ሆነ ድንበር ተሻግረዉ ለሚኖሩት ዜጎች ከፋፋይነትንና ዉጤቱን ለማስረዳት ብዙ መዳከር አያስፈልግም።

በተለይ ጎሳን ተመርኩዞ የሚደረግ የመከፋፈያ ዘዴ በአመዛኙ ሥራዬ ተብሎ ተይዟል። እንደዉነቱ ከሆነ፣ አድማጭ ካገኘ፣ በዘርና ጎሳ የመደራጀትን ያህል ለመብቴ እታገላለሁ ብሎ የተነሳን ወገን አመናምኖ የሚሰነጣጥር ክፉ በሽታ እንደሌለ እያየነዉ ነዉ። የተማሪዎችን መብት እናስከብራለን ብለዉ ከተነሱት አንስቶ ትልቅ አገራዊ ህልም አለን እስከሚሉት ቡድኖች ድረስ በዚህ በሽታ ተለክፈዉ ነን ያሉትን ሳይሆኑ ከአዉላላ ሜዳ የቀሩትን ብዙ አስተዉለናል። ወጣቱ የደቡብ ወይ የምሥራቅ ነኝ ካለ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ ወይም ሲዳማ ነኝ በሚል የጎሣ አጥር ከታጠረ አለቀለት፤ ለራሱም አልሆነ ለአገርም አልበጀ።

በተባበረ ሰላማዊ ትግል ድልን እንቀናጃለን! ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

የማዕድኑ ሙስና . . .

ከ ገፅ 7 የዞረ

ይቀጥሉበታል። የEITI የአባልነት ፈቃድ በመስጠት ለመስረቅ፣ የተፈጥሮ ሀብትን ታማኝነት በጎደለው የጮሌነት አካሄድ ጥቅምን ለማግበስበስ ለማይጠረጠሩ ባለሀብቶች በመስጠት የሞራል ልዕልና በጎደለው መልኩ ተበዳሪዎችን እና ለጋሽ ድርጅቶችን በመጭመቅ ሌላ ተጨማሪ ገንዘብ ማጋበስን የሚያስችል መብትን ይሰጣቸዋል።

የEITI አባል ለመሆን የተዘጋጁት ደረጃዎቹ እና መስፈርቶቹ ጸጥ የማድረጊያ የማስመሰያነት ዘዴዎች ናቸው። እነዚህ ጸጥ የማድረጊያ ስልቶች ከውጭ የሚሰነዘሩባቸውን ትችቶች ለመሸበብ ብቻ አይደለም የተዘጋጁት፤ ሆኖም ግን ከውስጥ ለሚነሱባቸው ሰላማዊ አመጾች ማዳፈኛ እንዲሆኑ ጭምር እንጂ። EITI በአሰልች እና ተደጋጋሚነት ባለው የቢሮክራሲ ውጣውረድ የተተበተበ ፍሬከርስኪ የበዛበት የአባልነት መቀበያ መስፈርቶች፣ ተጠያቂነት እና ግልጸኝነት ያለው መሆኑን ከጉራ ባልዘለለ መልኩ ዲስኩር ሲያደርግ ይደመጣል። ማዳም ሾርት ግልጽ ደብዳቤ ብለው አዘጋጅተው በለቀቁት ደብዳቤ ላይ ለድርጅቱ እጩነት ለመብቃት “ከEITI ጋር አብሮ ለመስራት በግልጽ እና በቀላል መንገድ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በቂ ምህዳር መኖር አለመኖሩ” ሁሉንም የህዝብ ግንኙት ስራዎች ሁሉ አፈር ድሜ አብልተውታል። ሌሎችስ በጣም አስመሳይ የሆኑ የባለስልጣን መስፈርቶች እንዴት ይታያሉ? እንዲሁ ዝም ብሎ የባህላዊ ጭፈራ እና ዳንስ ነውን?

ይቀጥላል...

የሚሊዮኖች ድምጽ ለነጻና ፍትሃዊ ምርጫ

ታምራት ታረቀኝ

የነገረ-ኢትዮጵያ አምደኛ የሆኑት ግርማ ሞገስ «የሚሊዮኖች ድምጽ ለመሬት ባለቤትነት ዘመቻ» በሚል ርዕስ መጋቢት 12/2006 ዓ.ም በዚሁ ጋዜጣ ባሰፈሩት ጽሁፍ ጥያቄው ወቅታዊ ዘመቻው ተገቢ መሆኑን በመደገፍ መደረግ ይገባዋል ያሉትንም ጥንቃቄ በመግለጽ አስተያየታቸውን አቅርበዋል። የመሬት ባለቤትነትን ጉዳይ ኢህአዴግ የፖለቲካ መጠቀሚያ ማድረጉን አስመልክቶ ባነሱት ሀሳብ ልዩነት የለኝም። የመሬት ባለቤትነት መብት በሚሊዮኖች ድምጽ ዘመቻ ይረጋገጣል በሚለው አስተሳሰባቸው እና በዘመቻው ወቅታዊነት ላይ ግን ልዩነት ስላለኝ ሀሳቤን ላካፍል።

ደርጎች አንድም በባህሪያቸው ሁለትም በህወሓት የፖለቲካ ስልት ተበልጠው (አውዜንን ያስታውሷል) አርሶ አደሩ ላይ ባደረሱበት በደል የቻለው በግልጽ ያልቻለው በስውር የህወሓት ደጋፊ እንዲሆን አበቁት፡፡ ሌላውም በሥርዓቱ በመማረር በህውኃት ደጋፊነት ባይሰለፍም የደርግ ደጋፊ መሆን አልቻለም። በመሆኑም ለኢህአዴግ ለሥልጣን መብቃት የአርሶ አደሩ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ሆነ። ኢህአዴግ ራሱን የአርሶ አደሩ ብቸኛ ወዳጅ አድርጎ የሚያቀርበውም በዚሁ መነሻነት ሲሆን የአርሶ አደሩ ኢህአዴግን መደገፍ ምክንያቱ ግን ከደርግ የተሻለ ሥርዓት በመናፈቅ እንጂ ኢህአዴግን በመወዳጀት እንዳልሆነ በአደባባይ አይናገረው እንጂ ኢህአዴግም የሚያውቀው እውነት ነው።

በ1996 ዓም ለምርጫ 97 ዝግጅት እኔና አሁን በእስር ቤት የሚገኘው አቶ አንዱአለም አራጌ በደሴ ወልድያ አድርገን ወደ ጎንደር ስንሄድ መንገድ ላይ በእግራቸው ሲሄዱ ያገኘናቸውን አንድ አርሶ አደር እንሸኝዎት አልንና አሳፈረናቸው። ወሬ ለመጀመር ብለን ጥያቄዎች ስናነሳ ማንም ትሆኑ ምን የራሳችሁ ጉዳይ በማለት ብዙ አወጉን። የዛሬዎቹ ንጉሶች እዚህ እኛ ሀገር በመሸጉበት ግዜ እኛ ስልጣን ስንይዝ ይህን እናደርግላችኋለን እንዲህ እንሆንላችኋለን ሲሉን ኖረው ወንበሩን ሲይዙት ከተናገሩት አንዱንም አልፈጸሙት። ሌላው ሌላው ሁሉ ቢቀር የመሬት ግብር ሁለት ብር ከሀምሳ እንደር.ጋለን ያሉትን አንረሳውም። ይሄው አሁን የሚያስከፍሉን ግን ደርግ ከሚያስከፍለን በእጥፍ ሆኗል። በዚህ የተነሳም አርሶ አደሩ ፊቱን አዞረባቸው፤ይህን ሲረዱ ስብሰባ እያሉ፣ በየለቅሶ ቦታ ካድሬዎቻቸውን እየላኩ እንዲህ አይነት ሰዎች፣ እንዲህ የሚባል ፓርቲ እየመጡ ስለሆነ ተጠንቀቁ ይሉናል። እኛ ደግሞ እኛ ሳናውቃቸው እናንተ አመጣችኋቸው፣ከመጡ እስየው ነው ከእናንተ የሚሻሉ ከሆነ እንቀበላቸዋለን እያልናቸው ነው በማለት ነገሩን።

እንዲህ ስንጨዋወት ቆይተን ላሊበላ መገንጠያ ጋር ስንደርስ እኔ ወደዚህ ነኝ በማለት ከመኪና ሲወርዱ ለማስታወሻ ፎቶ እንድንነሳ ጠይቀናቸው ፈቃደኛ ሆነው ፎቶ ተነስተን ልንለያይ ስንል ከኮታቸው የውስጥ ኪስ የጸሎት መጽኃፋቸውን አወጡና መገላለጥ ጀመሩ፣ ምን ሊያደርጉ ነው በማለት አይናችንም ቀልባችንም እርሳቸው ላይ ሆነ፡፡ ከመሀል ከብዙ ወረቀቶች ለይተው አንድ ወረቀት አወጡና ዘረጉልን። ያየነውን ማመን አቃተን። የኢዴፓ በራሪ ወረቀት ነበር፣ተመልክተን አድናቆታችንን ገልጠን አመስግነን መለስንላቸው። ከአርሶ አደሩ የሰማን ያየነው የኢህአዴግንና የአርሶ አደሩን የወዳጅነት ደረጃ የሚያመለክት ይመስለኛል። ምርጫ 97 ደግሞ ይበልጥ አሳይቶናል።

እናም አርሶ አደሩ በጽናት የሚመራው፣ተስፋ የሚያደርግበትና የሚያምነው አካል ማጣቱ እንጂ መሬት የመንግሥት በመሆኑ ምክንያት መሬቴን እንዳላጣ በሚል ፊርቶ ከኢህአዴግ ጋር አልተወዳጀም፡፡ በመሆኑም አቶ ግርማ «ህውኃት/ኢህአዴግ የገጠር መሬትን የፖለቲካ መጠቀሚያ በማድረግ የሥልጣን ዘመኑን አራዝሟል። በየአምስት አመት በሚደረገው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ በገጠር የሚኖረውን አርሶ እና አርብቶ አደር የምርጫ ፖለቲካ ጸባይ ሲቆጣጠርበት(በፍራቻ ተቀዋሚ እንዳይመርጥ ሲያደርግ) ቆይቷል ያሉት» ከፊል እውነት ሊሆን ይችላል። አርሶ አደሩን የሚገልጽ ግን አይሆንም።

የተቃውሞው ጎራ በየግሉ ተጠናክሮ በጽናት የማይታገል፣ርስ በርሱ የማይደጋገፍና የማይከባበር፣ ህዝቡን ለመስዋዕትነት የሚዳርግ እንጂ ለድል የማያበቃ መሆኑ እንጂ እንደ ሕዝቡ ለውጥ ፈላጊነት ኢህአዴግ የሚከተለው የመሬት ፖሊሲ መጠቀሚያው ሳይሆን መጠቂያው ይሆን ነበር።

አርሶ አደሩ አኗኗሩ የተበታተነ ሕይወቱ በመሬት ጥገኝነት ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ ሳይደግፍ ደጋፊ ሳይመርጥ የመረጠ ወዘተ እንደሆነ አድርገው ሊጠቀሙበት ያለ ፍላጎቱ እያስገደዱ ሊያሰልፉት የተመቸ ነው። አርሶ አደሩን በተለያየ ስልትና መንገድ ተጠቅሞ ለሥልጣን የበቃው ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘም በኋላ አርሶ አደሩን በቁጥጥሩ ሥር ማዋል ለሥልጣን እድሜው መራዘም ወሳኝ መሆኑን በመረዳቱ ነው የአርሶ አደሩ ሕይወት የተመሰረተበትን የመሬት ባለቤትነትን የመንግሥትና የሕዝብ በማለት አርሶ አደሩን ለመያዝ የጣረው።

በተለይም በከተማ ነዋሪው ዘንድ ያለው ተቀባይነት ደረት የሚያስነፋ አለመሆኑን በተግባር ሲያረጋግጥ በሥልጣን የመቆየቱን ተስፋ በአርሶ አደሩ ላይ አደረገ። አርሶ አደሩን ለመቆጣጠር የሚቻለው ደግሞ መሬትን የመንግሥት በማድረግ ነው የሚል እምት በማሳደሩ የመሬትን ጉዳይ ከፓርቲ ፕሮግራም አልቆ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40/3 «የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ኃብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው» የሚል ድንጋጌ በማስፈር የመሬትን ጉዳይ ሕገ መንግሥታዊ አድርጎታል። በመሆኑም ለመሬት ባለቤትነት ጥያቄ ትክክለኛውን ምላሽ ለማስገኘት ሕገ መንግሥቱን ማሻሻል ወይንም መለወጥ የግድ ይሆናል።ሕገ መንግሥትን ደግሞ በሰላማዊ ሰልፍም ሆነ በተቃውሞ ጨኸት መለወጥ አይቻልም። ሕገ መንግሥቱ ሊሻሻልም ሆነ ሊለወጥ የሚችለው በሁለት መንገድ ነው። አንደኛው መንገድ ሕገ መንግሥቱ ራሱን ስለማሻሻል በደነገገው መሰረት ነው። ይህኛው መንገድ አይደለም ለተቀዋሚዎች በጋራ ተስማምተው ካልሆነ በስተቀር ለኢህአዴግ አባል ድርጅቶች እንኳን በተናጠል ተግባራዊ ሊሆን የማይችል ነው።

ሁለተኛው መንገድ አሸንፎ ስልጣን መያዝ ነው። ለዚህ የሚያስፈልገው ደግሞ ሰላማዊ ሰልፍ ሳይሆን ብቁ ተወዳዳሪ ሆኖ መቅረብ ነው። ለዚህም ነው ዘመቻው የሚሊዮን ድምጽ ለመሬት ባለቤትነት ሳይሆን የሚሊዮን ድምጽ ለነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ቢሆን ተገቢም ወቅታዊም የሚሆነው።

የመሬት ባለቤትነትን ጨምሮ ኢህአዴግ ለህዝቡ የነፈጋቸውን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግና ዓላማን ለማስፈጸም ሥልጣን መያዝ ያስፈልጋል። ሥልጣን መያዝ የሚቻለው ደግሞ በምርጫ ነው፤ በነጻና ፍትሀዊ ምርጫ። ለነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ደግሞ የመንግሥት ቅንነትና ቁርጠኝነት እንዲሁም ነጻ ምርጫ አስፈጻሚ ተቋም ያስፈልጋል። ስለሆነም የመሬት ባለቤትነትንም ሆነ ሌሎች ማናቸውንም ዴሞክራሲያዊ የሕዝብ መብቶች ለማስከበር ወደሚያስችል ደረጃ ለመሸጋገር ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ መደረግ መቻሉ ወሳኝ ነውና የሚሊዮኖች ድምጽ ለነጻና ፍትሀዊ ምርጫ የሚል ዘመቻ ቢከፈት ምክንያታዊም ወቃታዊና ተገቢም ይሆናል።

በዚህ መሪ ቃል ዘመቻ ቢጀመር ነጻ ምርጫ የለነጻ ምርጫ አስፈጻሚ ስለማይሆን የምርጫ አስፈጻሚው ተቋም ነጻና ገለልተኛ ሆኖ እንዲደራጅ፣ የፖለቲካ ምህዳሩ ሁሉንም በእኩል የሚያሳትፍ እንዲሆን ጥያቄ ይቀርባል፣ሕዝቡ በተመራጭነት፣ በመራጭነትና በታዛቢነት በቆራጥነትና በንቃት እንዲሰለፍና ምርጫ 97ን እንዲደግም ጥሪ ይተላለፋል። ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ከመንግስት ጋር ወግኖ እንዳይሰለፍና ለእውነትና ለሕዝብ አጋርነት በመቆም ምርጫውን ከጅምር እስከ ፍፃሜው በንቃት እንዲከታተል ይጠየቃል።

የፓርቲዎቹ ጥያቄም እንበለው ዘመቻ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ላይ ቢያተኩር ኢህአዴግ የሚሰጠው የመልስ ምት አይኖርም። ቢኖርም ተራ መከራከሪያ ከመሆን አልፎ ከማንም ጆሮ ሊገባና ቀልብ ሊስብ አይችልም። የመሬት ጥያቄ ግን ለ21 ዓመት ሲጮህበትና ሲጠየቅ የኖረ ኢህአዴግም አንድና ቁርጥ ያለ ምላሽ የሰጠበት ነው። ዘመቻው ገቢራዊ ቢሆን አሁንም የሚሰጠው ምላሽ የተለመደውን የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ በህገ መንግሥት ምላሽ ያገኘ ስለሆነ በሰላማዊ ሰልፍና በጨኸት የሚለወጥ አይደለም የሚል እንደሚሆን ይገመታል።

ተቃዋሚዎች ንግግራቸውም ሆነ ተግባራቸው ለኢህአዴግ የመልስ ምት የተጋለጠ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያሻቸዋል። ጥንቃቄ ባለማድረጋቸውና በወቅታዊ ትኩሳት እየተመሩ ወይንም ሰሞነኛ ድጋፍ ያስገኙልናል በሚል በሚናገሩዋቸውና በሚያደርጉዋቸው ለመለስ መልስ ለሚቸገሩበት የመልስ ምት ሲጋለጡ ታዝበናል። የሚናገሩት የሚጽፉትም ሆነ ሊሰሩ የሚሞክሩት በቅድሚያ በቅጡ ታስቦ ተመክሮና ተዘክሮ ምን ውጤት ያስገኛል፣ምን ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፣ ከህብረተሰቡ ከመሰል ፓርቲዎችም ሆነ ሥልጣን ላይ ካለው ሀይል ምን ምላሽ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ መነሻና መድረሻው በዝርዝር ተፈትሾ በጋራ ተወስኖ ሊያመጣ ለሚችለው ጥቅምም ሆነ ጉዳት በቂ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ ነው መነገርም መተግበርም ያለበት።

መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው» ተብሎ በሕገ መንግሰት ከተደነገገ ሁለት ዓስርት አመታት ሊያስቆጥር ነው። በዚህ ግዜ ውስጥ ብዙ ተብሎአል፣ ስለሆነም በየግዜው እየተነሳ እየተጠየቀ ተቃውሞ እየቀረበ ኢህአዴግም የተደነገገው ተግባራዊ እንዲሆን መጠየቅ ተገቢም ወቅታዊም ይሆናል። ምርጫ 2007 ዋዜማ ላይ መገኘታችን ደግሞ የጥያቄውን ወቅታዊነትና ተገቢነት የሚያጠናክ ነው። በህገ መንግሥቱ የሰፈሩ ድንጋጌዎች መሬት ላይ ይውረዱ፣ በተግባር ይዋሉ ብሎ መጠየቅ ከማናቸውም ወገን ተቃውሞ ሊያስነዝር አይችልም። ለኢህአዴግ የመልስ ምትም አይመችም።

የጨኸታችን ምንነትና የአጫጫሀችን እንዴትነት በሚጮህበትም በሚጮህለትም ዘንድ ጨኸታችን በሚኖረው ተደማጭነት ላይ ቀላል የማይባል ፋይዳ አለው። የሕዝብን ዴሞክራሲያዊ የመብት ጥያቄዎችና ሀገራዊ ችግሮችን እንዲሁም የመንግሥትን ሕገ ወጥነት ጥያቄ አድርገን ተነስተን አጫጫሀችን ከተበላሸ ሰሚ ከማጣት አልፎ ተቃውሞ ሊያስነሳ፣ ተጠያቂነትም ሊያስከትል ይችላል።

በአንጻሩ የተነሳው ርዕሰ ጉዳይ እንደ ዘመኑ አባባል ውኃ የማይቋጥር ሆኖ አጫጫሀን ቢያሳምሩና ሰልፍ ቢያደምቁ የአንድ ሰሞን ትኩሳት መፍጠር ይቻል ካልሆነ በስተቀር የሚፈለገውን ግብ ለመምታት አያበቃም።

ስለሆነም የሚነሳው ጉዳይ ምንነትና የጥያቄ አቀራረቡ እንዴትነት ለሚፈለገው ውጤት መገኘት ወሳኝ መሆኑ ታውቆ የእቅዱ አንድ አካል ተደርጎ ሊታሰብ፣ በአፈጻጸም ዝግጅት ጊዜም ሊተኮርበት ይገባል። አበውስ ከአያያዝ ይቀደዳል ከአነጋገር ይፈረዳል ይሉ የለ።

እንደ ማጠቃለያ፣ በእርግጥ ለውጥ እንሻለን? ተቀዋሚ ፓርቲዎች በርግጥ ለለውጥ የሚታገሉ ናቸው? የሚነገር የሚሰራው፣ የሚታይ የሚሰማው በአብዛኛው ይህን አላመለክትህ ቢለኝ ነው መጠየቁ። ከልብ ለውጥ የምንሻ ከሆነ የለውጥ መገኛው መንገድ «አንድና አንድ »ብቻ ነው። እርሱም ምርጫ። በምርጫ ውጤታማ ሆኖ ለውጥ ለማስገኘት ደግሞ 1-ጠንካራ ተወዳዳሪ ሆኖ መቅረብ ይጠይቃል፣ 2-ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ያስፈልጋል 3-ነጻና ገለልተኛ ምርጫ አስፈጻሚ ተቋም መኖር አለበት 4-የመንግሥት ቁርጠኝነት ደግሞ በጣም ወሳኝ ነው።

ከዚህ ስፋትና ጥልቀት ካለው ተግባር አንጻር ምርጫው አንድ ዓመት በቀረው በአሁኑ ግዜ በተቃውሞው ጎራ ስለ ምርጫ ምን እየተሰራ ነው ብለን ብንጠይቅ አጥጋቢ ምላሽ ስለማግኘታችን እጠራጠራለሁ።

ያለፈው አልፏል፣ ልንማርበት እንጂ ልንማረርበት ፣ልንቆጭበት እንጂ ልንካሰስበት አይገባም፡፡ ልንማረርና ልንካሰስ የምንችለው በቀሪው ግዜም እንደ እስካሁኑ የአንድ ሰሞን ሙቀት በሚፈጥሩ ጉዳዮች ላይ ማተኮር፣ከተግባር ይልቅ ለፕሮፖጋንዳ ቅድሚያ መስጠቱ የቀጠለ እንደሆነ ነው።

ስለሆነም ከልብ ለለውጥ የምንታገል፣ ለሰላማዊ ትግሉ አሸናፊነት በጽናት የምንቆም፣ከራስ በላይ ሀገር ከሥልጣን ይበልጥ ሕዝብ የሚል የጸና እምነት ካለን ወቅታዊውም አስፈላጊውም ጥያቄና ትግል ምርጫ ነው። ስለሆነም በዚህ መንፈስና ዝግጁነት ላይ የሚገኙ ተቀዋሚዎች በሙሉ የውህደትና የህብረት እንካሰላንቲያቸውን አቁመው፣ ስሜት ለማነሳሳት የሚያደርጉትንም እንቅስቃሴ ገታ አድርገው ለነጻና ፍትሀዊ ምርጫ እውን መሆን የተጠና የታቀደና የተባበረ እንቅስቃሴ ሊጀምሩ ተገቢና ወቅታዊ ነው። ምርጫ በሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሶ አይነት እንቅስቃሴ ተካሄዶ ውጤት ሊያመጣ አይችልምና።

የተቃውሞው ጎራ በየግሉ ተጠናክሮ በጽናት የማይታገል፣ርስ በርሱ የማይደጋገፍና የማይከባበር፣ ህዝቡን ለመስዋዕትነት የሚዳርግ እንጂ ለድል የማያበቃ መሆኑ እንጂ እንደ ሕዝቡ ለውጥ ፈላጊነት ኢህአዴግ የሚከተለው የመሬት ፖሊሲ መጠቀሚያው ሳይሆን መጠቂያው ይሆን ነበር።

የሰማያዊ ፓርቲ ማሕበራዊ መርሆች

የማህበራዊ ስርዓታችን መርሆ በብሔራዊ ማንነቱ የሚኮራ፣ በአእምሮውም ሆነ በአካል የዳበረ ጤናማ ዜጋ እንዲኖር የሚያስችል፣ የዜግነት ክብርን፣ ሰላምን፣ ማህበራዊ ህይወትንና የእምነት ነፃነትን የሚያረጋግጥ የትምህርት፣ የጤና፣ የቤተሰብና የባህል ፖሊሲዎች ተቀርፀው በተግባር ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው፡፡

1. ኃይማኖት ሀ. ማንኛውም ዜጋ የፈለገውን ኃይማኖት የመከተል፣ የማራመድና የማስፋፋት መብትና ነፃነት ይኖረዋል፡፡ ለ. መንግስትና ኃይማኖት የተለያዩ ናቸው፤ አንዱ በሌላው ተግባር ጣልቃ እንዲገባ አይፈቀድም፡፡

2. ትምህርት ሀ. ሥርዓተ ትምህርትን ለመቅረፅ መምህራን፣ የትምህርት ባለሙያዎች፣ ወላጆችና ተማሪዎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡፡ ለ. የማቆያና የመዋዕለ ሕፃናት ትምህርት ልጆች ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲዘጋጁ የሚያደርግና ልጆች ከአዕምሮ ብስለታቸው ጋር የተመጣጠነ እውቀት እንዲያገኙ፣ ባህልና ቋንቋቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያደርግ ሥርዓተ ትምህርት ይዋቀራል፡፡ ሐ. መደበኛ ትምህርት ከአንደኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍሎች የተከፋፈለ ሆኖ፤ አንደኛ ደረጃ ከአንደኛ እስከ ስድተኛ ክፍል፤ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ከሰባተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል፤ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ሆኖ ይዋቀራል፡፡ መ. የቀለምና የሙያ ትምህርት ከአስረኛ ክፍል በኋላ የሚለያዩ ሲሆን ተማሪዎች የመረጡትን የትምህርት ዓይነት የመማር መብት አላቸው፡፡ የመረጡትን የትምህርት ዓይነት ትምህርት ቤቶቹ የመቀበል አቅም ውስን ከሆነ ተማሪዎች በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል ባላቸው አማካይ የትምህርት ውጤታቸው መሠረት ምርጫቸው ይጠበቅላቸዋል፡፡

ሠ. ትምህርት ተግባር ተኮር እንዲሆን፣ ጥራት ያለው የሳይንስና የቴክኖሎጅ፣ የስነ-ጥበባትና ስፖርት ትምህርት ዓይነቶች እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ በተለይ ለልዩ የፈጠራ ችሎታ አበረታች ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ረ. ሁሉም ዜጎች እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ትምህርታቸውን ከክፍያ ነፃ የመማር መብት አላቸው፤ ሆኖም የከፍተኛ ትምህርት ወጭን እንደአስፈላጊነቱ ሊጋሩ ይችላሉ፡፡ ሰ. በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ሕፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብት አላቸው፡፡ ሸ. መምህራንና የትምህርት ባላሙያዎች እንዲከበሩ፣ የሙያ ብቃታቸውን እንዲያዳብሩ፣ የተሻለ ጥቅምና ማበረታቻዎች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ቀ. ብሔራዊ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ከአንደኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ይሰጣል፡፡ በ. ማንኛውም ቤተሰብ ልጁን ወይም የሚያሳድጋቸውን ሕፃናት እስከ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መጨረሻ ድረስ የማስተማር ግዴታ አለበት፡፡ ተ. ሁሉም ዜጎች የትምህርት ሽፋን እንዲያገኙ የትምህርት ቤቶች በሁሉም አካባቢ ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ ቸ. ልዩ ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ችግሮቻቸውን ግምት ውስጥ የሚያስገባ የትምህርት ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ ነ. ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የሙያ ነክና የጎልማሶች ትምህርት እንዲስፋፋና ዜጎች ተግባር ተኮር እውቀት እንዲያገኙ፤ ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑና መሀይምነት ከሀገሪቱ እንዲጠፋ ልዩ እገዛ ይደረጋል፡፡

ኘ. በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎችን የሚያበረታታና ልዩ ተሠጥዖ ያላቸው ተማሪዎች ተሠጥዖአቸውን እንዲያዳብሩ እገዛ የሚደርግ ተቋም ይመሠረታል፡፡ ደ. የስኮላርሽፕ እና የተልዕኮ ትምህርት ዕድሎች ለሁሉም ዜጎች በእኩል ደረጃ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ መመዘኛውም የአካዳሚክ ብቃትና የሀገሪቱ የሙያተኞች ፍላጎት ሆኖ አሠራሩ ግላዕነት እና ተጠያቂነት ያለው ይሆናል፡፡ ጀ. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካዳሚያዊ ነፃነታቸው መሉ ለሙሉ የተረጋገጠ ሲሆን በራሳቸው ቻርተር እንዲተዳደሩ ይደረጋል፡፡ ጠ. በትምህርት ዘርፍ የግል ባለሃብቶች እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሁሉም ደረጃ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ የትምህርትን ጥራት የመጠበቅና የመከታተል ኃላፊነት የመንግስት ይሆናል፡፡

3. ጤና ሀ. አስቀድሞ በሽታን በመከላከል መርህ ጤናን መጠበቅ የሚያስችል ዕውቀትና አቅም ለመፍጠር ለሕብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ትምህርትና ለክትባት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ለ. የጤና ባለሙያዎች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት ለህብረተሰቡ እንዲያቀርቡ፣ ሙያና ክህሎታቸውን የሚያዳብሩ ስልጠናዎች እንዲያገኙ፣ የሚሰሩባቸው ተቋማት በተቻለ መጠን በዘመናዊ መሳሪያዎች የተሟሉ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ሐ. የጤና ባለሙያዎች የሙያ ስነ-ምግባራቸውን በማክበር የሞራል ግዴታቸውን እንዲወጡ ክትትልና እገዛ ይደረጋል፡፡ መ. ዜጎች አብዛኛው ወጭ በመንግስት የተሸፈነ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን አቅመ ደካሞችና የተለየ ትኩረት የሚስፈልጋቸው ነፃ ህክምና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ሠ. ሁሉም ዜጎች ፍትኃዊ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ የጤና ተቋማት በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

ረ. በወረርሽኝ መልክ የሚሰራጩ በሽታዎችን ለመግታትና ለመቆጣጠር ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ ይደረጋል፤ ሕክምናውም በነፃ ይሰጣል፡፡ ሰ. የባህል ህክምና በሳይንሳዊ ዘዴ እንዲታገዝና የተሻለ አገልግሎት ለህብረተሰብ ማቅረብ እንዲቻል ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ሸ. ሀገራችን በከፍተኛ ወጪ የምታስተምራቸው የጤና ባለሙያዎች ሀገራቸውን እየተው ወደ ሌሎች ሀገራት እንዳይሰደዱ የተሻሉ ጥቅሞች እንዲያገኙና የሚደርሱባቸውን የአስተዳደር ቅሬታዎች ለመፍታት ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ይዘረጋል፡፡ ቀ. በጤናው ዘርፍ መንግስት ወሳኝ ድርሻ ቢኖረውም የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም እንዲሳተፉ አመቺ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

4. ማህበራዊ ዋስትና ሀ.በመንግስት መስሪያ ቤቶችና በግል ድርጅቶች ስር የሚተዳደሩ ሠራተኞች ልዮ ልዮ የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ለ. የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን የሚያገኙ ሰራተኞች በጡረታ ወይም በፕሮቪደንት ፈንድ በመረጡት ስርዓት የጡረታ ገንዘባቸውን የማጠራቀም መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡ ሐ. ዜጎች አቅምና ፍላጎታቸው በፈቀደው የስራ ዘርፍ ሰርቶ የመኖር መብታቸው የተከበረ ይሆናል፡፡ መ. በጦርነት፣ በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋ የተፈናቀሉ ወገኖች ከደረሰባቸው ችግር እንዲወጡና ሰርተው እንዲተዳደሩ አስፈላጊው እገዛ ይደረግላቸዋል፡፡ ሠ. የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞች፣ ረዳት የሌላቸው ህፃናትና አረጋውያን የመኖር ዋስትናቸው እንዲጠበቅ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በፈቀደ መጠን አስፈላጊው እንክብካቤና ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ ረ. አቅማቸውና ዕውቀታቸው በፈቀደው ልዩ ልዩ የሙያ ዘርፎች ሃገራቸውን አገልግለው በጡረታ የሚኖሩ ዜጎች፣ በክብር እንዲያዙ የተለያዩ ድጋፎች እንዲደረግላቸውና የየጊዜውን የገበያ ሁኔታ የሚያገናዝብ የጡረታ ክፍያ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ሰ. የሥራ ክቡርነት ባህል እንዲዳብርና የሥራ ፈጠራ እንዲበለፅግ አስፈላጊው ሁሉ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

5. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሀ. ሀገራችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንድትደርስ መንግስት አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል፡፡ ለ. ከሀገር ውጪ የተሰሩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎች ለመተካት ወይም በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ በቂ ስልጠናዎችና ምርምሮች እንዲካሄዱ ይደረጋል፡፡ ሐ. በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በጥናትና ምርምር ዘርፍ ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ ዜጎችን ማበረታታትና መደገፍ ዓላማው የሆነ የሽልማት ድርጅት በህግ ይቋቋማል፡፡

6. ስፖርት ሀ. በአካልና በመንፈስ የዳበረ ብቁ ዜጋን ለመፍጠር እንዲሁም በዓለም የስፖርት መድረክ ሀገራቸውንና ራሳቸውን የሚያስጠሩ ምርጥ ስፖርተኞችን ለማፍራት ስፖርት በየደረጃው እንዲስፋፋ ጥረት ይደረጋል፡፡ ለ. ስፖርት ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ይደረጋል፡፡ ሐ. የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲገነቡ፤ በከተሞች ስፖርትና ለመዝናኛ የተመደቡ ቦታዎች ለዚሁ አገልግሎት ብቻ እንዲውሉ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ መ. የተለያዩ የስፖርት ፌዴሬሽኖች ከመንግስት ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው ይተዳደራሉ፤ መንግስት ተገቢውን ድጋፍና እገዛ ያደርጋል፡፡ ሠ. የግል ባለሀብቶች ወይም ነዋሪዎች በየአካባቢያቸው በመተባበር በተለያዩ የስፖርት ተቋማትን እንዲያስፋፉ ይበረታታሉ፤ አስፈላጊው ድጋፍም ይደረግላቸዋል፡፡

7. ኪነ-ጥበብ ሀ. ኪነ-ጥበብ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ለሀገር እድገት የሚያበረክተው አስተዋፅዖ የበዛ እንደመሆኑ መጠን ዘርፉ እንዲያድግና እንዲጠናከር ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ይደረጋል፤ ባለሙያዎቹም በነፃነት የመስራት መብታቸው ይጠበቅላቸዋል፡፡ ለ. የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች በየዘርፉ ለሚያበረክቱት የዓዕምሮ ፈጠራ ውጤት የህግ ጥበቃና ክለላ ይደረግላቸዋል፡፡ ሐ. የኪነ-ጥበብ ሙያን ለማዳበር መንግስትም ሆነ የግል ባለሀብቶች እንዲሁም የሙያው ባለቤቶች የመማሪያና የማሰልጠኛ ተቋማት እንዲያስፋፉ ሁሉን አቀፍ ጥረትና ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

8.ባህል ሀ. በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ አኩሪ ባህሎች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ባህሎቻችን በእኩልነት ተጠብቀው ይዞታቸውን ሳይለቁ ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆኑና ዓለም አቀፋዊ እውቅና እንዲያገኙ እንዲሁም ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን የኩራት ምንጭና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲሰጡ በተጠና የባህል ፖሊሲ እንዲመሩ ይደረጋል፡፡ ለ. ጠቃሚ ያልሆኑ መለወጥና መሻሻል ያለባቸው ጎጂ ልማዶች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር በመሆን በመወያየት እና ግንዛቤ በማስጨበጥ ለውጥ ለማምጣት ጥረት ይደረጋል፤ በምትኩ አዳዲስ እና ገንቢ ልምዶችና አስተሳሰቦች በህብረተሰቡ እንዲለመዱና እንዲሰርፁ ይደረጋል፡፡ ሐ. ኢትዮጵያዊን ሁሉ በኢትዮጵያ ያሉ ባህሎችን እንዲያውቁ እና ብሄራዊ ስሜታቸውን እንዲያጎለብቱ ጥረት ይደረጋል፡፡

9. አካባቢ ጥበቃ ሀ. የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ማውጣት ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በእኩል ደረጃ በማሳተፍ የተፈጥሮ ሀብት ከብክለት ለመታደግ የሚያስችል ፖሊሲ ተቀርፆ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ለ. በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ግለሰቦች ይበረታታሉ፡፡ ሐ. የቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራዎች ከቆሻሻ ማጠራቀሚያነት አልፈው ለመልሶ መጠቀም፣ ለማዳበሪያነት፣ ለኃይል ምንጭነት እንዲውሉ እንዲሁም የአካባቢ ብክለት ሳያስከትሉ እንዲያስወግዱ የሚያስችሉ ቴክኖሎጅዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡ ፡ መ. ኢንዱስትሪዎች አካባቢን ሊበክሉ የሚችሉ ተረፈ ምርታቶችን በተለየ መልኩ እንዲያስወግዱ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ሠ. አካባቢን የሚበክሉ ኢንዱስትሪዎች የብክለት ደረጃቸውን ለመቀነስ እንዲችሉ ጥረት ይደረጋል፡፡ ምዕራፍ ሦስት የኢኮኖሚ መርሆዎች የኢኮኖሚ መርሃችን ለዜጎች ሥራ መፍጠርን ዋነኛ አላማው ያደረገ እንዲሁም ለሃገራችን መሰረታዊ የልማት ችግሮች ሁነኛ መፍትሔ የሚሆን ለሁሉም ክፍላተ ኢኮኖሚ የተቀናጀ እድገት ትኩረት የሚሰጥ ከሕዝብ የሚገኘውን ልዩ ልዩ ግብዓት በሰፊው የሚጠቀም ኢኮኖሚን መገንባት ነዉ፡፡

አጠቃላይ ሀ. የእያንዳንዱ ዜጋ እድገት የኢትዮጵያ ሕዝብ እድገት መሠረት ሲሆን አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት መሰረትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡ ፡ ስለዚህም የኢኮኖሚው ፖሊሲ ትኩረት ሃገራዊ የኢኮኖሚ ኃይሎችን መፍጠርና ማጠናከር ይሆናል፡ ፡ ለ. የሃገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ገበያ-መር የኢኮኖሚ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ሐ. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፈለገው ሙያና የሥራ መስክ የመሰማራት፣ ሃብት የማፍራት፣ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ የመያዝ፣ የመሸጥ፣ የመጠቀምና በህጋዊ መንገድ ለሌላ ወገን የማውረስ ወይም የማስተላለፍ መብቱ ይከበርለታል፡፡ መ. የማንኛውም ሰው ንብረት አይወረስም፡፡ ሆኖም በግል የተያዘን ማንኛውንም ይዞታ መንግሥት ለሃገርና ለህዝብ ጥቅም መዋል አለበት ብሎ ሲያምን በጊዜው የገበያ ዋጋ ላይ የተመሰረተ ተገቢውን ካሳ ወይም ተመጣጣኝ ምትክ ወዲያውኑ አቅርቦ ይዞታውን ሊያስለቅቅ ይችላል፡፡ ሠ. የውጭ ኩባንያዎችና የግል ባለሃብቶች የሃገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ ኢኮኖሚው ውስጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ይበረታታሉ፡፡ ረ. የአካል ጉዳተኞች በኢኮኖሚው ውስጥ ያላቸው ሚና እንዲጠናከርና እንዲያድግ እንዲሁም ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡ ሰ. ሁሉም ዜጎችና የሃገሪቱ ክፍሎች ወደ ተመጣጣኝ የእድገት ደረጃ እንዲደርሱ በእድገት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙት ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ ሸ. የተፈጥሮ መዛባትና የአካባቢ መራቆት ከኢኮኖሚ እድገት መስፋፋት እንዲሁም ከሕዝብ ቁጥር እድገትና ፍላጎት ጋር እጅግ የተሳሰሩ በመሆናቸው የልማት ፖሊሲው ይህንን ያገናዘበ ይሆናል፡፡

ቀ. ከፍተኛ ሥራ አጥነትና የዋጋ ግሽበት ሲከሰት፣ የመንግሥት የበጀት ጉድለት ሲኖርና መሰል ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሲያጋጥሙ መንግስት የሚረጋጋት እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡ በ. የአሰሪና ሰራተኛ መብቶችና ግዴታዎችን፣ የኢኮኖሚ ነፃና ፍትሃዊ ውድድርን የሚያዳብሩ፣ የንብረት ባለቤትነት መብትን የሚያረጋግጡ፣ የተበላሸ አስተዳደርና ሙስናን የሚከላከሉና ሌሎች ለኢኮኖሚው አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ ህጎችንና መመሪያዎችን መንግስት ያወጣል፤ በሥራ ላይ ያውላል፡፡ ተ. የፖለቲካ መረጋጋት፣ ሰላምና ደህንነት ለኢኮኖሚው ጤናማ እድገት አስፈላጊ በመሆናቸው መንግስት እነዚህን እሴቶች የመጠበቅና የማስከበር ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ ቸ. ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቅ፣ አዋጭነቱ አጠያያቂ ወይም የሚያስገኘው ጥቅም ከረጅም ጊዜ በኋላ መሆኑ የታወቀ የሥራ ዘርፍ፣ ወይም ተፈላጊነቱ ለህዝብ ጥቅምና ስትራቴጅካዊ በመሆኑና በመሳሰሉት ምክንያቶች በግል ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ሊሸፈኑ ያልቻሉ ለኢኮኖሚው እድገት አጋዥ የሆኑ የልማት ተቋማትን መንግስት ከግል ባለሃብቶች ጋር በሽርክና ወይም ለብቻው አቋቁሞ ለሃገርና ለህዝብ ጥቅም እንዲውሉ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

ድ-ገፅ www.semayawiparty.org ይጎብኙ፡፡
ወይም Facebook BluePartyEthiopia ላይክ ፔጅ
semayawiparty Ethiopia ይከታተሉ፡፡
አድራሻ፡- ሰማያዊ ፓርቲ
ፖ.ሳ. ቁ 180298
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ +251118593006
+251118592950
አቢሲኒያ ባንክ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ቁጥር፡ C/A619

ከሙስሊሞች እንቅስቃሴ . . .

ከ ገፅ 5 የዘረ

በስተጀርባ ‹‹ህገ ወጥ›› አካል ሳይሆን ጭቆና እና ጣልቃ ገብነት እንዳለ በውል ያመለክተ ነበር፡፡ የእንቅስቃሴው አካላት ለዚህ ጭቆና እና ጣልቃ ገብነት ምክንያት የሚያደርጉት ደግሞ ገዥውን ፓርቲ ነው፡፡ ምናልባትም ከገዥው ፓርቲ ውጭ በግልጽ ከእንቅስቃሴው በስተጀርባ አንድ አካል አለ ከተባለ እንኳ በሰላማዊ ትግል የተካኑ አካላት ሊሆኑ እንደሚችሉ የተደረጉት እንቅስቃሴዎች አስረጅ ናቸው፡፡ በእርግጥ ገዥው ፓርቲ ከሙስሊሙ እንቅስቃሴ በስተጀርባ እንደ ሳውዲ ያሉ አገራት እንዳሉበት በገደምዳሜው ሲናገር ይደመጣል፡ ፡ ይሁንና እነዚህ አገራት የእሱው የራሱው ወዳጆች መሆናቸው የማይታበል ሀቅ ነው፡፡ ራሱ ኢንቨስትመንትና የውጭ ምንዛሬ በሚለው እነ ሳውዲ ወዳጆች ይሆናሉ፡፡ የሙስሊሞች እንቅስቃሴን ለመምታት ሲባል ደግሞ እነ ሳውዲ ኢህአዴ አብሯቸው የማይሰራና ‹‹ህገ ወጦች›› ሆነው ይቀርባሉ፡፡

<u>የኢህአዴግ የመነጠያ ስልት</u>

የሙስሊሙ እንቅስቃሴ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በሐይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባቱ በስፋት የሚነገርለት ገዥው ፓርቲ ‹‹ሐይማኖትና ፖለቲካ›› የተለያዩ መሆናቸውን በመግለጽ ተቃዋሚዎችም ሆኑ ሌሎች አካላት መብታቸውን ከሚጠይቁት ሙስሊሞች ጎን እንዳይሰለፉ ለማድረግ እየጣረ ይገኛል፡፡ ተቃዋሚዎች የሙስሊሞቹን ጥያቄ የመብት ጥያቄ አድርገው ሲያቀርቡም እነሱ የማያውቁትን እምነታዊ ካባ ይደረብላቸዋል፡ ፡ የሙስሊሙ እንቅስቃሴም ሆነ ተቃዋሚዎች በስተጀርባቸው አንዳች አካል እንዳለ በማስመሰል ተከታታይ ክስ ይቀርብባቸዋል፡፡ ይህ ስልት ባለፉት ጊዜያት በተደጋጋሚ የታየ እንደመሆኑ በቀጣይ የሙስሊሙ እንቅስቃሴና የሙስሊሞች ጥያቄ እንዲመለስ ጥያቄ በሚያቀርቡ ተቃዋሚዎች ላይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል መገመት ይቻላል፡፡

‹‹ዓለማዊ›› በሚባሉ አገራት ቤተ እምነቶች በመንግስት ውሳኔም ሆነ ፖሊሲ ላይ ቀላል የማይባል ተጽዕኖ ያሳድራሉ፡፡ አብዛኛዎቹ መንግስታት አንዳንዴ አጨቃጫቂ የሆኑ ጉዳዮችን ጨምሮ ከአንድ ሐይማኖት አካላት ድምጽ ላለማጣት ወይንም ለማግኘት የሚያስችሉ ፖሊሲዎቹን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ለአብነት ያህል አሜሪካ ውስጥ ውርጃ በቀዳሚ ምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡ ፡ መንግስትን የሚመሩት አብዛኛዎቹ ፖለቲከኞች በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ከቤተ እምነቶች ጋር አብረው ይሰራሉ፡፡ አብዛኛዎቹንም እንደ መሳሪያ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ሁለቱም ፖለቲካ ነው፡ ፡ ምንም እንኳ በሁሉም ቤተ እምነቶች መካከል ልዩነት ማድረግ አይገባም ቢባልም መንግስታት መሳሪያ የሚሆኑ አሊያም ስልጣናቸውን በስፋት የማይገዳደሩ ቤተ እምነቶች ጋር ሰፊ ስራ ሲሰሩ ማስተዋሉ ግን የተለመደ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር እያንዳንዱ የመንግስት አካልን የሚመሩት አካላት ከአንዱ እምነት ተከታይ አሊያም መልካም አመለካከት ያለው እስከሆነ ድረስ በሐይማኖትና በመንግስት ተቋማት መካከል ምንም አይነት ግንኙነት የለም ማለት አይቻልም፡፡

ህወሓት መራሹ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላም እንደ ትልቅ ስኬት ከሚመለከታቸው መካከል ‹‹በእልህ አስጨራሽ የፖለቲካ ትግል ምክንያት የተገኘውን የእምነት ነጻነት›› ትልቁ የፖለቲካ ስኬቱ አድርጎ መውሰዱ አዲስ አይደለም፡

፡ በወቅቱ መንግስትና ሐይማኖት መለያየት አለባቸው ሲል የነበረው ገዥው ፓርቲ ይህ ትግሉ ትክክለኛ ስለመሆኑ አሁንም ድረስ ይናገራል፡፡ በሌላ በኩል ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ እየወሰደው የሚገኘው ጣልቃ ገብነት ትክክል አይደለም ሲሉ ‹‹ሐይማኖትና ፖለቲካ መለያየት›› እንዳለባቸው ሲወቅሱ ይደመጣል፡፡

ሐይማኖት ፖለቲካው ውስጥ ዋነኛው ፖሊሲ የሚጫወት በመሆኑ በአሁኑ ወቅት አሜሪካን ጨምሮ የበርካታ አገራት ፖለቲካ ሐይማኖት ያስከትለዋል የሚለውን ጫና ምክንያት በማድረግ ፖሊሲዎቻቸውን እየቀያየሩ ነው፡፡ ለአብነት ብንወስድ እንኳ ኢህአዴግ ተጠቃሚ የሆነበትን የጸረ ሽብር ዘመቻ መንግስታት የእምነት ማንነትን ለማሳጣት በሚያደርጉት ጫና የተፈጠረ ፍትጊያ ነው፡፡ ኢህአዴግ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ እስረኞችና ሌሎች ባላንጣዎቹ ይቅርታ እንዲጠይቁም ሆነ ህዝብ እንዲቀበለው የሚያደርገው በ‹‹ሐይማኖት አባቶች›› በኩል ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ሌሎች በመሳሪያነት እንዳይጠቀምባቸው በሐይማኖት ተቋማት ላይ የራሱን ፖለቲካዊ አሻራም እያሳደረ ይገኛል፡፡ ህገ መንግስት ላይም ቢሆን ‹‹መንግስትና ሐይማኖት›› የተለያዩ መሆናቸው የሚገልጸው ኢህአዴግ ያጸደቀውን ህገ መንግስት ራሱ ፖለቲካዊ ሰነድ ነው፡፡ በዚህ ፖለቲካዊ ሰነድ ውስጥ ደግሞ ባይተገብራቸውም በርካታ ስለ እምነት ነጻነት የሚያወሩ መብቶች ታጭቀዋል፡፡ እምነት ደግሞ የፖለቲካ መብት ነው፡፡ ምክንያቱም እምነት አንዱ የማንነት መገለጫ ነው፡፡

እንደ ኢህአዴግ ከሆነ ይህ ሰነድ ስለ እምነት ነጻነትም ሆነ ገደብ ማውራት አልነበረበትም፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 11 መንግስትና ሐይማኖት መለያየት አለባቸው ሲልም ዓለማዊ መንግስት እንደሚኖር ነው እንጂ መንግስት እና ሐይማኖት ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም አይልም፡፡ ይልቁንም የሚለው መንግስታዊ ሐይማኖት መኖር የለበትም ነው፡፡ እነዚህ አሁም ሆነ ከአሁን ቀደም ‹‹መንግስት በሐይማኖታችን ጣልቃ አይግባ፣ መጅሊሱ ነጻ ይሆን...›› የመሳሰሉትን ጥያቄ የሚያቀርቡት አማኞችም የሐይማኖት መንግስት እንመሰርታለን ብለው አያውቁም፡፡ በእርግጥ በዚህ ህገ መንግስት የተደነገጉትም እየተከበሩ ነው ለማለት ይከብዳል፡፡ ህገ መንግስቱ ‹‹መንግስት በኃይማኖት ጉዳዮች ጣልቃ መግባት የለበትም እንዲሁም ሐይማኖት በመንግስት አሰራር ጣልቃ መግባት የለበትም፡፡›› ቢልም በአሁኑ ወቅት ኢህአዴግ ‹‹አህበሽ›› የተባለውን እምነት እየደገፈ ስለመሆኑ ከሙስሊሞቹ ውጭም ቢሆን ሌሎችም ምስክርነታቸውን እየሰጡ ነው፡፡

በተለይ በፌደራል ጉዳዮች አማካኝነት ስለ አህበሽ መልካምነት እና መንግስት የሐይማኖት ማንነታቸው ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ የሚፈልጉትን የሙስሊሙ ማህበረሰብ አባላት በ‹‹አጥፊነት›› የሚፈርጁ በርካታ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡ ፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ የመንግስት ሚዲያ ‹‹አክራሪ›› የሚላቸውን በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ እያወገዘ ነው፡፡ በመሆኑም ሐይማኖትና መንግስት ሊለያዩ ይችሉ ይሆናል እንጂ ሐይማኖትና ፖለቲካ በፍጹም ሊለያዩ አይችሉም፡፡ በእኛው አገር ደግሞ መንግስትና ሐይማኖት ህገ መንግስቱ በሚለው መሰረትም መነጣጠል አልቻሉም፡፡ መንግስት ይህን አዲስ ስልት የሚያነሳው ተቃዋሚዎች የሙስሊሙ እንቅስቃሴ አካላት ጎን እንዳይቆሙ ለማድረግ ነው፡፡

በመንግስትና በእስልምና ሐይማኖት መካከል ያለው ቅራኔ ደግሞ ዋነኛው ፖለቲካና ሐይማኖት እንደማይለያዩ ወቅታዊ ማሳያ ነው፡፡ ኢህአዴግ በሙስሊሙ ማህበረሰብ የእምነት ጉዳይ ጣልቃ ሲገባ ሐይማኖትና ፖለቲካ ሊነጣጠል እንደማይችል አጥቶት አይደለም፡፡ በተቃራኒው ተቃዋሚዎች የእምነታቸው መርህ የተጣሰው ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ጎን ሲቆሙ ለስልጣኑ አደጋ መሆኑን ስለሚያውቅ ‹‹ሐይማኖትና ፖለቲካ የተለያዩ ናቸው›› የሚል አጀንዳ ይስባል፡ ፡ ይህን በሚልበት ወቅት እንኳ ፌደራል ፖሊስ መስጊድ ውስጥ እየገባ የሙስሊሙን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር እየጣረ ነው፡፡ መጅሊሱ የተመረጠው ከሙስሊሙ ይሁንታ እና ከእስልምናም ህግ ውጭ በራሱ በገዥው ፓርቲ መሪነት ነው በሚል ቅሬታ ውስጥ ሊከት ችሏል፡፡ እስልምና ዋነኛውና ድንበር ተሻጋሪው ማንነት እንደመሆኑ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ይህን ማንነታቸውን ለማስጠበቅ ፖለቲካው ውስጥ መግባታቸው የግድ ነው፡፡ ኢህአዴግ ግን እነዚህን ኢትዮጵያውያን ‹‹አሸባሪ›› የሚል ስም ይለጥፍባቸዋል፡፡ እሱ ለእምነት ነጻነት መቆሙን በመግለጽ የፖለቲካ መስመሩን ለማስረዳት እንዳልሞከረ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከሙስሊም ኢትዮጵያውያን ጎን ሲቆም ‹‹የሙስሊም ፓርቲ›› ተብለው ይፈረጃሉ፡፡

ሐይማኖት ‹‹ስስ›› ከሚባሉት ጉዳዮች መካከል ቀዳሚው ነው፡፡ ህዝብ የእምነት ማንነቱን ከተጣሰ ይህን መብቱን ለማስከበር ከሚችል ኃይል ጎን በቀላሉ ይሰለፋል፡፡ ይህ ደግሞ እንደ ኢህአዴግ ያሉትን የአምባገነኖችን ስልጣን የሚያሳጣ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም የሙስሊሙን እንቅስቃሴ በማስተባበር የሚያግዙትንና ችግሩን በግልጽ የሚናገሩት የፖለቲካ ፓርቲዎችና አማኙን ለመነጣጠል ‹‹ሐይማኖትና ፖለቲካ›› የተለያዩ ናቸው የሚሉት ‹‹ቀይ መስመር›› አስምረዋል፡ ፡ በሌላ በኩል ሌሎች አማኞች ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ለመነጠልም ‹‹ሐይማኖትና ፖለቲካ›› የተለያዩ መሆናቸው እንደመሳሪያ እያገለገለ ነው፡ ፡ ለአብነት ያህል የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሙስሊሙ ወኪል እንደሆኑ በማስመሰል መንግስት ‹‹አክራሪና አሸባሪ›› ብሎ ለሚፈርጀው የሙስሊሙ እንቅስቃሴና ይህን እንቅስቃሴ እየደገፉ ነው ተብለው ከተፈረጁት ተቃዋሚዎች መነጠል ነው፡፡

የሌሎች ሐይማኖት አማኞችም በመንግስት ላይ የራሳቸው ቅሬታ አላቸው፡፡ እነዚህ አማኞችን ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ነጠለ ማለት ሙስሊሙም በእነሱ ጉዳይ ያገባኛል ብሎ እንዳይነሳ መከፋፈል ማለት ነው፡፡ ስለ አወሊያ፣ ኮሚቴውና መጅሊሱ የሚከራከሩትን ‹‹አክራሪና አሸባሪ›› ብሎ ከክርስቲያን ወገኑ መነጠል ከቻለ ሙስሊሙን የገዳሞቹን መፍረስ ከሚቃወመው ኦርቶዶክስ ጋር እየነጠለ መሆኑን ያውቀዋል፡፡ ስለሆነም ‹‹የሐይማኖትና ፖለቲካ መነጣጠል›› ትረካ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ከአማኞች ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያውያንን ሐይማኖትን መሰረት አድርጎ በመነጣጠል ከፋፍለህ ግዛ የሚያመች አዲስ ስልት በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ኢትዮጵያውያን እምነት ዋነኛው የፖለቲካው አካል መሆኑን አምነው መብታቸውን ለማስከበርና የሌሎች ወገኖቻቸው መብት እንዲከበር መቆም ሲችሉ ስልጣኑን እንደሚያጣ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ነው፡፡

የሂውማን ራይትስ ዎች . . .

ከ ገፅ 5 የዘረ

እናውቃለን፡፡ ሁሉንም እናውቃለን፡፡ ግን ምን ማድረግ እንችላለን? አእምሯችን ውስጥ ያለውን ለመናገር በጣም እንፈራለን፡፡” ሲል ሃሳብን በነጻነት መግለጽ ላይ ያለውን ችግር አስከፊነት ደረጃ ላይ መድረሱን ሪፖርቱ ያስረዳል፡፡

ሚዲያና ኢንተርኔትን በተመለከተ ደግሞ ሪፖርቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የኢንተርኔት ተጠቃሚ 1,5 በመቶ መሆኑን እና እጅግ አነስተኛ ቁጥር መሆኑን ጠቅሶ ሆኖም ገመድ አልባ (ዋየር ለስ) ኢንተርኔት እያደገ የመጣ መሆኑን ጠቅሷል፡፡ ፌስቡክ እጅግ ፈጣን በሆነ ሁኔታ በታዳጊ አገሮች እያደገ መሆኑን የሚያብራራው የሂውማን ራይትስ ዎች ሪፖርት ኢትዮጵያ ውስጥ ወጣቱና የተማረው ክፍል በሰፊው እየተጠቀመው እንደሆነ ገልጿል፡፡ ስካይፒም እየተስፋፋ ነው ይላል፡፡ ትዊተር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ሰፊ ተቀባይነት እንደሌለው ያስረዳል፡፡

መንግስት በብቸኝነት (monopoly) የተቆጣጠረው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪውን ድርጅት “የሚታለብ ላም” እያለ እንደሚጠራው ያብራራው ሪፖርቱ ድርጅቱን በአለም ባንክ እና ሌሎች ድርጅቶች ውድድርን እንዲፈቅድና ለግል ድርጅቶች እንዲሰጥ ግፊት ቢደረግበትም አለመፍቀዱ አሳዛኝ መሆኑን ሪፖርቱ አትቷል፡፡ በርካታ ግለሰቦች በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሲውሉ የፖሊስና ደህንነት ሃላፊዎች ለረጅም ጊዜ ሲከታተሏቸው እንደነበር እንደሚነግሯቸው ያስረዳሉ የሚለው ሪፖርቱ የጸጥታና ደህንነት ሰዎች የተጠርጣሪዎችን ሙሉ መረጃ ከኢትዮ ቴሌኮም እንደሚያገኙ ሪፖርቱ ያምናል፡፡ አንድ የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ ፓርቲ አባል የነበረ ግለሰብ አስተያየት ለሃሳብ ማጠናከሪያነት አቅርቧል፡፡ እንዲህ የሚል አስተያየትን ለሂውማን ራይትስ ዎች ሰጥቶ ነበር፡፡ “በቁጥጥር ስር ውዬ ከታሰርኩ በኋላ አንድ ቀን ወደ ቢሮ ጠሩኝ፡፡ ያነጋገርኳቸውን ሰዎች በሙሉ ዝርዝር ነበራቸው፡፡ ሃላፊው ‹እገሌ ከሚባል ግለሰብ ጋር ስለ እዚህ ጉዳይ አውርተሃል› አለኝ፡፡ ዝርዝሩን አሳየኝ፡፡ 3 ገጽ ዝርዝር ነበር፡፡ ሰአትና ቀን፣ ስልክ ቁጥር፣ የኔ ስም እና ያናገርኩት ሰው ስም ሰፍሯል፡፡ ‹እያንዳንዱን እንቅስቃሴህን መንግስት እየተከታተለው ነበር፡፡ የተቀረጸው ድምጽህ አለንና አትክደንም፡፡ እገሌ ለሚባል ድርጅት ኢሜይል መላክህንም እናውቃለን› አሉኝ፡፡ እኔም ዝም አልኩኝ.....” ይላል፡፡ ይህ ተቃዋሚ ፓርቲ አባል ግለሰብ መንግስት የግለሰቦችን ግላዊ ነጻነትን በመጋፋት እንደሚሰልል ማስረዳቱን ሪፖርቱ ያስረዳል፡፡

ሪፖርቱ ለተለያዩ አካላት መልእክቱን አስተላልፏል፡፡ ከሁሉም ቅድሚያ የሰጠው ለኢህአዴግ ነበር፡፡ ሪፖርቱ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይሰሩ የተዘጉ የፖለቲካ ፓርቲ ድህረ ገጾች፣ሚዲያ እና ብሎጎች (blogs) በሙሉ እንዲከፍት እና ድህረ ገጾችን መዝጋት የሰዎችን መረጃ የማግኘት መብት ስለሚጻረር ወደፊትም እንዳይፈጸሙ ሲል የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪው ድርጅት ጠይቋል፡፡ መንግስት ሰዎች ሃሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ መብታቸውን በመጠቀማቸው የሚደርስባቸውም ጫና ይቁም ይላል ሪፖርቱ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የግለሰቦችን የግል ኑሮ የሚመለከቱ መረጃዎችን የመጥለፍ እና ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ በምርመራ ጊዜም ይሁን በሌላ ሁኔታ መውሰድን ተችቷል፡፡ ኢህአዴግ ሊያስተካክላቸው፣ሊያሻሽላቸውና ሊለውጣቸው ይገባሉ ያላቸውን ከ12 በላይ ነጥቦች በሪፖርቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡

ለአለም አቀፍ የቴክኖሎጂ ተቋማትና ኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት ለሚሰጡ የቴሌኮም ድርጅቶች ሪፖርቱ ያስተላለፈው መልእክት በአጭሩ የቴክኖሎጂ ምርቶችንና አገልግሎቶችን አላግባብ እንዳይውሉ ያሳስብ ነበር፡፡ የመብት ጥሰቶች ሲፈጸሙም ድርጅቶቹ አገልግሎታቸውን ማቋረጥ ወይም የቴክኒክ ድጋፎችን መስጠት ማቆም እንዳለባቸው የሰብአዊ መብት ድርጅቱ አለም አቀፍ የቴክኖሎጂ ተቋማቱን ያሳስባል፡፡ ለቻይና፣ ጀርመን፣ ጣሊያን፣ እንግሊዝና ሌሎች መንግስታትን በተመለከተ ሪፖርቱ ያተኮረው “ለሁለት አገልግሎት” የሚውሉ ማለትም ለማጥቃትም ለልማትም የሚሆኑ ቁጥጥሮች ላይ እንዲያተኩሩ አጽንኦት ሰጥቶ ያስረዳል፡፡ ሰብአዊ መብትን የሚያስከብሩ ነጻ የእምባ ጠባቂ ተቋማት እንዲቋቋሙ ግፊት እንዲያሳድሩ ጠይቋል፡፡

አለም ባንክን፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ እና ሌሎች ለጋሾችንም ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሰዎችን የግል መብቶችን የሚጋፉ፣ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ፣የመደራጀትና የመንቀሳቀስ እንዲሁም መረጃ የማግኘ መብቶችን በሚጻረሩ ፕሮጀክቶች ላይ እንዳይሳተፉ ይመክራል፡፡ ሪፖርቱ በርካታ ጉዳዮችን ቢዳስስም ለዩናይትድ ስቴትስ መንግስት በተናጠልም ሆነ በጋራ ያስተላለፈው መልእክት አልነበረም፡፡ በሪፖርቱ መጨረሻ ሂውማን ራይትስ ዎች ለኢትዮጵያ መንግስት፣ ዜድ ቲ ኢ፣ሁአዌይ፣ ፍራንስ ቴሌኮም ኦሬንጅ፣ ሃኪንግ ቲም፣ ጋማ ኢንተርናሽናል (የፊን ፊሸር መሰለያ ሶፍትዌርን ለኢትዮጵያ መንግስት ሽጧል ይባላል) እና ለአለም ባንክ የጻፋቸውን ደብዳቤዎች እና አንዳንዶቹ የሰጡትን ምላሽ አያይዞ አስቀምጦታል፡፡

11 ቀናት ከጣይቱ ልጆች ጋር!

(የእስር ቤት ማስታወሻ)

ብርሃኑ ተክለያሬድ

እሁድ የካቲት 30 ቀን 2006 ዓ.ም የመገናኛ አደባባይ ገና በጧቱ ቢጫ ቲሸርት በለበሱ እንስቶች ተሞልቶ አደይ አበባ የበቀለበት ሜዳ መስሏል። እንስቶች በተለያየ ቡድን ተሏድነው ጭፈራውን ያስነኩታል፤ ዳንሱን ያቀልጡታል። ያለወትሮዬ በጠዋት ተነስቼ በመገናኛ ዲያስፖራ አደባባይ የተገኘሁት በዕለቱ የሴቶች ቀንን አስመልክቶ በተዘጋጀው የሴቶች ሩጫ የሰማያዊ ፓርቲ አባላት የሆኑ ሴቶች ጓደኞቼ እንደሚሳተፉና በሩጫው ላይም ‹‹ሊመለሱልን ይገባል!›› የሚሏቸውን ጥያቄዎች እንደሚያነሱ በመስማቴ ጓደኞቼን ለማበረታታትና የህዝቡን ስሜት ለማየት ነበር።

በቦታው ስደርስ ሌሎች ጓደኞቼ ቀድመውኝ ደርሰዋል። ከጓደኞቼ ጋር ተቀላቅዬ በጋራ የሩጫውን መጀመሪያ ሰዓት በመጠባበቅ ላይ ሳለን በዕድሜ የገፉ እናቶች ከሀይገር ባስ ውስጥ የመሮጫውን ቲሸርት ለብሰው መውረድ ጀመሩ። እናቶቹ ከመኪናው እየወረዱ በመርገብገብ ድምፅ፣

‹‹ብሔር ብሔረሰቦች

ኑኑ የኢትዮጵያ ልጆች.....›› የሚለውን መዝሙር ሲዘምሩ ተመከትኩ።

ከእናቶቹ በዕድሜ አነስ የምትል አንዲት ጎልማሳ ሴት እናቶቹ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲዘምሩ ታበረታታቸዋለች። አንዱ ጓደኛዬ ዛሬ ‹‹ማርች 8›› ነው ወይስ ‹‹ህዳር 29››? ብሎ አሳቀን። እናቶቹ በሴቶች ሊግ ‹‹ስፖንሰር››ነት ሩጫውን ለመካፈል የተመለመሉ ኑረዋል። ትንንሽ ሰንደቅ ዓላማዎችን እያውለበለቡ የመጀመሪያውን መዝሙር እየደጋገሙ እየዘመሩ ከሯጮቹ ጋር ተቀላቀሉ።

በግምት 3:00 አካባቢ ሩጫው ተጀመረ፡፡ በዓይኔ ሴት የትግል አጋሮቼን መፈለግ ጀመርኩ። አይታዩም! ቪዲዮ ካሜራ ከያዘ ጓደኛዬ ጋር አስፋልት ዳር ሆኜ ከሚተራመሰው ህዝብ መሀል ቃኘሁ። ከዚህ ሁሉ ሽህ ሴት መሀል ጥቂት ቆራጥ እንስቶችን መፈለግ ሞኝነት መስሎ ተሰማኝ። ‹‹ደግሞስ ሁሉም በሚጮህበትና በሚጨፍርበት ሩጫ መሀል የጓደኞቼ ድምፅ ተውጦ ይቀራል እንጂ ማን ሊሰማው?›› እያልኩ በማሰብ ላይ እያለሁ ከሯጮች መሀል ‹‹ነፃነት! ነፃነት!›› የሚል በእልህ የታጀበ ድምፅ ሰማሁ። አዎ! የጓደኞቼ ድምፅ ነው። የእኔ ጀግኖች 30 ሺህ ከሚሞሉ ሯጮች መሀል "ብሔር ብሔረሰቦች....." እያሉ ከሚዘምሩ የሴት ሊግ እናቶች፣ ስለ ቸኮሌት የሚዘምሩ ኮረዶች መሀል ሲቃ በተቀላቀለው ድምፅ ‹‹ነፃነት! እኩልነት! ፍትህ!›› እያሉ ይዘምራሉ። እምባዬ በዓይኔ ግጥም አለ። ከመሀላቸው አንዷ ግምባሯ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ህብረ-ቀለም ዓርማ አስራ አስራ መፈክር ታሰማለች። ጀግኖች ቆንጆዎቹ እህቶቼ ‹‹የጣይቱ ልጆች ነን!›› ሲሉ ይፎክራሉ፤ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ይዘምራሉ። አዎ፡-

‹‹ተከብረሽ የኖርሽው በአባቶቻችን ደም

እናት ኢትዮጵያ ያስደፈረሽ ይውደም!››

ሲሉ ይዘምራሉ። ካሜራ የያዘ ጓደኛዬን ጎትቼ በሩጫ መከተል ጀመርኩ። ፎቶ ግራፍ ለማንሳት የሚመቸን ቦታ እስክንደረስ በፍጥነት እንሮጣለን። ከዚያም ቆመን እንጠብቃቸዋለን። እንደገና እንሮጣለን። ድካም የለም። መሮጥ ፎቶ ማንሳት፣ መሮጥ ፎቶ ማንሳት መሮጥ.... አሁን ብዙ ሰው ተቀላቅሏቸዋል። እነሱ ነፃነት! ሲሉ ህዝቡ ተቀብሎ ነፃነት! ይላል።

‹‹የጣይቱ ልጆች ነን !

የጣይቱ ልጆች ነን !

ነፃነት እንፈልጋለን!

ነፃነት እንፈልጋለን!›› እነሱ ይጮሀሉ ህዝቡ ይቀበላል።

እኔና ፎቶ አንሺው ጓደኛዬ ተዳክመናል፡፡ እህቶቻችን ግን ምንም አይነት ድካም አይታይባቸውም። ‹‹በጨለማ መኖር ሰልችቶናል! ያለውሃ መኖር መሮናል! ‹‹እስረኞችን ማሰቃየት ይቁም!›› እያሉ ይጮሃሉ። አቤት ብርታት! አቤት ጉልበት! አንዷ ተቀብላ አንዷ ትቀጥላለች እውነትም ሴቶች የጣይቱ ልጆች፣ የማርታ የብርቱካን፣ የርዕዮት እህቶች ከመነሻው እስከ መድረሻው ያለ እረፍት ይጮሃሉ።

አሁን ሩጫው ወደማለቁ ተቃርቧል። በየመንገዱ ወጣቶቹን እየተከታተሉ ስልክ ይደውሉ የነበሩ የድህንነት አካላት ነን ባዮች ስለነበሩ እህቶቼን ምን ያደርጓቸው ይሁን ብዬ ተጨነኩ። ‹‹አረፍ በሉ አሁን ደርሳችኋል›› አልኳቸው። የአንዷ ግንባር ላይ የታሰረውን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ጥለት አስወልቁ ወሰድኩ፡፡ እህቶቼ ወደ ሩጫው ማጠናቀቂያ ደርሰዋል፡፡ ሩጫውን አጠናቀው መግባት እንደጀመሩ ወደ ዳር ወጣሁ። ድንገት ‹‹ቁረጥ፣ ቁረጥ፣ እሱ ጋር ቁረጣቸው!›› የሚል ድምፅ ሰማሁ፡፡ ዳር ይገፍ መመልከት ጀመርኩ። ያናድዳል! ፖሊሶች እየያዟቸው ነው። አንድ ሬድዮ መገናኛ ይዞ ሲቪል የለበሰ ግለሰብ ትዕዛዝ እየሰጠ አንድ በአንድ እየለየ ጓደኞቼን ወደዳር እያስወጣ ያዛቸው።

ግራ ገባኝ፣ ያጠፉት ጥፋት የለም። ሁሉም በሩጫው ላይ የተሳታፈ ሰው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እንደዘመረ፤ ሁሉ እነሱም ዘምረዋል። በሴቶች ቀን ሊነሱ ይገባቸዋል፤ ያሏቸውን ጥያቄዎች ህገ መንግስታዊ መብታቸውን ተጠቅመው በድፍረት አንስተዋል። ታዲያ ምን አደረጉ? ግራ ተጋብቼ አስፓልቱን ተሻግሬ ቆምኩ። ሌሎች የሰማያዊ ፓርቲ አባላትና አመራሮች እንደኔው ጉዳዩን በግራ መጋባት ይመለከታሉ። ኦ! ኢትዮጵያ እስከመቼ ልጆችሽ በአመለካከት ምክንያት ይታሰራሉ? እስከ መቼስ አምባገነኖች ቆራጥ የህዝብ ልጆችን በህዝብ ፊት ያለከልካይ እየሰሩ ይደበደባሉ? ለማን አቤት ይባላል? ፖሊሶች 7 ወጣቶችን በቁጥጥር ስር ካዋሉ በኋላ በአካባቢው ያለውን ሰው ማባርር ጀመሩ፡፡ እልህ ያዘኝ። ከአጠገቤ የሰማያዊ ፓርቲ የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ ጌታነህ ባልቻ በእልህ ይንቀጠቀጣል። ፖሊሶቹ ሰውን ሁሉ እያባረሩ እኛ ወዳለንበት አካባቢ ተጠጉ። በኪሴ ውስጥ የነበረውን ስልክ፣ ካሜራና ገንዘብ በአጠገቤ ለቆሙት ወጣቶች አስረከብኩ። ‹‹በፍፁም ጀግኖቹን ጥለን አንሄድም!›› ከጌታነህ ጋር በዓይን ተግባባን፤ ሌሎች ጓደኞቻችንን ንብረቶቻችንን ይዘው እንዲሄዱ ነገርናቸው።

አሁን ፖሊሶች አጠገባችን ደርሰዋል። ‹‹ዞር በሉ ከዚህ!›› አሉን።

‹‹አንልም!›› ሆነ መልሳችን።

ሬድዮ መገናኛ የያዘው አዛዥ ወደእኛ ተጠጋ፡፡ ‹‹ዞር በሉ እኮ ነው የምለው!››

ተቆጣ! ‹‹ዞር አንልም፤ እህቶቻችንን ለምን እንዳሰርካቸው ንገረን›› አልን።

‹‹ምን አገባህ? አሁን ከዚህ ጥፋ!›› ዱላውን ለመሰንዘር ተዘጋጀ።

‹‹ደብድበን እንጂ ከዚህ አንሄድም! ከእህቶቻችን ጋር መቀላቀል እንፈልጋለን!›› አለ ጌታነህ። አዛዡ ይኼኔ ተረጋጋ።

‹‹አብራችሁ ናችሁ እንዴ? በሉ ተቀላቀሉ፡፡›› ብሎ ለፖሊሶች ትዕዛዝ በመስጠት እንድንቀላቀል አደረገ። ወዲያው ከየት መጡ ያላልናቸው የካሜራ ባለሙያዎች ዙራያችንን ከበው በፖሊሶች እየታዘዙ ይቀርፁን ጀመሩ። መዝሙሩ አሁንም አልባራም።

‹‹ተከብረሽ የኖርሽው .....

ያስደፈረሽ ይውደም። ፖሊስ የህዝብ ነው!›› መፈክሩም ቀልጧል።

ይኼኔ ጌታነህና እኔ በህግ አምላክ ያለ ፈቃድ ‹‹አትቅረፁን ማንነታችሁን ንገሩን!›› በማለት እንዳንቀረፅ መከላከል ጀመርን፡፡ የተሰጠን መልስ ‹‹ዝም ብለህ የታዘዝከውን ፈፅም!›› የሚል ነበር። ይኼኔ እየቀረፀችን ወዳለች የካሜራ ባለሙያ ማንነቷን ለመጠየቅ ተንደረደርኩ። ሬዲዮ መገናኛ የያዘው የፖሊስ አዛዥ (በኋላ ስሙ ኮማንደር በርጋ መሆኑን ሠምቻለሁ) ማጅራቴን በዱላ መታኝ። ቆመው እየተቁነጠነጡ የነበሩ ፖሊሶች በሙሉ በድብደባው ለመሳተፍ ተሯሩጠው ከበቡኝ፡፡ በመጀመሪያ ባረፈብኝ ምት ለመውደቅ እየተንገዳገድኩ ስለነበር ጌታነህ ሮጦ እንዳልወድቅ በመያዝ የሚወርድብኝን ዱላ ይከላከልልኝ ጀመር። ከብዙ ማመናጨቅና ማጉላላት በኋላ በደህንነቶች ክትትል ከህዝቡ መሐል ተይዞ ክእኛ ጋር የተቀላቀለው ጓደኛችን አቤልን ጨምሮ 7 ሴቶች ሶስት ወንዶች በድምሩ 10 ሆነን በፖሊስ መኪና ከተጫንን በኋላ የካ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ ተወሰድን።

ሁላችንም በጋራ ወደ መሰብሰቢያ አዳራሽ ካስገቡን በኋላ በ2 የካሜራ ባለሙያዎች ቪድዮ እያስቀረጹ ‹‹የላካችሁ ማን ነው?›› የሚል ጥያቄ አቀረቡልን። ሁላችንም የሰማያዊ ፓርቲ አባላት እንደሆንን እና ማንም እንዳላከን፣ ሴቶችም ሀሳባቸውን የመግለጽ መብት እንዳላቸውና መብታቸውን ተጠቅመው እንደተናገሩ አስረዳን። ኮማንደሩ ኢቲቪያዊ ስድቦችን ያዥጎደጉድብን ያዘ። ‹‹ፀረ-ሰላም! ፀረ-ልማት! አሸባሪ! ህገ-ወጦች!...›› እያለ ተሳደበ። በጸጥታ አዳመጥነው። ከዚያ ለየብቻ እንድንቀመጥ ተደርገን። በመርማሪዎቹ ቢሮ እየገባን ስድብና ማስፈራሪያ የተቀላቀለበት ምርመራ ቀጠለ። ከዚያ በተለያየ አቅጣጫ እያዘዋወሩ ፎቶ ሲያነሱን መሸ።

ምሽት ላይ ወደማረፊያ ቤት እንድንገባ ተነገረን። ማረፊያ ቤት አልኩት እንዴ? ማጎሪያ ቤት ቢባል ይቀላል። 4 የወንዶችና የሴቶች ማጎሪያ ክፍል አለ። ሴቶቹ ወደ ሴቶቹ ክፍል፣ ወንዶቹም ተያይዘን ወደ ወንዶቹ ክፍል ገባን። እኛ የገባንበት ቤት 29 እስረኞች ነበሩበት። ራት ከተበላ በኋላ እስረኞቹ በህብረት መዝፈን ጀመሩ። ዘፈኑ ብሄር ብሄረሰቦች በሚለው ዜማ ሲሆን እኔን ከጣራ በላይ ያሳቀኝ ግጥሙ ነበር።

‹‹ሌቦች ሌቦች ነን ሌቦች

እኛ የሸገር ልጆች

የምንዘርፈው ወደ ቦሌ

መጨረሻችን ነው ከርቸሌ

ታስረንም በዋስ እንወጣለን

ተመልሰንም እንሰርቃለን

እኛ ልጆችሽ ተደራጅተን

እንዘርፍሻለን በቀን በቀን

ላላላላ ላላላላላላ.....›› የሚል ነበር።

መጀመሪያ በጣም አሳቀኝ፤ ከዚያ ደግሞ ግጥሙን ሳስበው ደነገጥኩኝ። ልጆቹ እያሉ ያሉት እኮ እንዘርፍሻለን በቀን በቀን ነው። ከግርምቴ ሳልወጣ እስረኞቹ የዘፈን ተረኞቹ እኛ መሆናችንን ነግረውን እንድንዘፍን ጠየቁን። በእስረኞች ጭብጨባ ታጀበን።

‹‹የትግል ጉዞው ታሪካዊ

አላማው ፍፁም ህዝባዊ

ራእያችንም ኢትዮጵያዊ

ሰማያዊ፣ ሰማያዊ

ፓርቲያችን ነው ሰላማዊ!››

ድምፃችንን ከፍ አድርገን መዘመር ጀመርን። ድንገት ግን የእስር ቤቱ በር በሀይል ተደበደበ!

ይቀጥላል...

ቅዳሜ መጋቢት 27 2006

የ‹‹ዴሞክራሲ ጽንሰ-ሃሳብ እና ለዘብተኛ ሌብራሊዝም››

በሚል ርዕስ በአቶ ጌታነህ ባልቻ አቅራቢነት በሰማያዊ ፓርቲ ጽ/ቤት ውይይት ይደረጋል፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በውይይቱ መሳተፍ የሚችል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

የውይይቱ አዘጋጆች